# ብኩርና

**አዘጋጅ**
መምህር ጥበበ ሥላሴ አሰፋ ገብሬ
Tibebesellassie Asseffa Gebrie
(Theologian)

ታኅሣሥ ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
Dec./Jan.2000
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

**የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው**

All Rights reserved

**ማሳሰቢያ**

የተወደዳችሁ የክርስቶስ ቤተሰቦች ያዘጋጀኋት መጽሐፍ ይዘቷ በርከት በማለቱ ለህትመትና ለአያያዝ ስለከበደች ለሁለት ለመክፈል ተገድጃለሁ፣ ስለሆነም ተከታዩን በሁለተኛው መጽሐፌ ላይ የማቀርብ መሆኔን በታላቅ መንፈሳዊ አክብሮት እገልጻለሁ።



## የመጽሐፉ መታሰቢያነት

1ኛ. ምስጢረ ሃይማኖት አሳውቀው የወንጌልን ፍቅር በልቤ ላኖሩት የቤተክርስቲያን አምድ ለነበሩትና በሠማዕትነት ላረፉት አባቴ ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ሊቀጳጳስ ዘሸዋ ትሁንልኝ።

2ኛ. የእኔነቴ ምስክርና የሕይወቴ ባለውለታ ለሆኑትና በጸሎትና በምክር በሃይማኖት ለዚህ ላበቁኝ አባቴ ለብፁዕ አቡነ ሰላማ የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ትሁንልኝ።

3ኛ. በጥበብ ሥጋዊ በጥበብ መንፈሳዊ ጠብቀው በቤተክርስቲያን ጥላ ሥር አንጸድግና እግዚአብሔርን ፈርቼ ሰውን አክብሬ እንድኖር ላደረጉኝ ቤተሰቦቼ:-

ሀ. ለአባቴ ለአቶ አሰፋ ገብሬ ምህረት

ለ. ለእናቴ ለወ/ሮ ክብበፀሐይ መንገሻ (ክበቡሽ) ትሁንልኝ

3ኛ. በኦርቶዶክሳዊት እምነታቸው ፀንተው መላ ዘመናቸውን ለቤተክርስቲያን ክብር ጠበቃ ሆነው ወንጌልን ለአለም ለሚሰብኩ ሊቃውንትና መምህራነ ወንጌል (ሰባኪያን) ትሁንልኝ።

*መምህር ጥበበ ሥላሴ አሰፋ ገብሬ*
*Tibebesellassie Asseffa Gebrie*
*(Theologian)*

# ምሥጋና

1ኛ. ይህችን የመጀመሪያ መጽሐፌን ለቤተክርስቲያን ሳበረክት ለጠ/ቤ/ክ/ድ/ቤት ባቀረብኩት ጥያቄ መሠረት ተፈቅዶልኝ ጽሑፌን በግረም የጎደለውን በመምላት የጎበጠውን በማቅናት ለህትመት እንድትበቃ ያደረጉልኝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን **የሊቃውንት ጉባኤን** በልዑል እግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።

2ኛ. በፀሎት፣ በምክር በሃሳብ ሳይለዩ ላበረታቱኝ ለተወዳጅ ቤተሰቦቼ እና ለቅርብ ጓደኞቼ በእግዚአብሔር ስም ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

3ኛ. ረቂቁን በኮምፒዩተር በማዘጋጀት እና በሊቃውንት ከተመረመረ በኋላም ለህትመት እንዲበቃ ያዘጋጁልኝን ኤሮ የኮምፒዩተር ሕትመትና የማስታወቂያ ሥራ ድርጅትን ከልብ አመሰግናለሁ።

*መምህር ጥበበ ሥላሴ አሰፋ*
*አዲስ አበባ*



# ማውጫ

## ክፍል አንድ


| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|
| መቅድም .................................... | 10 |
| መግቢያ .................................... | 14 |
| 1. አውሬው ማን ነው?.................................... | 17 |
| 2. ዘንዶው የተባለው ማን ነው?.................................... | 37 |
| 3. ምድር ሁሉ አውሬውን ይከተላል.................................... | 38 |
| 4. አውሬው ተሳዳቢ ነው .................................... | 38 |
| 5. የእግዚአብሄር ማደሪያ ማን ናት .................................... | 41 |
| 6. ከአውሬው ጋር ውጊያ የሚገጥሙት ቅዱሳን........ | 46 |
| 7. ከምድር የሚወጣ ሌላ አውሬ .................................... | 48 |
| 8. በመጨረሻ .................................... | 50 |


## ክፍል ሁለት


| | |
|---|---|
| 1. ምስጢረ ጥምቀት .................................... | 55 |
| 1.1. የመጥምቀ መለኮት ቅ/ዮሐንስ ስብከት ... | 57 |
| 2. ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት .................................... | 60 |

2.1. መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ........... 64

2.2. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ የተጠመቀበት ምክንያት.......... 65

2.3. ጌታችን በዮርዳኖስ ለምን እንደተጠመቀ .................................. 66

3. የጥምቀት ጥቅም .................................................. 70

3.1. ከእግዚአብሔር መወለድ /ልጅነትን ማግኘት/.......................... 70

3.2. ሥርየተ ኃጢአት /ከኃጥያት መንጻት/ ....... 72

3.3. ድኅነት ........................................................ 74

3.4. የቤተክርስቲያን ወገን /አባል/ መሆን .......... 75

4. ምሥጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ግዴታዎች ...................................... 77

4.1. የተጠማቂው ሃይማኖት ................................ 77

4.2. አጥማቂ ካህን ................................................ 79

4.3. በውሃ መጠመቅ ............................................ 80

4.4. በሥላሴ ስም መጠመቅ ................................ 82

5. ጥምቀት አንዲት ናት ................................................ 84





*ጥምቀት የማይደገም አንድ ብቻ የሆነበት ምክንያት.............................. 85

6. የአንዲት ጥምቀት ክፍሎች ................................................. 86

7. የህፃናት ጥምቀት ............................................................ 90


## ክፍል ሦስት


የመናፍቃን ማንነት ከቤተክርስቲያን ታሪክ አንፃር ................................................................ 107

ሦስቱ የቤተክርስቲያን ዓለም አቀፍ ጉባኤያት ............................................................ 109

1ኛ. የኒቂያ ጉባኤ ...................................................... 109

2ኛ. የቁስጥንጥንያ ጉባዔ ........................................ 110

3. የኤፌሶን ጉባኤ ................................................ 111

4ኛ. የኬልቄዶን ጉባዔ ................................................ 112

የልዩነታቸው ምክንያት ............................................. 113

ፕሮቴስታንትና ክፍፍሎቹ /ከሐድያንና ክህደታቸው/ መናፍቃንና ኑፋቄያቸው ............................................... 114

1. ሉተራውያን ................................................... 114

*ሉተር ማነው ........................................... 115

2. አናባፕቲስቶች /ዳግም አጥማቂዎች/ ................ 116
3. ካልቪኒዝም /Calvinism/ ................ 117
4. አንግሊካን /Anglican/ ................ 118
5. ሜቶዲስት /Methoddist/ ................ 119
6. ጴንጤዎች /Pente-Coastal/ ................ 119
ሀ. ዩኒተርያሊዝም ወይም ኢየሱስ ብቻ የሚሉት ናቸው /Only Jesus/ ................ 120
ለ. ትሪኒቴሪያን /Triterian/ ................ 121
7. የይሆዋ ምስክሮች /Jehouvea witness/ ................ 121
*ቻርልስ ራስል ማን ነው? ................ 223
8. ሰባልዮስ ................ 125
9. ፎጢኖስ ................ 126
10. አርሲሳውያን ................ 127
11. አውጣኪ ................ 128
12. መንክዩን ................ 128
13. አርጌንስ ................ 129
14. እስማኤላውያን ................ 130
15. ሞርሞናውያን /Mormons/ ................ 131



## ክፍል አራት

ቤተ ክርስቲያን ማለት ................ 133
ሥርዓተ አምልኮ መቼ ተጀመረ ................ 135
በብሉይ ኪዳን የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ................ 137
1. ሐመረ-ኖህ /የኖህ መርከብ/ ................ 137
2. ክህነተ መልከጼዴቅ ................ 138
3. ቤተ-ኤል /ቤቴል/ ................ 139
4. ምኩራብ /ሲና ጎግ/ ................ 140
5. ደብረ ሲና ................ 143
6. ደብተራ ኦሪት ................ 143
ቤተክርስቲያን በሊቃውንት አነጋገር ................ 145
ቤተክርስቲያን በፍትሐ ነገሥት ................ 151
ለቤተክርስቲያን ልታደርጉላት የሚገባ ቢኖር ................ 152
ሰባቱ ሰማያትና ቤተ ክርስቲያን ................ 153

## መቅድም

ከሁሉ አስቀድሜ በፀጋና በረድኤት ጠብቃ የዘለዓለም ልጅነት ሽልማ ላሳደገችኝ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጽሑፌን እንዳበረክት በነገር ሁሉ የረዳኝን የአባቶቻችን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይግባው፤ እያልኩ እንደ ሊቃውንት አባቶቼ ምስጢር አመስጥሬ ብዙ የምገልጸው የሌለኝ ብላቴና ብሆንም ከሊቃውንት አባቶቼ ያገኘሁትን፣ ቅድስት ቤተክርስቲያን ያስተማረችኝን መሠረት በማድረግ ለወገኖቼ ለህዝበ ክርስቲያን ሳቀርብ ታላቅ ደስታ ይሰማኛል።

የመፅሐፌንም ርዕስ ብኩርና ብያታለሁ። ከቃሉ ትርጉም እንደምንረዳው ብኩርና ማለት የመጀመሪያ፣ ታላቅ፣ ከሁሉ በፊት የነበረ ማለት ሲሆን መጽሐፏም በምስጢራዊ ይዘቷ ብኩርናን ትገልጻለችና እንዲህ አልኳት።

በመሆኑም፤

1ኛ. መጽሐፏ ስለ አውሬው ማለትም ስለ 666 ድብቅ ሚስጢርና ምንነት የምትገልፅ ስትሆን ለአውሬው መልዕክተኞች ራሳቸውን ያልሰጡ፣ ሃይማኖታቸውን በሃሰተኛው በአውሬው መንፈስ ተመርዘው (ልጅነት ያገኙባትን) የቀደመች ቅድስት እምነታቸውን በምንም በምን ያልለወጡ ብኩርናቸውን ያልጣሉ በመሆናቸው ብኩርና ብያታለሁ።



2ኛ. የልዑል እግዚአብሔር ባለሟል ተብለው ስማቸው በህይወት መጽሐፍ ተፅፎ የፀሎታቸውና የቃልኪዳናቸው ዕሴት ለሃጥአን ምርኩዝ፣ የሆኑ ቅዱሳንን ክብር፣ ቅድስናና ምልጃ በስፋት ታትታለችና፤ የእሊህን የቅዱሳንን ክብር ጠብቆ አውቆና ተረድቶ በፀሎታቸው መታመን ታላቅነት ነውና ብኩርና ብያታለው።

3ኛ. በቅድስት ቤተክርስቲያን ህግና ሥርዓት ተመርተው በየዘመኑ ራሳቸውን ለጥፋት በተለያየ መልኩ በመለዋወጥ ሥማቸውን በመቀያየርና ንፁሃን ምዕመናን ህግ አፍራሽ ሆነው ከአምላካቸው ተለይተው የክህደታቸው እድምተኛ እንዲሆኑ ከሚፈልጉ ከመናፍቃን የሐሰት ትምህርት ራስን ጠብቆ በቤተክርስቲያን ሥርዓትና ደንብ መኖር ከምንም በላይ ክቡርነትና ታለቅነት ነውና ብኩርና ብዬ የሰየምኳት ሲሆን፤

4ኛ. ኤሳው ለመብል ብኩርናውን እንደሸጠና ክብሩን እንዳጣ ዘፍ.25÷34 ኋላም በእንባና በንስሐ ተግቶ እንኳ ቢፈልግ አላገኘም ብሎ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልዕክቱ እንደተናገረው ዕብ. 12÷12-16 እኛም ተመልሰን የማናገኛትን የልጅነትን ክብር በሃጢአት በርኩሰት እንዳናጣ ብናጣም እንኳ ትንሳኤ ልቡናን ተነስተን ለክብር እንደምንበቃ ለዘለዓም ክብርና ድህነት የተዘጋጀን እንጂ ጥምቀታችን በከንቱ

የማይቀር፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ያለን መሆናችንን የምትገልጽ በመሆኗ መጽሐፏን ብኩርና ብያታለሁ።

በመጨረሻም ዓለም ለዚህ ለሰማያዊ በረከት ባለመታደሉ የዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ሃብት ባለቤት የሆነችው ዘወትር እጆቿን ወደ አምላኳ ወደ ፈጣሪዋ ከመዘርጋት በቀር አንድም ቀን እጇ ታጥፎ የማታውቀው የቅድስት ሃገራችን የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን እምነትና ሥርዓት ትውፊትና ክብር ስለምታበስር ብኩርና ብዬ ሰይሚያታለሁ። አዎ! ሌላው ዓለም እንጨት ጠርቦ ደንጊያ አለዝቦ በሚያመልክበት ጊዜ እንኳ ሃገራችን ኢትዮጵያ ግን የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን እንዳለ ኢያሱ (መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 24÷15) ልዑል እግዚአብሔርን ጌታዬ አምላኬ ብላ የኖረች ቅድስት ሃገር በመሆኗ ብኩርና ብያታለሁ።

የተወደዳችሁ ምዕመናን፤ ታናሽነቴን ሳትመለከቱ በመልዕክቷ ተጠቅማችሁ ከዘመኑ መናፍቃንና ከዚህ ከከሃዲ ትውልድ የክህደት መልዕክት ራሳችሁንና ቤተሰባችሁን እንድትጠብቁ መጽሐፏን ትመለከቷት ዘንድ በአክብሮት እየጋበዝኩ በተለይ የወንጌል ገበሬዎች የሆናችሁ አባቶቼና ወንድሞቼ መምህራን የመጽሐፏን ምስጢር ለምዕመናን በጣፈጠ እንደበታችሁ ንጹሁን የስንዴ ዘር ትዘሩ ዘንድ አደራዬ የጠበቀ



*በመሆኑም:-

የመጨረሻ መልዕክቴ ቢኖር እኛም ከተነገረው ትንቢት ከሚፈጸመው ክህደት ራሳችንን ጠብቀን፤

ኢትዮጵያዊት፣ ብኩርና
አርቶዶክሳዊት፣ ብኩርና
የቅዱሳን የቃልኪዳን ልጅ መሆን ብኩርና
ከከሃደያንና ከመናፈቃን ራስን መጠበቅ ብኩርና መሆኑን
አውቀን ብኩርናችንን ጠብቀን የክብሩ ወራሾች
እንድንሆን የልዑል እግዚአብሔር ቸርነቱ
የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕሟና ፍቅሯ
የቅዱሳን አባቶቻችን በረከታቸው ከሁላችን ጋር ይሁን
አሜን!

መምህር ጥበበ ሥላሴ አሰፋ

(Theologian)

## መግቢያ

የመጻሕፍትን ምስጢር መመርመር ብዙ ጥቅም ሲኖረው የራስን ማንነት አውቆ ራስን አስከብሮ ሰውንም አክብሮ በመጨረሻም ዘለዓለማዊ ዓለምን (መንግሥተ ሰማያትን) ለመውረስ ያበቃል።

በምንኖርበት ዘመን ሥልጣኔ ያደገበት ሁሉም ነገር ኮምፒዩተራይዝድ (Computerized) በሆነበት እና በሥልጣኔ ተራመድን የሚሉ ጠበብቶች በራሳቸው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱስን በሚተረጉሙበትና የመጻሕፍትን ትርጓሜ የቤተክርስቲያንን ትውፊት በማይቀበሉበት በዚህ ዘመን እንዲሁም ሰው ራሱ የለዘብተኝነት እምነት (Liberalism) እያለ እኔ ምን አገባኝ በዚህ ምድር በተድላ በደስታ ልኑር እንጂ ለሌላው አለ ለሚባለው ለማላውቀው ዓለም አልጨነቅም በሚልበት በዚህ ዘመን እኔ ከአባቶቼ አልበልጥም አባቶቼ በተጓዙበትና በክብር ላይ ክብር ባገኙበት ቀጥተኛ ጉዞ እጓዛለሁ የመጻሕፍትንም ምስጢር እመራመራለሁ የሚጠቅመኝንም እይዛለሁ በማለት የቅዱሳንን ቃል ኪዳን በማመን ሕገ ቤተክርስቲያንንን በመጠበቅ መኖር ስለሚያስፈልገን እንዲሁም አመለካከታችንን በማስፋት



ቀደም ሲል ያልተገነዘብናቸውን እውነቶች እንድንረዳ ዋናው የእግዚአብሔር አምላካችን እርዳታና ፈቃድ ቢሆንም መጻሕፍትን መመርመር ወሳኝ ነው። በመሆኑም መጻሕፍትን መመርመር አዲስ የእውቀት ወጋገን ስለሚፈነጥቅልን ስለ አለምም ሆነ ስለ ራሳችን ያለንን ግምት ይለወጣል። ህወታችንም ትርጉም ያለው ይሆናል።

ምናልባትም ይህን አነስተኛ መጽሐፍ በዘመኔ ሳበረክት ታላቀ መንፈሳዊ ደስታ የሚሰማኝ ሲሆን ዋናው ዓማዬም ከጥርጣሬ ምዕመናንን ለመመለስና ከክህደት ለማዳን ሲሆን በዘመናችን የተነሱትን የአውሬ መልዕክተኞች እግዚአብሔር በፈቀደ ከአባቶቼ ባገኘሁት ጥቂት እውቀት አሳፍሮ ለመመለስ በማሰብ ነው። በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ ሁሉንም የቤተክርስቲያንን ትምህርትና ምስጢር ማስፈር ስለማይቻል በጥቂቱ መጽሐፏ ጥሩ ግንዛቤ አላት ብዬ አምናለሁ።

በአንዳንድ ጸሐፊያን የተጻፉ መጻሕፍት በጣም ብዙ ጥቅሶች ሲደረደሩ ይታያሉ ምናልባትም ስህተት ላይሆን ይችላል ቢያንስ ነጥቡን የሚደግፉ ብዙ ጥቅሶች እንዳሉ ያሳያል፤ ይሁን እንጂ አንባቢው በዚህ በረጅም የጥቅስ ዝርዝር ተሰላችቶ አንዱንም ሳይመለከት እንዳያልፍ በማለት

የአበውን ትውፊትና ምስጢር ለማስታወስና ድብቁን የመጻሕፍትን ህይወት ለመመርመር እንዲቻል በዚህ መጽሐፍ የተመለከቱት ጥቅሶች የተወሰኑ ናቸው ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል ተብሎ እንደተነገረ።

ደራሲው ጥበበ ሥላሳ አሰፋ

ውድ አንባቢያን

መጽሐፉን ሲያነቡ ምናልባት በአብዛኛው ረቀቅ ያሉ ምስጢራት አሉትና ያልተረዱት ነገር ቢኖርዎት ደጋግመው ይመልከቱት እንዲሁም በእግርጌው ማስታወሻው (footnote) የተገለጸ ስለሆነ በተመለከተው ምልክትና ቁጥር በመመራት ያገናዝቡት ዘንድ አደራዬ የጠበቀ ነው።



# ክፍል ፩ (አንድ)

# አውሬው ማነው?

# "666"

*በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።*

"ዑቁ እንከ ዘከመ ተሐውሩ ከመ ጠቢባን ወአኮ ከመ አብዳን። እንዘ ታናሕስይዎ ለዝ ዓለም። እስመ እኩይ መዋዕሊሁ።" "እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።" /ኤፌ 5÷15-16/ ይህንን ቃል የተናገረው ታላቁ ሐዋርያ ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ሲሆን ቃሉም የተነገረው ለኤፌሶን ክርስቲያኖች ነው። ይህ ቃል የተነገረበት ምክንያት በወቅቱ

የነበሩት የኤፌሶን ምዕመናን ከሐዋርያት በተማሩትና በተረዱት አውነተኛና ቀጥተኛ ትምህርት ጸንተው ራሳቸውን በዘመኑ ከነበረው የስህተትና የክህደት እርሾ ጠብቀው በቀናው የሕይወት መንገድ ላይ በጥበብና በማስተዋል እንዲመላለሱ ነው። /ኤር 6÷16 ማቴ 16÷5-12 2ጢሞ 3÷13-14/

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌል "ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ። ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቆጠቁጥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደቀረበ እወቁ።" በማለት በዘመናችንና በጊዜያችን ከምናየው፤ ከምንሰማውና እንዲሁም ከሚሆነው ነገር ሁሉ በማስተዋል ልንማር እንደሚገባን አስተምሮናል። "እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።" /ማቴ 10÷16/ እንደተባለ እኛም ዛሬ እንደ ኤፌሶን ክርስቲያኖች ዘመኑን ልንዋጅ፣ ልንመረመርና ልናውቅበት ይገባል። /ኢዮብ 8÷8-10 ምሳ. 22÷6-28 2ኛጴጥ. 1÷10 1ኛጢሞ. 6÷20 2ጢሞ. 3÷1-17/



የዓለም ገጽታ ባልተጠበቀ ሁኔታ እየተለወጠ ዘመኑ ከሽማኔ መወርወሪያ ይልቅ እየፈጠነ ነው። ሁሉም ነገር በከፍተኛ ፍጥነት ወደ ፍጻሜ ዘመን እየተጓዘ ነው። ክስተቶች የዳግም ምጽአትን ምልክቶች እያሳዩ ነው። የ "666" ነገርም የዓለምን ትኩረት እየሳበው ነው። የ666 ማንነት ዓለምን እያከራከረ ነው። የተለያዩ አመለካከቶች በዚህ ትንግርት ዙሪያ በመሽከርከር ላይ ናቸው። በተለይም በአሁኑ ጊዜ ከባሕር ይወጣል የተባለው አውሬ መንፈስ በዓለም ላይ ሰፍኗል ለማለት ይቻላል። ለመሆኑ መጭው አውሬ ማነው? የሚነሳውስ ከየት ነው? የአውሬው ቁጥር የተባለው የ666 ምስጢራዊ ፍቺስ ምንድ ነው? የእነዚህን መሠረታዊ መጠይቆች መልስ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ከዚህ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

ይህን በራዕይ 13÷1 ላይ አውሬ ተብሎ የተጻፈውን ራዕይ በታናሽ እስያ ውስጥ በምትገኘው ፍጥሞ በምትባል ደሴት እንዳለ በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ በታላቁ የእግዚአብሔር መልአክ መሪነትና አስተርጓሚነት ያየው በቤተክርስቲያናችን ታዕገሎስ ተብሎ የሚጠራው ፍቁረ እግዚእ /የጌታ ወዳጅ/ የሆነው ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ነው።

(ራእይ 1፥9-11) በቤተክርስቲያናችን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ይህ የዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ <u>የአዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ</u> በመባል ይታወቃል። ምክንያቱም ስለዓለም ፍጻሜና ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ስለሚናገርና ስለሚተነብይ ነው። ስለዚህ ራእይ ሲባል ወደፊት ስለሚሆነው ነገር የሚገልጽና የሚያስረዳ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ሰማያዊ የሆነ ታላቅ መንፈሳዊ ጸጋና ምስጢር ስለሆነ ትርጓሜው የሚፈታው በራሱ ማለትም የራዕዩ ገላጭ በሆነው በእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ መሪነት ብቻ ነው። /ማቴ. 16፥16 1ቆሮ. 2፥10-14 ቆላ. 4፥3 2ጴጥ. 1፥20/

ይህን የቅዱስ ዮሐንስ ራእይ ቅዱሳን የቤተክርስቲያናችን አባቶች በመንፈስ ቅዱስ ምሥጢር ገላጭነት ተመርተው እጅግ በሚያስደንቅ መንፈሳዊ ምሥጢር ተርጉመውታል። የ666ትን ምስጢራዊ ፍቺ የዚህ ዓለም ጠበብቶች (scholars) በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚመለከቱትና ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ደግሞ እንዴት በምሥጢር አራቅቃና ተርጉማ እንደምታስተምር ከዚህ ቀጥለን እንመለከታለን።



የዚህ ዓለም ጠበብቶች <u>"የአውሬው መለያ ቁጥር ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው"</u> የሚለውን በመያዝ ይህ ታላቅ የባሕር አውሬ የዘመናችን የቴክኖሎጂ ውጤት የሆነው ኮምፒዩተር /computer/ ነው የሚል አመለካከት አላቸው። እነዚህ የኮምፒዩተር ሰዎች ለዚህ የተሳሳተ አመለካከታቸው እንደማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ነገር አለ። ይኸውም ከA-Z /ከኤ-ዜድ/ ያሉትን የእንግሊዝኛ ፊደላትን /Alphabet/ ይጽፉና ለA-1፤ ለB-2፤ ለC-3፤... ለZ-26 ተራ ቁጥሮችን ይሰጣሉ። ከዚህም እያንዳንዱ በ6 ያበዙታል። ከዚህ በኋላ በእንግሊዝኛው ፊደል ኮምፒዩተር /COMPUTER/ ብለው ይጽፉና ከሊስቱ ውስጥ የእያንዳንዱን ፊደል ቁጥር በማውጣት ሲደምሩት ውጤቱ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት /666/ ይሆናል። ይህም የመጭው አውሬ የመለያ ቁጥሩ ማለት ነው። ስሌቱን ከዚህ እንደሚከተለው እንገልጻለን።

A. 1X6=6

B. 2X6=12

C. 3X6=18

D. 4X6=24

E. 5X6=30

F. 6X6=36

G. 7X6=42

H. 8X6=48

I. 9X6=54

J. 10X6=60

K. 11X6=66

L. 12X6=72

M. 13X6=78

N. 14X6=84

O. 15X6=90

P. 16X6=96

Q. 17X6=102

R. 18X6=180

S. 19X6=114



T. 20X6=120

U. 21X6=126

V. 22X6=132

W. 23X6=138

X. 24X6=144

Y. 25X6=150

Z. 26X6=156

ኮመፒዩተር /COMPPUTER/ የሚለው ቃል በእንጊሊዘኛው ስምንት ፊደላት አሉት። ከላይ እንደተመለከትነው እያንዳንዱ ፊደል የያዘውን ቁጥር አውጥተን ስንደምር 666 ይሆናል።

C- 18

O- 90

M- 78

P- 96

U-126

T- 120

E- 30

R- 108

666

ይህን የሒሳብ አቀማመር መሠረት በማድረግ የዚህ ዓለም ጠበብቶች መጭው አውሬ ኮምፒዩተር ነው የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሰዋል። ዳሩ ግን በዮሐንስ ራእይ ምዕ. 13÷1 ላይ የተጠቀሰው የባሕር አውሬ በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ኮምፒተር አይደለም ሊሆንም አይችልም። በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ መጭው አውሬ ኮምፒተር ሳይሆን የዕለተ አርብ ፍጥረት የሆነና ቁመቱም ሦስት ክንድ ከስንዝር የሆነው ሰው ነው። /2ኛ ተሰ. 2÷1-5 ራእይ 13÷18/

"በ2ኛ ተሰ. 2÷1-5 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደገለጸው በተሰሎንቄ ከተማ ስለዳግም ምጽአት ያልሆነና የተሳሳተ ነገር ይወራ ስለነበር በወቅቱ ለነበሩት ክርስቲያኖች የማጽናኛ መልዕክቱን ሲጽፍ "የአመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ" የተባለው አውሬ /ሐሳዊ መሲሕ/ ሳይገለጥ ክርስቶስ



ዳግም አይመጣም በማለት ሰብአዊ ፍጡር መሆኑን ገልጸአል። በዚህም ይህ በራእይ. 13 ላይ አውሬ የተባለው ሰው የሚሠራውና የሚያዘው የሰው የሥራ ውጤት የሆነው ኮምፒዩተር እንዳልሆነ በግልጽ አስረድቷል።

በራእይ 13÷18 ላይ ደግሞ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሲጽፍ "አእምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና ቁጥሩም ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው።" ብሏል። ይህም ማለት ብልሀና አዋቂ አስተዋይም የሆነ ዕውቀት ያለው የሐሳዊ መሲሕን መጠኑን ያውቃል። በሰው ልክ መጠን ሦስት ክንድ ከስንዝር ቁመት ያለው ነው። ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት አሥራው /ጅማቶች/ ያሉት የዕለተ አርብ ፍጥረት /ሰብአዊ ፍጡር/ ነው ማለት ነው። በሃይማኖት አባቶች ትምህርት የማንኛውም ሰው ጅማት /ሥር/ 666 ነው። ይህንንም አክሲማሮስ የተባለው የቤተክርስቲያናችን የሥነፍጥረት መጽሐፍ ያስረዳል። ስለዚህ ይህ አውሬ ተብሎ የተጠቀሰው ሐሳዊ መሲሕም ከሰው ወገን የሆነ በዕለተ አርብ የተፈጠረ የአዳም ወገን እንጂ ሌላ ፍጥረት አለመሆኑን ሐዋርያው ቅዱስ

ዮሐንስ ሲገልጽ <u>“ቁጥሩም የሰው ቁጥር ነው”</u> አለ። ከዚህ የምንረዳው መጭው አውሬ /ሐሳዊ መሲሕ/ ኮምፒዩተር ሳይሆን ሰው መሆኑን ነው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ. 8÷47 ላይ “ከእግዚአብሔር የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል።” እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜውንና ምስጢሩን እንመለከታለን። በራእይ 13+1 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ “አንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፤ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሰሶቹም ላይ የስድብ ስም ነበረ።” ይላል።

***<u>የስሙም የቁጥር ቀመር በሊታውንት አነጋገር እንዲህ ነው</u>***

መ = ሚም = 40
ር = ሬስ = 200
ም = ሚም = 40
ያ = ዮድ = 10
ዎ = ዋው = 6
ዖ = ኤ = 70
ስ = ሳን = <u>300</u>
<u>666</u> ይሆናል።



ይህንን የስሌት ቀመር አመሳጥረው ያዘጋጁ መተኪያ የሌላቸው የቤተክርስቲያናችን ማለትም የኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብርቅዬ የሃይማኖት ሊቃውንት (ልጆች) ናቸው።

## *<u>ባሕር የተባለች ማን ናት? አሥር ቀንዶች የተባሉት ምንድን ናቸው? ሰባት ራሶች የተባሉትስ እነማን ናቸው? ዘንዶውስ ማነው?</u>*

<u>ባሕር</u>:-የተባለችው ይህች ተለዋዋጭና ብልጭልጭ ዓለም ናት። በህባሕር ውስጥ የተለያዩ ፍጥረታት /የውኃ ውስጥ አውሬዎች/ አሣ፣ ጉማሬ፣ አዞ፤ አሳ አንበሪ የመሳሰሉት ይኖራሉ። በምድር ላይም በተፈጥሮአቸው ሰብአዊ ሆነው በግብራቸው / በስራቸው/ ደግሞ የተለያዩ ሰዎች ይኖሩባታል። በቅድስና የሚኖሩ እንዳሉ ሁሉ በርኩሰትም የሚኖሩ አሉ። እንዲሁም በባሕር ውስጥ ደጋግ ፍጥረታት እንዳሉ ሁሉ በምድርም ላይ ደጋግ ሰዎች አሉ። ታዲያ ባሕር ከማለት መሬት ማለት አይቀለውምን? ቢሉ ባሕር የረጋ አይደለም፣ መሬትም በጦርነት፣ በስደት፣ በረሃብ ስትታወክ የምትኖር ስለሆነ የረጋች አይደለችም። በመሆኑም <u>“አውሬው ከባሕር ወጣ”</u> ሲል <u>አውሬ</u> የተባለው <u>ሐሳዊ መሲሕ</u> ነው። <u>“ከባሕር ወጣ”</u> ማለቱ ደግሞ የሐሳዊ መሲሕ ሥልጣኑ በመጀመሪያ አካባቢ የተረጋጋና የተደላደለ

እንደማይሆን መግለጡ ነው። ስለ ክፉ ሥራው (ግብሩም) አውሬ ብሎታል።

## አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች የተባሉትስ ምንድን ናቸው?

አሥር ቀንዶች፡- እዚህ ላይ ቀንድ ሲባል ቀንድ አይደለም። ምክንያቱም አውሬ የተባለው በቁሙ አውሬ ሳይሆን ሰው ነው ብለውናልና። ቀንድ የሚያገለግለው ጠላትን ለመውጋት ነው የሚበቅለውም ከጊዜ በኋላ ነው። እንዲሁም ይህ መሳቲ ከጊዜ በኋላ መንግሥቱን ሲያደላድል በሥሩ የሚሾማቸው ባለሥልጣናት ናቸው አሥር ቀንዶች የተባሉት። እነርሱም እንደ ቀንድ የእርሱን ተቃዋሚዎች እየወጉ ይጥላሉ። የሚታዘዙትና የሚያገለግሉትም እርሱን ብቻ ነው።

ሰባት ራሶች፡- የሚለው ገጸ-ንባብ ደግሞ ሁለት ትርጓሜና ፍቺ አለው። እነዚህም፡-



1ኛ/ ሰባት ራሶች፡- የተባሉት የአውሬው /የሐሳዊ መሲሕ/ ዋና ተገዢ የሚሆኑ ሰባት ሀገሮች ናቸው። እነርሱም ፋርስ፣ ባቢሎን፣ ግሪክ፣ ሜዶን፣ ግብጽ፣ ሮምና ኢየሩሳሌም ናቸው። እነዚህም ሰባት ሀገሮች ሀሳዊ መሲህ ቁጥጥር ስር የሚሆኑና መላውን ዓለም በክህደት ትምህርትና በታላላቅ ምትሀታዊ ተአምራት የሚያስቱና የሚያናውጡ ናቸው።

2ኛ/ ሰባት ራሶች፡- የተባሉት በእነርሱ ማለትም በሐሳዊ መሲሑ ዘመን የሚፈጸሙ ሰባቱ ዋና ዋና ኃጢአቶች ናቸው። እነዚህም ሰባቱ አርዕስተ ኃጣውዕ /የኃጢአት ራሶች/ በመባል ይታወቃሉ።

እነርሱም፡-

1/ ኃጢአተ አዳም (የአዳም ሐጢአት)

2/ ቅትለተ አቤል (የአቤል መግደል)

3/ ጥቅመ ሰናኦር (የሠናዖር ህንፃ)

4/ ኃጢአተ ሰዶም (የሰዶምና የገሞራ ሰዎችሐጢአት)

5/ ኃጢአተ እስራኤል (የእስራኤላውያን ሐጢአት)

6/ ቅትለተ ዘካርያስ ካህን (የዘካርያስ ካህን መገደል)

7/ ሞተ ወልደ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት)ናቸው።

1ኛ/ <u>ኃጢአተ አዳም፡-</u> ማለት የአዳም ኃጢአት ማለት ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም አምላክነትንና ፈጣሪነትን ስለፈለገና <u>ስለተመኘ አትብላ የሰባለውን ዕፀ</u> በለስን በላ። በዚህም ከፈጣሪው ጋር ተጣልቶ ከክብር ቦታ ከገነት ተባርሮ ወጣ። አሁንም በዚህ በመጨረሻው ዘመን የሚነሳው ይህ ሐሳዊ መሲሕ እኔ አምላክ ነኝ፣ ፈጣሪ ነኝ ለእኔ ስገዱ እያለ ይመጣል። በሞተ ወልደ እግዚአብሔር ተደምስሳ የነበረችውም የአዳም ኃጢአት /አምላክነትን መሻት/ በዚህ በሐሳዊ መሲሕ



ዘመን እደላ ትፈጸማለች ማለት ነው። /ዘፍ. 3÷1-24 2ኛ ተሰ. 2÷3-4/

2ኛ/ <u>ቅትለተ አቤል፡-</u> ማለት የአቤል መገደል፣ መሞት ማለት ነው። አቤልና ቃየል የአአዳምና የሔዋን ልጆች ናቸው። ዘፍ. 4÷1-12 ቃየን ከአንድ ማኅፀን የወጣውን የገዛ ወንድሙን በግፍና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ገድሎታል። አሁንም በዚህ በአውሬው /በሐሳዊ መሲሕ/ ዘመን መገዳደል እጅግ ይበዛል፣ ርኀራኄ ከሰው ልጆች ዘንድ ትርቃለች፣ ወንድም ወንድሙን ይገድላል፣ እኅት እኅቷን ትገድላለች ማለት ነው። /ማቴ. 10÷21-36/

3ኛ/ <u>ጥቅመ ሰናአር</u>፡- ጥቅመ ሰናአር ማለት የሰናአር ሕንፃ /ግንብ/ ማለት ነው። ባቢሎናውያን በአንድ ወቅት ሰይጣን በልባቸው አድሮ፣ አይነልቡናቸውን በትዕቢት አሳውሮ፣ የማይታየውን ረቂቁን አምላክ እናየዋለን፣ የማይዳሰሰውንና የማይጨበጠውን እሳተ መለኮት የሆነውን አምላክ እንዳስሰዋለን፣ እንጨብጠዋለን፣ በጦር ወግተን ከዙፋኑ

እናወርደዋለን በማለት በእግዚአብሔር ላይ በትዕቢት ተነሳስተው ግንብ መገንባት ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ልዩ ሦስት የሆነ ጌታ እግዚአብሔር "ንዑ ንረድ ወንከአው ነገሮሙ ለከለዳውያን" ማለትም "ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው" አሉ።*(1) ዘፍ. 11÷7/ ወዲያውኑም ቋንቋቸው ተደበላለቀባቸው። ድንጋይ አቀብለኝ ሲለው ውኃ፣ ውኃ አቀንለኝ ሲለው ደግሞ እንጨት ያቀብለው ጀመር። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ቋንቋቸው ተደበላልቆባቸዋል። እግዚእብሔርም በትዕቢታቸው ምክንያት በተናቸው። /መዝ. 2÷5/

አሁንም በዚህ በሐሳዊ መሲሑ ዘመን ከዚህ እጅግ በረቀቀ ሁኔታ ቴክኖሎጂው ይራቀቃል፣ ይሰለጥናል። ሰዎችም እጅግ ኮምፒዩተራይዝድ /COMPUTERIZED/

---

*(1) ባቢሎናውያን ታላላቅ ህንፃዎችን ያንፁ የነበሩበት ዋናው ምክንያት በጥፋት ውሃ በኖህ ዘመን ብዙዎች ስለጠፉ እነርሱ የጥፋት ውሃ ዳግመኛ ቢመጣ ለመዳንና ለመትረፍ ነበር። ነገር ግን በሃጢአት ከሚመጣ ቅጣት ግንብ በመገንባት ማምለጥ አይቻልምና ልዩ ሦስት የሆነ ጌታ በመዓት ቀጣቸው። ብሂለ ሊቃውንት



በሆኑ መሣሪያዎች እግዚአብሔር ያለበትን ቦታ ለማግኘት ከጨረቃ አልፈው ይመጥቃሉ፤ እግዚአብሔርን ግን አያገኙትም፣ አያዩትም። እርሱ ግን ባለበት ቦታ ሆኖ ያያቸዋል፣ ይሳለቅባቻዋል፣ በመአትም ያውካቸዋል። /መዝ. 2÷4-5 ት. አብድዩ 11÷1-4/ በዚህን ጊዜ ሐሳዊ መሲሕ እግዚአብሔር የት አለ? አምላክ፣ ፈጣሪ እኔ ነኝ ይላል። ለዚሀም ሙት ያስነሳል፣ እሳት ከሰማይ ያወርዳል፣ ታላላቅና ድንቅ ድንቅ ተአምራትን ያሳያል። ፀሐይና ጨረቃን በእጁ የያዘ አስመስሎ በምትሐታዊ ተአምር ያሳያል። በዚህም እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እያስነገረ በቤተ መቅደስ ይቀመጣል *(2) በዚህን ጊዜ መላው አለም አውሬውን ማን ያሀለዋል? ማንስ ይመስለዋል? እያለ ይከተለዋል። ይሰግድለታል። /ማቴ. 24÷23-27 2ኛ ተሰ. 2÷4 ራዕይ 13÷4።/

4ኛ/ <u>ኃጢአተ ሰዶም፡-</u> ይህ ኃጢአተ ሰዶም ተብሎ የሚጠራው በሎጥ ዘመን በሰዶምና በገሞራ

---

*(2) ካህናትን ሳይቀር ያስታቸዋል ማለት እንጂ በቤተ መቅደስ ይቀመጣል ማለት አይደለም።

የተፈጸመው የኃጢአት ሥራ ነው። ሰዶምና ገሞራ በአንድ ወቅት ትዕዛዝ እግዚአብሔርን አፍርሰው ሕጉንም ተላልፈው ለባሕርያቸው የማይስማማውንና የማይገባውን እንስሳዊ ግብር በመፈጸማቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ከሰማይ እሳትና ዲን አዝንቦባቸዋል። /ዘፍ. 19÷24 መዝ. 48÷12 ሉቃ. 17÷28-30 2ኛ ጴጥ. 2-6-8 ሮሜ 1÷22-32/

ይህ ግብረ ሰዶም /HOMO SEXUALITY/ በአሁኑ ጊዜ በመላው ዓለም ላይ እንደሰደድ እሳት እየተቀጣጠለ ነው። በተለይም በሰለጠነው ዓለም ይህ ግብረ ሰዶም /Homo Sexuality/ ሕጋዊ እንዲሆን የሚጠይቁ ብዙ ሰላማዊ ሰልፎች ተደርገዋል።*(3) በብዙዎችም ዘንድ ተቀባይነትን እያገኘ ነው ይህ ሁሉ የሚያስረዳን በዚህ በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ይህ ዓይነቱ የግብረ ሰዶም ኃጢአት በገሀድ እንደሚፈጸም ነው። /ማቴ. 24÷15።/

---

*(3) ይልቁንም የዚህ ጉዳይ ዋነኛ አቀንቃኞች ፕሮቴስታንቶች ናቸው። ለዚህም በሃራሬ ዚንባቡዌ የተካሄደው የአለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ምስክር ነው።



5ኛ/ <u>ኃጢአተ እስራኤል</u>:- እስራኤል ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቡም ሕዝበ እግዚአብሔር ይባሉ እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሁላችንም የምናውቀው ነው። እስራኤላውያን ግን በዚያንጊዜ የአባቶቻቸውን አምላክ የእስራኤልን ቅዱስ እግዘኤብሔርን ትተውና ረስተው ሕጉንም ተላልፈው በአሕዛብ ጣኦታት ያመልኩና ለጣኦታቱም ይሰግዱ ነበር። እንደዚሁም ሁሉ በዚህ በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ብዙ ሰዎች ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወጥተውና ተለይተው ወደተለያየ አምልኮተ ጣኦት ይገባሉ። የአውሬው /የሐሳዊ መሲሑ/ ስምና መንፈስ፤ መለያ ቁጥሩም ለሆነው "666" ላለበት ጣኦት ይሰግዳሉ። /ራእይ 13÷15።/

6ኛ/ <u>ቅትለተ ዘካርያስ:-</u> ይህ ማለት የካህኑ የዘካርያስ መሞት፣መገደል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ካህን የነበረው ዘካርያስ የተገደለው በተልዕኮ ላይ እያለ በቤተመቅደስ ውስጥ በመሠዊያው አጠገብ ነበር። እርሱም የሞተው ጥፋት ኖሮበት ሳይሆን በግፍ ነው። እንደዚሁም ሁሉ አዕይንተ እግዘአብሔር

የተባሉ ካህናት በሐሳዊ መሲሕ ጊዜ አገልግሎታቸው ለእውነተኛው አምላክ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኑ መከራ ይደርስባቸዋል፤ በአገልግሎት ላይ እንዳሉም ይገደላሉ። ስለዚህ ይህ የሚያመለክተው የቅዱሳን ካህናትን መከራ መቀበልና በሰማዕትነት ማለፍ ሲሆን እነ ሄኖክና ኤልያስ ሌሎችም የተሰወሩ ቅዱሳን ወደዚህ ዓለም ተመልሰው መጥተው በዚህ አውሬ /ሐሳዊ መሲሕ/ ዘመን በሰማዕትነት ያርፋሉ።

ት.ሚልክ. 4÷5, ማቴ. 23÷34-36, ራእይ 11÷3-13

7ኛ/ <u>ሞተ ወልደ እግዚአብሄር:-</u> ንጹሕና ቅዱስ የሆነው የእግዚብሔር አብ የባሕርይ ልጅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተው ስለ ሰው ልጆች ፍቅርና ህይወት እንጂ አንዳች በደል ኖሮበት አይደለም። ንጹሐ ባሕርይ አምላክ ሆኖ ሳለ እውነተኛ ፍርድ ስለጠፋ ነው በቅንአተ አይሁድ የሞተው፤ እንደዚሁም በዚህ በሐሳዊ መሲሕ ዘመን እውነተኛ ፍርድ ትጠፋለች፣ ፍትሕ ትጓደላለች፣ ክርስቲያኖች ያለአግባብ ይታሰራሉ፣ ይሰቃያሉ፣ ይገደላሉ ማለት ነው። /ዮሐ 15÷18-20 ማቴ. 10÷16-20።/



ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በዚህ ሁኔታ ከጻፈ በኋላ እነዚህ ሰባቱ ዋና ዋና ኃጢአቶች በዚህ በሐሳዊ መሲሕ ዘመን ከበፊቱ ይልቅ አይለውና ገነው ስለሚፈጸሙ ሰባት ራሶች ብሏቸዋል። ከዚህ በኋላ ደግሞ:-

"ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው" ይላል። /ራዕይ 13÷2።/

## <u>*ዘንዶ የተባለው ማነው?*</u>

የዘንዶውን ማንነት ለማወቅና ለመረዳት ደግሞ ወደ ራእይ 12÷3,7-9 እንመለሳለን። በዚህ በራእይ 12÷3 ላይ "ታላቅ ቀይ ዘንዶ" በማለት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ስለዘንዶው ማንነት ይናገራል። ይህም ዘንዶ የተባለው አባታችንን አዳምና እናታችንን ሔዋንን ያሳተው ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው። /ዘፍ. 3÷18።/

"ታላቅ" መባሉ የቀድሞ ተፈጥሮውንና ክብሩን ለመግለጽ ነው፤ የመላእክት ሁሉ አለቃ ነበርና። "ቀይ" ያለበት ምክንያት ደግሞ ተፈጥሮው እንደሌሎቹ ብርሃናውያንና እሳታውያን ቅዱሳን መላእክት ከእሳትና

ከነፋስ ስለሆነ ነው። /መዝ. 103÷4 ዕብ. 1÷7 ሕዝ. 28÷14 ኢሣ. 14÷12 ።/

## ምድር ሁሉ አውሬን ይከተላል

/ራዕይ. 13÷4/

መላው ዓለም በአውሬው የተመሰለው ይህ ሐሳዊ መሲሕ በሚያደርገው ምትሐታዊ ተአምር ይሳባል፣ ይደነቃል "እውነተኛ አምላክ ነው" እያለም ይከተለዋል ማለት ነው። በምትሀታዊ ተአምራቱ ህዝቡን ሁሉ ያስገርም ዘንድ ሥልጣን ለሰጠው ለዘንዶውም ይሰግዱለታል፣ ይገዙለታል። አውሬውን "ማን ይመስላዋል? ማንስ ይስተካለዋል? ብቸኛ ገናና አምላክ ነው" ብለው ያመልኩታል ማለት ነው። /ዘዳ. 13÷1-8 ማቴ. 12÷38-39/

## አውሬው ተሳዳቢ ነው

/ራዕይ. 13÷5-7/



"አውሬው ታላቅንም ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፤ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሰራ ሥልጣን ተሰጠው" ይላል። /ራእይ 13÷5።/

ይህ አውሬ /ሐሳዊ መሲሕ/ በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ይሰድባል። እግዚአብሔር ማን ነው? የትስ አለ? እግዚአብሔር እኔ ነኝ፤ አምላክም እኔ ነኝ ይላል። እውነተኛውን አምላክ ሰዎች እንዳይረዱትና እንዳያመልኩት እርኩስ መንፈስ በልባቸው እያሳደረ ያስታል። ዛሬም ቢሆን ክብር ምስጋና ይግባውና ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን "ፍጡር፣ አማላጅ" የሚሉ አሉ። እነዚህ ለአውሬው ጥርጊያ መንገድ የሚያዘጋጁ ናቸው። ምክንያቱም በዮሐ. 1÷1,14 ላይ " በመጀመሪያ ቃል ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ። ቃልም እግዚአብሐር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሰው ሆነ።"*(4) ተብሎ የተነገረለትን እግዚአብሔር ወልድን ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ለይቶና አሳንሶ ፍጡር

---

*(4) 2ኛ ዮሐ. 1÷9-11 "ለሚመጣው ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው እምላክ የለውም በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት"

አማላጅ ማለት ይህ እግዚአብሔርን መሳደብ ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለምና፤ ተማላጅ እንጂ አማላጅ አይደለምና። ኢሳ. 48÷12-16 1ኛ ዮሐ.3÷7 1ጢሞ. 3÷15-16 ዮሐ. 1÷1-3,14 ኤፌ. 2÷10 ሚል. 2÷10 እብ. 13÷8 መዝ. 2÷8 መዝ. 109÷3 እብ. 1÷5 ማቴ. 16÷13-17 ዮሐ. 20÷28 ማቴ. 3÷17 ማቴ. 17÷5 ዮሐ. 9÷35-38 ራእይ. 1÷17-18 ሮሜ. 9÷5 ኢሳ. 9÷6 1ኛ ዮሐ. 5÷20 ፊሊጵ. 2÷10 ኢሳ. 45÷20-22 ሉቃ. 2÷11 ዮሐ. 4÷42 ሆሴ 13÷4 የሐዋ. 4÷12 ቲቶ. 1÷3 ቲቶ. 2÷12-13 መዝ. 77÷67 ማቴ. 28÷5-10 ሉቃ. 24÷5 መዝ. 46÷5- ሉቃ. 24÷51 የሐዋ. 1÷9 መዝ. 49÷1-4 ኢሳ. 40÷10 ዘካ. 14÷5 የሐዋ. 1÷11 1ኛ ተሰሎ. 3÷12 ራዕ. 22÷12 2ኛ ዮሐ 1÷9/

አውሬው /ሐሳዊ መሲሕ/ ስድቡን በዚህ ብቻ አያበቃም አርባ ሁለት ወር ሙሉ የወደደውን ምትሐታዊ ተአምር እየሰራ ራሱን ብቻ ከፍ በማድርግ የእግዚአብሔርን ማደሪያ ይሳደባል። ይላል ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ /ራእይ 13÷6።/



## የእግዚአብሔር ማደሪያ ማን ናት?

1ኛ. እግዚአብሄር ማደሪያው ትሆን ዘንድ ከአንስተ ዓለም መርጦ የቀደሳትና ለተዋሕዶ የመረጣት እመቤታችን ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። /መዝ. 131÷13/ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣትን የአማላጅነት ክብር፣ የአምላክ እናት መሆኗንና ዘለዓለማዊ ድንግልናዋን መጠራጠርና መካድ ይህ የእግዚአብሔርን ማደሪያ መሳደብ ነው። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ግን <u>"ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ።"</u> በማለት ክብሯን እና ልዕልናዋን ተናግሮላታል። <u>ልዑል</u> የተባለው እግዚአብሔር ሲሆን ማደሪያው የተባለችው ደግሞ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናትና። መዝ. 45÷4።[(5)]

2ኛ. የእግዚአብሔር ማደሪያ የተባለችው እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በገዛ ደሙ የዋጃት፣ ቅዱስ ስሙ የሚጠራባት፣ የሚቀደስባትና የሚሠለስባት፣ ቅዱስ ሥጋውና

---

(5) "ማዕምንት ሠዓሊተ ምህረት ለውሉደ ሰብዕ" እንዳለ ቅዱስ ኤፍሬም

ክቡር ደሙ የሚፈተትባት ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። /የሐዋ. 20÷20 ማቴ. 21÷13 ሉቃ. 2÷49 የሐዋ. 5÷20።/

በዘመናችን የእግዚአብሄር ማደሪያ የሆነችውን ቅድስት ቤተክርስቲያንን የሚነቅፉና የሚያቃልሉ አሉ። እንዲህም በማድረግ ለአውሬው መንገድ እየጠረጉለት ነው።

3ኛ. ሌላው የእግዚአብሔር ማደሪያ የተባለው ታቦተ ሕጉ ነው። የታቦት ትርጓሜው ማደሪያ፣ መታያ፣ መገለጫ ማለት ነው። ንጉሥ በዙፋኑ እነዲገኝ እንዲገለጥ ታቦትም የእስራኤል አምላክ መገለጫ ነውና። ይልቁንም ቃሉንና ሕጉን የያዘው የፅላት ማደሪያ ነውና። /ዘጸ.34÷12-18 ዘጸ. 25÷8-22 ዘጸ.27÷20-21 ዘጸ.31÷1-7,8 ዘጸ.32÷15-16 ዘጸ.33÷7-11 ዘጸ.34÷1-5,29 ዘጸ.40÷20-21 ዘዳ.9÷9-11/ በአጠቃላይ አነጋገር ታቦት በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ለምሕረት ለሕዝቡ በሚገለጥበት ጊዜ ዙፋኑ ነው። በዘመነ ሐዲስ ደግሞ ታቦተ ሕጉ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ ማክበሪያ (መሰዊያው) ነው። በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን እምነት መሠረት በአዲስ ኪዳን የታቦቱና የጽላቱ ዋና አገልክግሎት የቅዱስ ቁርባን የክብር ዙፋን ነው።



በቅዳሴ ጊዜ ካህኑ ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ኅብስቱን ሥጋ መለኮት ወይኑን ደመ መለኮት ወደመሆን የሚለውጠው በዚህ በታቦቱ ላይ ነው። የደብተራ ኦሪት ጽላት እግዚአብሔር በደመና ተሰውሮ መሴንና አሮንን የሚያነጋግርበት ለእስራኤል ብቻ በረድኤት የሚገለጥበት ዙፋን ነበር። ይህ ግን የአምላክ ሥጋና ደም የሚፈተትበት የምሕረት ምስዋዕ ነው። /ዘዳ. 10÷1-5 ኢያሱ 3÷13-17 6+12-21 1ሳሙ. 5÷1-12 2ሳሙ. 6÷1-12 1ዜና. 13÷1-14 1ዜና. 15÷1-2 የሐዋ. 7÷35-46 2ቆሮ. 6÷14-18 ዕብ. 9÷1-9 ራእይ 11÷19/ በታቦተ ሕጉ ላይ የተጻፈውም ቃል "አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው የዘላለም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚል ነው። /ዘጸ. 3÷14 ራእይ 1÷8 22÷13/ የእግዚአብሔር ቃል "ከሰማይና በምድርም በታች ያለ ጉልበት <u>ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሥም ይንበርከክ።</u>" /ኢሳ. 45÷23 ፊልጵ. 2÷10/ እንዳለ በታቦተ ሕጉ ፊት የምንሰግደውም ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስም ነው። /ኢሳ. 9÷6 ሉቃ. 1÷49-

50, ዘጸ. 33÷7-11, መዝ. 5÷7 131÷7, 137÷2 ኢያሱ. 7÷6, ዮሐ. 4÷24/

አውሬው የሚቀረው የለም በሰማይ የሚያድሩትን ቅዱሳን ሁሉ ማለትም ቅዱሳን መላእክትትን፣ ነቢያትን፣ ሐዋርያትን፣ ፃድቃንንና ሰማዕታትን ይሰድባል። ዛሬም አንዳንዶች በሰማይ የሚያድሩትን የእግዚአብሔርን ባለሟሎች ቅዱሳን መላእክትና ጻደቃን ሰማዕታትን ሲሰድቡ ይሰማሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ቅዱሳን በሙሉ በምዕመናን ዘንድ እስከዘለዓለም ድረስ ሲታሰቡ እንደሚኖሩ መታሰቢያቸውም እንደማይጠፋ መታሰቢያቸውንም በማድረግ በረከት እንደሚገኝ በሚገባ ያስረዳናል። /መዝ. 111÷6 ምሳ. 10÷7 ኢሳ. 56÷4-7 ማቴ. 10÷40-42።/

እንግዲህ ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ መጠራጠርና መካድ፣ የእግዚአብሔርንም ቅዱሳን መሳደብ የአውሬው ተግባር መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። /ዘዳ. 12÷1-15 2ነገሥ. 2÷23-25 መዝ. 30÷18 መዝ. 104÷14-15 ማቴ. 12÷34-37/ ስለሆነም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 24 ላይ የሰው ልጅ ዳግም በክብሩ ሲመጣ



ከሰው ልጆች በእምነት የጸና ያገኝ ይሆንን? ብሎ የተናገረውን ኃይለ ቃል ሁል ጊዜ በማስተዋል ከእምነታችን እንዳንናወጥ መጠንቀቅ አለብን። /ሉቃ. 18÷8 1ቆሮ. 10÷12 2ቆሮ. 13÷5 ዕብ. 3÷12/

ዛሬ እኛ የምንጨነቅላትና የምንጓጓላት ይህቺ ከንቱ ዓለም ነገ እንደወረቀት ተጠቅልላ ታልፋለች። ኃላፊና ጠፊ ከንቱ መሆኗን አውቀውና ተረድተው እንደመርገም ጨርቅ ጥለዋት፣ በሃይማኖታቸው እስከመጨረሻው ድረስ ጸንተው አምላካቸውን መስለው የኖሩ ሁሉ ግን በመጨረሻው ጊዜ በሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም /በመንግሥተ ሰማያት/ ለዘላለም ብርሃን ለብሰው ብርሃንን ተጎናጽፈው በደስታ ይኖራሉ። /ማቴ. 13÷43 ማቴ. 24÷13 ሉቃ. 10÷41-42 1ኛ ዮሐ. 2÷17 ራእይ 2÷10 2ኛ ጴጥ. 3÷4-13 ራእይ 21÷14።/

ስለዚህ ሁላችንም ከዛሬ ጀምረን የእግዚአብሔርን መንግሥቱንና ጽድቁን ልንፈልግ ይህንንም ክፉ ዘመን ልንዋጅ /ልንመረምር/ ይገባል። /ሮሜ. 13÷11 ኤፌ. 5÷14-17/ የድህነት ቀን ዛሬ ነውና። /2ኛ ቆሮ. 6÷2/

## ከአውሬው ጋር ውጊያ የሚገጥሙት ቅዱሳን፡-

/ራዕይ 11÷1-13/

"ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ሐሳዊ መሲሕ በሚሰለጥንበት ዘመን ልክ ያስተምሩ ዘንድ ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በበጉ ደም የታተሙትንና ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፉትን ያጸኑ ዘንድ።" /ራእይ 11÷3።/

ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች የተባሉት ከነቢያት ኤልያስና ከአበው ደግሞ ሄኖክ ናቸው። የእግዚአብሔር ባለሟሎች የሆኑ እኒህ ሁለት መምህራን ናቸው። በትምህርታቸው የሰውን ልቡና ብሩህ ያደርጋሉና። እነርሱም እስከዛሬ ድረስ የሞትን ጽዋ ሳይቀምሱ በብሔረ ሕያዋን ያሉ ናቸው። /2ኛ ነገ. 2÷11 ዘፍ. 5÷24 ዕብ. 11÷5/ በፍጻሜው ዘመን ግን መጥተው ስለአውሬው ሐሳዊ መሲሕ መሆንና ስለታላቁ ጌታ ስለፈጣሪያችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነትና አምላክነት ይመሰክራሉ። ጠላቶቻቸውን የሚያጠፋ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ሰማዩንም ያዝዙታል። ይህም ማለት ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ ይከለክሉ ዘንድ



ሥልጣን አላቸው ማለት ነው። ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ በአክዓብና በኤልዛቤል ተቆጥቶ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀንቶ 3 ዓመት ከ6 ወር ዝናብ እንዳይዘንም ሰማዩን አዝዞት ነበርና ነው። /1ኛ ነገ. 17÷1-7 ያዕ. 5÷17።/

የሐሳዊ መሲሕንም ምትሐታዊ ተአምር በአማናዊ ተአምር ያከሽፉታል። ይህም ሊቀነቢያት ሙሴ የግብፅ ጠንቋዮችን አስማት እንዳከሸፈው ማለት ነው። ሐሳዊ መሲሕ "አምላክ አይደለም" "ሰማዩንና ምድሩን የብሱንና ባሕሩን የፈጠረ አምላክ እግዚአብሔር አለ" ብለው መስክረውና አስተምረው ከፈጸሙ በኋላ በሐሳዊ መሲሕ እጅ በሰማዕትነት ያርፋሉ። /ማቴ. 10÷32/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለባት ሀገር በኢየሩሳሌምም ሕዝብና አሕዛብ እያየው ሥጋቸው ሦስት ቀን ተኩል ተኝቶ ይታያል። የሐሳዊ መሲሕ ግብረ አበሮች በዚህ ደስ ይሰኛሉ። እርስ በርሳቸው የደስታ መግለጫ ስጦታ ይለዋወጣሉ እነዚህ ሁለቱ ወይራዎች የተባሉት ነቢዩ ኤልያስና ሄኖክ ሐሳዊ መሲሕን በመቃወም የክርስቶስ ወገኖች በእምነታቸው እንዲጸኑ በማድረጋቸውም ሥጋቸው እንዳይቀበር ሐሳዊ መሲሕ ይከለክላል። ከሦስት ቀን ተኩል በኋላም ነፍሳቸው ከእግዚአብሄር ዘንድ መጥታ

ትዋሀዳቸዋለች። ሁሉም በሚሰበሰቡበት በቀኑ እኩሌታ ወደዚህ ውጡ። የሚላቸውን ታላቅ ድምጽ ከሰማይ ይሰማሉ። ጠላቶቻቸውም እየተመለከቷቸው ወደ ሰማይ በደመና ይወጣሉ። በታላቅ ክብርም በደመና ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። በዚህም ታላቅ የምድር መናወጥ ይሆናል ከከተማይቱም አሥር እጅ ይወድቃሉ በመናወጥም ሰባት ሺህ ሰዎች ይገደላሉ። በምድርም ላይ የቀሩትንም ታላቅ ፍርሃት ይይዛቸዋል። /ራእይ 11÷7-13።/

## *ከምድር የሚወጣ ሌላ አውሬ*

/ራእይ 13÷11/

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በራእይ 13÷11 ላይ "ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ የበግ ቀንዶችም የሚመስሉ ሁለት ቀንዶች ነበሩት።" ይላል።

ይህ በግ መስሎ ይመጣል የተባለው አውሬ መንፈሳዊ መስሎ የሚመጣው ሐሳዊ ኤልያስ /ሐሰተኛው ኤልያስ/ ነው። በፍጻሜ ዘመን ኤልያስ እንደሚመጣ አስቀድሞ ስለተገለጸ ሐሳዊ መሲሁ ይህንን ምክንያት አድርጎ ለማስመሰል



የቀሩትንና በእርሱ ያላመኑትን ሌሎችን በደበልጥ ለማሳመን ሐሳዊ ኤልያስን ያዘጋጃል። /ት.ሚልክ. 4÷5።/

ከየብስ ተነሳ ማለቱ ደግሞ ሐሰተኛው ኤልያስ የሚያመጣውና የሚነሳው የፊተኛው የሐሳዊ መሲሕ ሥልጣንና መንግሥት ከተደላደለ በኋላ ስለሆነ ነው።

<u>የበግ የመሰሉ ሁለት ቀንዶች</u> አሉት የተባሉትም እርሱ አስከትሎአቸው የሚመጡት <u>ሐሰተኛ ኤልሳዕና ሐሰተኛ አብድዩ</u> ናቸው። ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ ሁለት ደቀመዛሙርት ነቢዩ ኤልያስዕና አብድዩ እንደነበሩት ማለት ነው። በግ ይመስላል ማለት ኤልያስ ነኝ ይላል ኤልያስን ለመምሰል ይሞክራል፤ /ማቴ. 7÷15 2ቆሮ. 11÷14/ በምትሐትም እሳት ከሰማይ ያወረደ አስመስሉ ያሳያል፤ ሰዎችም እውነተኛው ኤልያስ መስሎአቸው በሚከተሉት ጊዜ ሐሳዊ መሲሕ አምላክ እንደሆነ ይናገራል፤ ያስተማምናል። ምክንያቱም ነቢዩ ኤልያስ በዘመኑ ከሰማይ እሳት አውርዶ ነበርና ነው /2ኛ ነገ. 1÷9-13።/

እንግዲህ ከላይ በተገለጸው መሠረት 666 የአውሬው /የሐሳዊ መሲሕ/ የስሙ ቁጥር ነው። ስሙም መርምያዋያስ ነው። እንግዲህ 666 የሚለውን ማንተም በወዳጆቹ ቀኝ

እጅና ግምባር ላይ ያትማል ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች በአውሬው ዘንድ ባለሟልነትን ያገኛሉ። 666 የሚለውን የአውሬውን መለያ ቁጥር በእጃቸው ወይም በግምባራቸው ላይ ያላሳተሙት ግን እንዳይሸጡና እንዳይገዙ በሐሳዊ መሲሕ ይከለከላሉ /ራእይ 13÷16-17።/

## *በመጨረሻስ?*

ከዚህ ሁሉ በኋላ በእግዚአብሔር ዘንድ ቀነ ዘጠሮ የተያዘላት ዓለም ወደ ፍጻሜዋ ታመራለች ጣዕምዋ ለዛዋ ሁሉ ይሟጠጣል ፍጻሜ አለም ይሆናል። ምድር ከመሠረቷ ትናጋለች ፀሐይ ትጨልማለች፤ ከዋክብትም እንደቃሪያ ፍሬ ከሰማይ ይረገፋሉ። /መክ. 12÷2 ኢሳ. 13÷6-13 ኢዩ. 2÷10-11,30-32 ማቴ. 24÷29-31 ራእይ. 6÷12-17/ በታላላቅ ድንጋዮች የታተሙ መቃብሮች በውስጣቸው የያዙአቸውን ሙታን ይሰጣሉ የሙታን ሥጋ ከረጅም የእንቅልፍ አለም ይባንንና ሁሉም ወደ ፍርድ አደባባይ ይሰበሰባሉ ታላቁ ዘንዶ ለብዙዎች ስህተት ምክንያት የሆነው ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ለዘላለም በማይፈታ በእሳት ሰንሰለት ታስሮ ወደ ገሃነመ እሳት ይጣላል። ፊተኛው ሰማይና ምድር ከፍጡራን



ፊት እንደወረቀት ተጠቅልለው ያልፋሉ ሥፍራም አይገኝላቸውም ለዘለዓለምም ያልፋሉ። /ኢሳ. 13÷6-13 መክ. 12÷17 1ኛ ተሰ. 4÷13-18 2ኛጴጥ. 3÷10።/

በበጉ ደም የተዋጁና ሃይማኖታቸውን የጠበቁ ታማኝ የክርስቶስ ልጆች ገናናውንና ታላቁን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ሊቀበሉ በታላቅ ክብር በደመና ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። የድንግል ማርያም ልጅ የባሕርይ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስም በታላቅና እጅግ አስፈሪ በሆነ መለኮታዊ ግርማ የብዙ ብዙ በሚሆኑ እልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ይመጣል። /ዘካ. 14÷6 ማቴ. 25÷31 1ኛ ተሰ. 4÷16/ አቤት! በዚያን ጊዜ በፊቱ ችሎ የሚቆም ማን ይሆን? /ኢዩ. 2÷11/ አመጣጡም እንደቀድሞው ከሃና ወደ ቀያፋ ከዚያም ወደ ጲላጦስ አደባባይ እያንገላቱ ሲወስዱት ዝም እንዳለ ሁሉ በዚህ ዓይነት አመጣጥ አይደለም። የሚመጣው እጅግ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ መለኮታዊ ግርማ ክብር እንጂ። /መዝ. 49÷2/ መጥቶም ዝም አይልም እሳት በፊቱ ይነዳል ኃጥአንን ከፊቱ ጠራርጎ ወደ ገሃነመ እሳት የሚጨምር ጥቅል አውሎ ነፋስም አለ። /ማቴ. 24÷30 ራእይ. 1÷7/

እረኛ በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ ጻድቃንን በቀኙ ኃጥአንን በግራው ያቆማቸዋል። በቀኙ ያሉትን “ እናንተ የአባቴ ቡሩካን ወደ እኔ ኑ ወደ አባታችሁ ደስታ ወደ መንግሥተ ሰማያት ግቡ።” ብሎ ለዘለዓለም ሕይወት ይጠራቸዋል። በግራው ያሉትን ደግሞ እጅግ በሚያስፈራና በሚያስደነግጥ የቁጣ ቃል “ እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።” ይላቸዋል።*(6) ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትወርዳለች ማለት ለምዕመናን ትሰጣለች። ምዕመናንም ርስት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ ብርሃን ለብሰው ብርሃንን ተጎናጽፈው ለዘላለም በደስታ ይኖራሉ።

/ማቴ. 25÷31-46 ራእይ 21÷1-2/

ኦርቶዶክሳውያን! ነቢዩ ኤርምያስ “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደሆነች እወቁ በእርሳዋም ላይ ሂዱ ለነፍሳችሁም ዕረፍት

*(6) እሳት ይነድድ ቅድሜሁ የተባለውም ትርጉሙ ይህ ነው።



ታገኛላችሁ” /ት.ኤር. 6÷16/ በማለት እንደተናገረው በቀደመችው መልካሚቱ የሕይወትና የጽድቅ መንገድ በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ እምነታችን እስከ መጨረሻው ድርስ ጸንተን ልንኖር ይገባል። ለዚህም የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን።




*"በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጅ ይህ ነው "ማቴ 3፥17*

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፡ ባጭር ቁመት፡ በጠባብ ደረት ተወስኖ ፴ ዓመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ወንዝ፡ ሰማያዊው በመሬታዊው ዮሐንስ እጅ በትሕትና ተጠመቀ።



# <u>ክፍል ፪</u> (ሁለት)

ውድ አንባቢያን ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር ውስጥ እኒህን ሁለቱን ምስጢራት ማለትም ምስጢረ ጥምቀትንና ምስጢረ ትንሳኤ ሙታንን ብቻ ለማጻፍ የተገደድኩበት በዘመናችን የተነሱት ቢፅ ሐሳውያን የተባሉ መናፈቃን በጥምቀት ላይና በትንሳኤ ሙታን ላይ ደብልጥ በማተኮር ምዕመናን እያደናገሩ ስለሚገኙ እንዲሁም በመጸሀፍት ያልተጻፈውን እንደተጻፈ አድርገው የሐሰት መልዕክታቸውን በማስተላለፍ ስለሚገኙ ለዚህ መልስ ይሆን ዘንድ ነውና ሌሎቹን ምስጢራት እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ በሚቀጥለው እትም ለማውጣ እሞክራለሁ።

## <u>*ምሥጢረ ጥምቀት*</u>

ጥምቀት ማለት መነከር፣ መዘፈቅ፣ ውሃ ውስጥ ገብቶ መውጣት፣ መጥለቅ ማለት ነው ጥምቀት ምሥጢር መባሉ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ፀጋ ማለትም የእግዚአብሔር ልጅነትን ስለምናገኝበት ነው። በተጨማሪም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መጠመቅ በመጠመቁም

እኛ ያገኘነው ፀጋና የተደረጉት ተዓምራትን ጥምቀትን ከእምስቱ አዕማደ ምሥጢር አንዱ አድርጎታል። በሚፈፀም አገልግሎት የማይታየውን የአምላካችንን ፀጋና በረከት ስለምናገኝ ሥርዓተ ጥምቀት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ ሆኗል።

በዚህ በምሥጢረ ጥምቀት ትምህርታችን፡-

1. ስለመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት፣ ስብከትና ለጌታ የሰጠውን ምስክርነት
2. ስለጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
   ሀ. በዮሐንስ እጅ መጠመቅ
   ለ. በውሃ መጠመቅ
   ሐ. በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቅ
3. የጥምቀት ጥቅም (በጥምቀት የሚገኝ ልጅነት)
4. ምሥጢረ ጥምቀት ለመፈጸም የሚያስፈልጉን ነገሮች
5. ጥምቀት አንዲት ስለመሆኗ
6. የአንዲት ጥምቀት ክፍሎች



7. የሕፃናት ጥምቀት የሚሉትን ርዕሶች ሰፋ ያለ ትምህርት ለማየት እንሞክራለን።

## 1. *የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ስብከት እና ጥምቀት እንዲሁም ለጌታ የሰጠው ምስክርነት*

ዮሐንስ ጌታን በልደት በ6 ወር ይበልጣል። ጌታን በ6 ወር ዕድሜ የሚበልጠው ዮሐንስ ለክርስቶስ መመስከር የጀመረው ገና ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ነው። አባቱ ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ እናቱ የእመቤታችን ዘመድ ማለትም የአክስቷ ልጅ ቅድስት ኤልሳቤጥ ናቸው። እመቤታችን በብስራተ ገብርኤል በመንፈስ ቅዱስ ግብር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጸነሰች እለት ወደ ኤልሳቤጥ አገር ሄዳ ነበር። ኤልሳቤጥም በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝታ "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽ ፍሬ የተባረከ ነው የጌታዬ እናት ወደኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማህጸኔ በደስታ ዘሏልና" በማለት

እመቤታችንን አመስግና የዮሐንስንም ለጌታውና ለጌታ እናት መዝለሉን /መስገዱን/ መስክራለች የሉቃስ ወንጌል መዕራፍ 1 ከቁጥር 39-45። መጥመቀ መለኮት ዮሐንስ ያደገው በምድረ በዳ ነው።.

ጌታ ሰላሳ ዓመት ሊሞላው 6 ወር ሲቀረው ውጣና አስተምር የሚል ቃል ከእግዚአብሔር መጣለት። ዮሐንስም ከምድረበዳ ወደ ዮርዳኖስ ዙሪያ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሀ ግቡ" እያለ እየሰበከ መጣ በነብዩ በኢሳያስ እንደተነገረ ትንቢትም የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና ሰር ጓጉጡም ሜዳ ይሁን እያለ የሰዎችን ልብ ለእግዚአብሔር መንግሥት ያዘጋጅ ጀመር ኢሳ. 40÷3-5 ማቴ 3÷1 ሉቃ 3÷2-17 ማር 1÷1 ዮሐንስ ልብሱ የግመል ፀጉር ነበር በወገቡ ጠፍር ይታወቅ ነበር። ምግቡም አንበጣና የበረሃ ማር ነበር። ዮሐንስ የሚናገረው እውነት ነው ኃጢያተኞች ወደ ንስሐ እንዲመጡ አጥብቆ ይመክራል ሰዎች ወደ እርሱ እየመጡ ኃጢያታቸውን እየተናዘዙ ይጠመቁ ነበር። በልባቸው ትዕቢትና ተንኮል የተሞላባቸው



ሰዱቃውያና ፈሪሳውያን ወደ እርሱ ሲመጡ "እናንተ የእፉኝ ት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ" እያለ በመገሰፅ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ እንዲያፈሩ ከመልካም ግብር የተለዩ ሆነው ከተገኙ እንደሚቆረጡ ወደገሃነመ እሳትም እንደሚጣሉ አበክሮ ይናገር ነበር። ዮሐንስ ወንጌላዊው ስለ መጥምቁ ዮሐንስ ሲጽፍ "አይሁድም አንተ ማነህ ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ የዮሐንስ ምሥክርነት ይህ ነው መሰከረም አልካደም እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ እንግዲያስ ማነህ ለላኩን መልስ እንሰጥ ዘንድ ስለ ራስህ ምን ትላለህ አሉት እርሱም ነብዩ ኢሳያስ እንዳለ የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምጽ እኔ ነኝ አለ። እኒህ መልእክተኞች ለምን እንደሚያጠምቅ ሲጠይቁት ዮሐ 1÷19-34 "እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ብሎ የሱ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት መሆኑን ገልጿል። ከዮሐንስ በኋላ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት የንስሐ ጥምቀት ያጠምቁ ነበር። ክርስቶስም ሲመሰክር "እናንተ የማታውቁት ከመካከላችሁ ቆሟል ተነንብሼ የጫማውን ጠፈር ልፈታ የማይገባኝ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ

ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው። እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል መንሹ በእጁ ነው አውድማውንም ያጠራል ስንዴውንም በጎተራ ይከታል ገለባውንም በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል ይል ነበር። ዮሐ. 4÷2-3

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ማጥመቅ በጀመረ በ6ኛው ወር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ። ዮሐንስም ጌታን ሲያየው እነሆ የአለምን ሀጢያት የሚያስወገድ የእግዚአብሔር በግ እነሆ ብሎ መሰከረ። እንዲሁም አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል። ከእኔ በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኗል ብዬ ስለ እርሱ ያልኩት ይህ ነው ብሎ ተናገረ።

## 2. ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡ ከተጠመቁ በኋላ ወደ ዮሐንስ ቀርቦ "አጥምቀኝ" አለው። ዮሐንስም "እኔ በአንተ እጠመቅ ዘንድ ይገባኛል፣ እንዴት አጥምቀኝ ትለኛለህ? ብሎ ጌታችንን



ለማጥመቅ እምቢ አለ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን "አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል።" ቢለው ፈቀደለትና አጠመቀው። በዚህም ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ተብሏል። ዮሐንስ ወልደ እግዚአብሄር ክርስቶስን የማጥመቅ ጸጋ ተሰጥቶታልና ሴቶች ከወለዳቸው ዮሐንስን የሚበልጠው የለም ተብሎ ከጌታ ተመስ ክሮለታል።

ዮሐንስ ጌታን "ሌላውን በአንተ ስም አጠምቃለሁ አንተን በማን ስም ላጥምቅህ"*(1) ብሎ በጠየቀው ጊዜ

-"እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት አንተ ለዘላለም ካህን ነህ መዝ. 109÷4

-ብርሃንን የምትገልጽ የአብ የባህርይ ልጅ ሆይ ይቅር በለኝ እያልክ አጥምቀኝ" ብሎታል። እንዳለውም አጥምቆታል። ወልዱ ለቡሩክ ከሳቴ ብርሃን ተሣሀለነ እንዲሉ። ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው እጁን አልጫነበትም ነበር። እጁን ጭኖበት ቢሆን ኖሮ አይሁድ ጌታችንን በዮሐንስ ከበረ ባሉ ነበርና ክርስቶስ የተጠመቀበት እለት

---

*(1) ስመ አብ ብከ ወስመ ወልድ ለሊከ መስመ መንፈስ ቅዱስ ሀልው ውስቴትከ ባዕደ አጠምቅ በስምከ መበስመ መኑ አጠምቅ ኪያከ እንዲሉ ሊቃውንት ትርጓሜ ወንጌል ተመልከት

ኢጲፋንያ ይባላል። ኢጲፋንያ ቃሉ የፅርዕ ሲሆን በግዕዝ አስተርዕዩ በአማርኛ መታየት /መገለጥ/ ማለት ነው። ጌታችን መጥተህ አጥምቀኝ ሳይል ወደ ዮሀንስ ሄዶ ነው የተጠመቀው እንደ ሥርዓቱ ከሆነ ሎሌ ወደ ጌታው ይሄዳል እንጂ ጌታ ወደ ሎሌ አይሄድም። ጌታችን ግን መምህረ ትህትና ነውና ወደ ዮሐንስ ሄዶ ተጠመቀ። ክርስቶስ ዮሐንስን መጥተህ አጥምቀኝ ቢል ኖሮ የዛሬ ሹማምንት የበላይ ባለሥልጣናት መጥታችሁ አጥምቁን ባሉ ነበረና ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ይጠመቁ ሲል ለአብነት ሄዶ ተጠምቋል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ የተጠመቀው እንደ አይሁድ ሥርዓት ለመንጻት አይደለም አይሁድ ከርኩሰታቸው ለመንጻት ይጠመቁ ነበር ጌታ ግን ኃጢያት ኑሮበት ሊነጻ የተጠመቀ ሆኖ ሳይሆን ከንጹህ ከርሱ ጋር አንድነት ይሰጠን ዘንድ ተጠመቀ። በመጠመቁ ኃይል የሚያገኝ ሆኖ አይደለም። በዚያ ፈንታ በጥምቀት ጥምቀታችንን ቀድሶልን ሰይጣንን የምናሸንፍበት ኃይል፣ የእግዚአብሔር ልጅ የምንሆንበትን ጸጋ፣ ሊያድለን ተጠመቀ



እንጂ[*(2)] ጌታ በ30 ዘመኑ የተጠመቀበት ምክንያት አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ በጥምቀት ያገኛተን ልጅነት አስወስዶ ነበርና ያን ለመመለስ ሲል ጌታ በ30 ዘመኑ ተጠመቀ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ30 ዓመት ከ13 ቀኑ በ5531 ዓ.ዓለም /በ31 ዓመተ ምህረት/ በዘመነ ሉቃስ ጥር 11 ቀን ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ተጠመቀ። ሲጠመቅም የዮርዳኖስ ወንዝ ከመካከሉ ተከፍሎ ወደፊትና ወደኋላ ሸሽቷል። ኮረብቶችና ተራሮችም ወደ ላይ በመዝለል አምላክነቱን መስክረዋል። በዚህም ልበ አምላክ ዳዊት በመዝ 113÷3-8 ላይ "ባህር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ ተራሮችም እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ አንቺ ባህር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖስ ወደ ኋላሽ የሸሸሽ ምን ሆናችኋል? እናንተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረበቶችም እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ?

---

*(2) ሃይማኖተ አበው ግዘት ዘጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት ከገፅ 549-557 ተመልከት
* ሃይማኖተ አበው ሳዊሮስ ዘአንፆኪያ መቅዶንዮስን አውግዞ የተናገረው ከገፅ 356-378 ተመልከት

ከያዕቆብ አምላክ ፊት፣ ከጌታ ፊት ምድር ተናወጠች በማለት የተናገረው ትንቢት ተፈጸመ በተጨማሪ መዝ 76/77÷16 ተመልከቱ።

በዘመነ አሪት ተሰውሮና ርቆ የነበረው ምስጢረ ሥላሴ በግልጽ ታይቷል። ይኸውም ወልድ /ኢየሱስ ክርስቶስ/ በዮርዳኖስ ወንዝ ሲቆም አብ በደመና ሆኖ በርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነውና እርሱን ስሙት" ሲል መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታ ራስ ላይ አርፏልና። በዚህም አንድ አምላክ እግዚአብሔር ሦስት አካላት ሦስት ስሞች ሦስት ግብራት እንዳሉት በግልፅ ተረጋግጧል።

## መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል የወረደበት ምክንያት

ሀ. በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች በጥፋት ውሃ ከጠፉ በኋላ ኖህ በመርከብ ውስጥ ሆኖ ርግብን የጥፋት ውሃ እንደጎደለ አይታ እንድትመጣ በላካት ጊዜ ርግብ "የጥፋት ውሃ ጎደለ" ስትል ቆፅለ ዘይት "/የወይራ ቅጠል/ ይዛ መጥታለች። መንፈስ ቅዱስም የኃጢአት ባህር ጎደለ" ሲል በርግብ አምሳል ታይቷል።



ለ. ርግብ የዋህ ናት፣ ቂም በቀል አትይዝም መንፈስ ቅዱስም ሐዳጊ በቀል ይቅር ባይ፣ የዋህ ተጸጽተን ይቅር በለን ካልነው ይቅር የሚል ነውና በርግብ አምሳል ወረደ።

ሐ. ርግብ ቢመቷት እንቁላሏን ቢሰብሩባት ቤቷን ካላፈረሱባት በቀር ቦታዋን አትለቅም መንፈስ ቅዱስም ሃጢአት ቢሰሩ ጨርሰው ካልካዱት በቀር ከክርስቲያኖች አይለይምና በርግብ አምሳል ተገለጠ።

## 2.2. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃ የተጠመቀበት ምክንያት

ሀ. እግዚአብሔር አምላክ ቀድሞ ሰብዐ ትካትን በማየ አይህ /በጥፋተ ውሃ/ ሰብዐ ግብጽን በኤርትራ ባህር ካጠፋ በኋላ ውሃ ለመአት እንጂ ለምህረት አልተፈጠረም ይሉ ነበርና ለምህረት እንደተፈጠረ ለማጠየቅ።

ለ. ማርና ወተት ለባለፀጎች እንጂ ለድሆች አይገኝም ጥምቀት ግን የተሰራው ለሁሉም ነውና በቀላሉ በሚገኝ /ሁሉም/ በሚያገኘው ውሃ ተጠመቀ።

ሐ. ማርና ወተት አትክልት ላይ ቢያፈሱት ያደርቃል እንጂ አያለመልምም ውሃ ግን ያለመልማል እናንተም በማየ ገቦ /ከጌታ ቀኝ ጎን በፈሰሰው ውሃ/ ብትጠመቁ ልምላሜ ሥጋ ልምላሜ ነፍስ ታገኛላችሁ ሲልበ ውሃ ተጠመቀ።

መ. ማርና ወተት ቢታጠቡበት ያቆሽሻል እንጂ አያነጻም ውሃ ግን እድፍን ያስለቅቃል እናንተም በማየ ገቦ ብትጠመቁ ከሥጋ እድፈትና ከነፍስ እድፈት ትነጻላችሁ ሲል በውሃ ተጠመቀ።

ሠ. ውሃ መልክን ያሳያል እናንተም በጥምቀት ክርስቲያን ሆናችሁ መልክዓ ሥላሴን ታያላችሁ ሲል።

ረ. ውሃ እሳትን ያጠፋል እናንተም በጥምቀት በገሃነም ከመጥፋት ትድናላችሁ ሲል በውሃ ተጠመቀ።

## 2.3. ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ ለምን እንደተጠመቀ



ጌታችን ከሌሎች ወንዞች መርጦ በዮርዳኖስ የተጠመቀበት ብዙ ምክንያቶች አሉት ከእነዚህም መካከል፣

ሀ. ዮርዳኖስ በተፈጥሮ ከላይ ነቁ /መነሻው/ አንድ ሲሆን ትንሽ ወረድ ብሎ ለሁለት ይከፈላል።1ኛ. ዮር 2ኛ. ዳኖስ በመባል። ከዚያም ተመልሶ ተጋጥሞ ዮርዳኖስ ተብሎ ይወርዳል። ጌታ በተጋጠመበት ቦታ ተጠምቋል። ዮርዳኖስ ከላይ አንድ መሆኑ የሰው ዘር ሁሉ የአንድ መሆኑን /ሁለም የአዳም ልጅ የመሆናቸውን/ ምሳሌ ሲሆን ወረድ ብሎ ለሁለት መከፈሉ ሕዝብና አህዛብ ተብለው ለመከፋፈላቸው ምሳሌ ነው።ተመልሶ መጋጠሙና ጌታ በተጋጠመበት ቦታ ላይ መጠመቁ ክርስቶስ የመጣው ለአዳም ዘር ሁሉ እንደሆነና ያመኑበትን ሕዝብና አህዛብን ሁሉ ዘር፣ ቀለም፣ ቦታ፣ ዕድሜ ሳይለይ እንደሚያድን የሚያሳይ ነው።

ለ. ትንቢትና ምሳሌውን ለመፈጸም በዮርዳኖስ ተጠምቋል ትንቢቱ በመዝ. 113÷4-7 እና በመዝ 76÷16 የተገለጸው ነው።

<u>ምሳሌ</u>:- 1. አብርሃም የሰዶምና የገሞራን ነገሥታት ድል ነስቶ ዮርዳኖስን በመሻገር መልከጼዴቅን ተገናኝቷል። አብርሃም የምዕመናን ዮርዳኖስ የጥምቀት መልከጼዴቅ የክርስቶስ ምሳሌ ናቸው። /ዕብራ.7÷1-10/ አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻግሮ መልከጼዴቅን እንደተገናኘ እኛም ክርስቲያን ለመባል በጥምቀት ከእግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ መወለድ አለብን። በዚህም ባህረ ሃጢአትን እንሻገራለን አሪት ዘፍጥረት ምዕ. 14 ሙሉውን ተመልከት።

2. እዮብ በሰይጣን ፈተና ምክንያት በደዌ ተይዞ ሳለ እግዚአብሔር አምላኩ፤ እንዲድን በዮርዳኖስ ወንዝ እንዲጠመቅ ነገሮታል። በዮርዳኖስ በተጠመቀም ጊዜ ከደዌው ሁሉ ተፈውሷል /መጽሀፈ ኢዮብ/ ኢዮብ የምዕመናን፣ ደዌ የመርገመ ሥጋ የመርገመ ነፍስ፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ናቸው።

3. ኤልያስ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ብሔረ ሕያዋን ገብቷል /2ኛ ነገ 2÷7-21 እኛም በጥምቀት ከእግዚአብሔር ተወልደን ገነት መንግሥተ ሰማያት እንገባለንና።



4. የሶሪያ የሠራዊት አለቃ ንእማን በለምፅ ተመትቶ ይሰቃይ ነበር በነበነቢዩ በኤልሳዕ አማካኝነት በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከለምጹ ነፅቷል። ንእማን የምዕመናን ኤልሳዕ የካህናት ለምፅ የኃጢአት /የመርገም/ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ ናቸው እኛም በሥላሴ ስም በካህናት ተጠምቀን ከኃጢአት ነፃ ለመሆናችን ምሳሌ ነው።

ሐ. አዳምና ሔዋን ዕፀ በለስን በመብላታቸው የተነሳ ከገነት ተባረው ወጥተው ነበር ከገነት ከተባረሩ በኋላ ዲያቢሎስ የጨለማ መጋረጃ ጋርዶ አገዛዝ አጸናባቸው አገዛዙን እንዳቀልላችሁ ስመ ግብርናችሁን ጽፋችሁ ስጡኝ አላቸው እነርሱም በሁለት እብነ ሩካብ /ዕብነ በረድ/ ፅፈው ሰጡት ጽሕፈቱም "አዳም የዲያቢሎስ ባሪያ ሔዋን የዲያቢሎስ ገረድ" የሚል ነበር አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎታል ጌታ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ ያን የዕዳ ደብዳቤ እንደሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶታል። በሲኦል ያለውንም በእለተ አርብ ደምስሶታል። ቅዱስ ጳውሎስ "በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም

በትዕዛዙ የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው" ቆላ 2÷11 ያለው ይህን ለመግለፅ ነው።

## 3. የጥምቀት ጥቅም

ጌታችን በጥምቀቱ ውሆችን ቀድሶ የርዳኖስን ብርሀት ማህፀን አድርጎ ሰጥቶናል በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ታላቅ ቦታ የሚሰጠው ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ክርስቲያን ሊያምነውና ሊፈጽመው የሚገባ ታላቅ ምስጢር ነው። እያንዳንዱ ሰው ምስጢረ ጥምቀትን ማመንና በተግባር መፈጸም ግዴታው የሆነው በጥምቀት አማካይነት የሚሰጠው ጸጋ እንዳያመልጠው ነው።

### 3.1. ከእግዚአብሔር መወለድ /ልጅነት ማግኘት/

ሰው በሥላሴ ስም በተጠመቀ ጊዜ ከሥላሴ የፀጋና ልጅነትን ይጎናጸፋል ከእግዚአብሔር የምንወለደው ልደት ሁለተኛ ልደት ነው። የመጀመሪያው ልደት ከወላጆቻችን በሥጋ የምንወለደው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከእግዚአብሔር በጥምቀት አማካይነት በመንፈስ ቅዱስ እንወለዳለን የመጀመሪያው ልደት ግዙፍ ሲሆን ሁለተኛው



ልደታችን ረቂቅ ነው፡ ጌታ በወንጌል ይህንኑ ሲያስረዳ "ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው /ዮሐ. 3÷3-6/ በማለት ገልጿል።

እግዚአብሄር አምላክ የዲያቢሎስ ልጆች ከመሆን በጥምቀት ነፃ አውጠቶ የጸጋ ልጆቹ እንድንሆን ፈቅዶልናል። የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ደግሞ የግድ መጠመቅ ያስፈልገናል የዲያቢሎስ ልጆች የሆኑ የግብር አባታቸውን የሰይጣንን ርስት ገሃነመ እሳትን እንደሚወርሱ /ማቴ. 25÷41/ ከእግዚአብሔር የተወለዱ ደግሞ የአባታቸውን ርስት መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳሉ። /ማቴ. 25÷34/ በሐዲስ ኪዳን ከእግዚአብሔር ፍፁም ፍቅር የተነሳ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለው ግንኙነት የአባትና የልጅ /የቤተሰብ/ ግንኙነት እንደሆነ /ማቴ. 5÷9-48 ማቴ. 6÷1-9 ማቴ. 7÷11 1ኛ ጴጥ 1÷3-23 ገላ. 3÷26 ቲቶ 3÷5/ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመጥቀስ አበው ያስተምሩናል።*(3)

*(3) ወበዝንቱ እሙራን ውዕቶሙ ደቂቀ እግዚአብሔር ወደቂቀ ጋኔን እንዲል 1ኛ ዮሐ. 3÷10

እምነት ለመዳናችን መሠረት ነው ፍጹም የሚሆነው ግን በጥምቀት ነው በጥምቀት ከጌታ ጋር አንድ እንሆናለን ይህን ቅዱስ ጳውሎስ ሲገልጸው "በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል" /ገላ 3÷26-27/ ብሏል።

## 3.2. ሥርየተ ኃጢአት /ከሐጢያት መንፃት/

በጥምቀት ከሚገኘው ጸጋ አንዱ የኃጢአት ሥርየት ነው። ጥምቀት ኃጢአትን ያስተሰርያል በኃጢአት የረከሰን ሰውነት ይቀድሳል በኃጢአት ያረጀውን ያድሳል ጥምቀት ከረቂቅ የኃጢአት ቆሻሻ የሚያነጻ በመሆኑ ቅዱሳን አባቶች በጸሎተ ሃይማኖት "ኃጢአት በምታስተሰርይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" ብለዋል ቅዱስ ጴጥሮስ በሐ.ሥ. 2÷38-39 ላይ በትምህርቱ ያመኑትን ሰዎች "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ" ብሏቸዋል።



ቅዱስ ጳውሎስንም ሐናንያ "አሁን ለምን ትዘገያለህ ተነስና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ" /የሐ.ሥ. 22÷16 የሐዋ.ሥራ 9÷1-18/ ብሎታል ቅዱስ ጳውሎስ የኃጢአት ስርየት ያገኘው አምኖ በመጠመቁ ነው። በጥምቀት አማካይነት ሥርየት ኃጢአት ንጽህና ቅድስና እንደሚገኝ ነቢያት በትንቢት አስቀድመው ተናግረዋል። ነቢዩ ሕዝቅኤል በምዕራፍ 36÷25 ላይ "ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩስታችሁም ከጣኦታችሁም አጠራችኋለሁ አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ" በማለት ጽፏል። ነቢዩ ሚክያስም ተመልሶ የጥምቀትን አስፈላጊነት ገልጾታል። ቅዱስ ጳውሎስም የነቢያቱን ቃል በማረጋገጥ በጥምቀት ቅድስና ክብር እንደሚገኝ ተናግሯል። ኤፌ. 5÷26-27 የተጠመቀ ሰው አሮጌ ሰውነቱ ታድሶ አዲስ ሰውነት ያገኛል። ፍጥረታዊ ሰው መሆኑ ቀርቶ መንፈሳዊ ሰው ይሆናል። 1ኛ ቆሮ 2÷14-16/ በአዲሱ ሰውነት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሆኑትን ዘጠኙን ፈቃዳተ ነፍስ ያፈራል። /ገላ 5÷22-24/

## 3.3. ድኅነት

ሰው ለመዳን ወይም የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ወደ መንግሥተ ሰማያት ለመግባት መጠመቅ ያስፈልገዋል። ጌታችን በወንጌል "ሰው ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት አይገባም" በማለት ተናግሯል። ዮሐ. 3÷5 ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት ካልቻለ ወደገሃነም መሄዱ የማይቀር ነው ወደ ገሃነም ከገባ ደግሞ የሚያጋጥመው ዘላለማዊ ሞት ነው። ስለዚህ ሰው ለመዳን የግድ መጠመቅ ያስፈልገዋል። በተጨማሪም በማርቆስ ወንጌል በም. 16 ቁ.16 ላይ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል" በማለት ለመዳን ማመን ብቻ ሳይሆን መጠመቅም እንደሚያስፈልግ አረጋግጧል። "ያመነ ይድናል" አላለም ያመነ የተጠመቀ ይድናል አለ እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ሕይወን እንዲያገኙ መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ ነው ። ስለዚህ እግዚአብሄር አምላካችን የርሱ ልጆች ሆነን እንድንድን ጥምቀትን አዘጋጅቶልናል። በልጁ አምነንና በውሃ ተጠምቀን በመንፈስ ቅዱስ ክብር የዘላለም ሕይወትን መውረስ ይገባናል።



## 3.4. የቤተክርስቲያን ወገን /አባል/ መሆን:-

ማንም ሰው የቤተክርስቲያን አባል ለመሆንና ቤተክርስቲያን ለምዕመናን ለምትሰጠው ምሥጢራት ተካፋይ ለመሆን መጠመቅ አለበት። ከሌሎች ምሥጢራት አስቀድሞ ጥምቀት የሚፈጽመው ያለሱ የተቀሩትን ምስጢራት ለመሳተፍ ስለማይቻል ነው። ስለዚህ ጥምቀት ወደ ቤተክርስቲያን ለመግባት እንደ በር የሚያገለግል ነው። የተጠመቀ ሰው የእግዚአብሔር ሕዝብ (እስራኤል ዘነፍስ) ይሆናል።*(4)

እግዚአብሄር አምላክ በቤተክርትሲያን በኩል የሚያድለውን በረከትና ጸጋ ይካፈላል ከክርስቶስ መንጋ /ምዕመናን/ ጋር አንድ ይሆናል። /ገላ. 3÷24-26/ ቤተክርስቲያን የኖህ መርከብ አምሳል ናት። ሐመረ ኖህ በውስጧ የተጠለሉትን ከጥፋት ውሃ እንዳዳነች ሁሉ

---

*(4) እሥራ- ሕዝብ
* ኤል -እግዚአብሔር
* እስራኤል-ህዝበ እግዚአብሄር ማለት ነው በዕብራይስጥ /አምላኩ እግዚአብሄር የሆነለት ህዝብ/ ማለት ነው።

ቤተክርስቲያንም ከሚመጣው ከገሀነብ እሳት ጥፋት በጥምቀት አማካይነት ወደርሷ የገቡትን ታድናለች። 1ኛ ጴጥ 3÷20-21 በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመሆን መገረዝ ግዴታ ነበር። ግዝረት ሊመጣ ላለው ለጥምቀት ምሳሌ ነው /ቆላ. 2÷11-13/ እግዚአብሔርም ለአብርሃም "ቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና።" ዘፍ 17÷14/ በማለት የመገረዝን አስፈላጊነት ገልጿል። ምሳሌ የሆነውና በጥምቀት የተተካው ግዝረት የሄን ያህል ቅጣት ካስከተለ አማናዊውን ጥምቀት ያልተጠመቀማ የበለጠ ቅጣት እንደሚገጥመው የተረጋገጠ ነው። ይህም ቅጣት የዘለዓለም ሞት ነው።

ግዝረት ለሕዝበ እስራኤል የአብርሃም ቃል ኪዳን ባለቤቶች (ተሳታፊዎች) የመሆናቸው መለያ ምልክይት እንደሆነ ሁሉ ጥምቀትም በክርስቶስ ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆናቸውና የመንግሥቱ ወራሾች እንዲሆኑ ምልክት ነው።



ግዝረት በኦሪት ግዴታ እንደነበር በጥምቀትም ለክርስቲያን ሁሉ ሊፈጽሙት የሚገባ ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ሕዝበ እሥራኤል ከዘመናት የባርነት ቀንበር ነፃ የወጡት ከሃይለኛው የፈርኦን እጅም የተላቀቁት ባህረ ኤርትራን ተሻግረው ነው። እኛም ጥምቀትን ከተቀበልን በጥምቀት ከገሃነመ እሳት ጥፋትና ከዲያቢሎስ ተገዢነት እንድናለን።

## 4. ምስጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ግዴታዎች

ምሥጢረ ጥምቀትን ለመፈጸም /ለምሥጢረ ጥምቀት/ አፈጻጸም የማይቀሩ ነገሮች አሉ። እነዚህንም:-

### 4.1. የተጠማቂው ሃይማኖት

ተጠማቂው በእድሜው ከፍ ያለ ሰው ከሆነ /አስቀድሞ ክርስትናን ያልተቀበለ ከሆነ/ ከመጠመቁ በፊት የሃይማኖት ትምህርትን በሚገባ መማር አለበት። ሃይማኖትን በሚገባ ተምሮ ካመነ በኋላ ሰይጣንን ክዶ ክርስቶስን አምኖ

ሃይማኖቱን መስክሮ /ጸሎተ ሃይማኖትን ደግሞ/ ይጠመቃል። ሐዋሪያትም በጥንት ስብከት ከቤተ አይሁድና ከቤተአሕዛብ ወደ ክርስትና የተመለሱትን ሰዎች ያጠመቁት በመጀመሪያ አስተምረው አሳምነው ነው። ጌታችንም በወንጌል ያመነ የተጠመቀ ይድናል ብሏል። /ማር. 16÷16 ዮሐ. 2÷37/ በፍትሐ ነገሥት ንኡስ ክርስቲያን /የክርስቲያን ታናሽ / ይህ ስም የተሰጠው ተጠምቆ የእግዚአብሔር ልጅ ስላልሆነ ነው። /ከመጠመቁ በፊት ሥራው ይመረመራል ተመርምሮ እምነቱ ከተረጋገጠ በኋላ ይጠመቃል ይላል። ተጠማቂው ሃይማኖቱን ከተረዳና ከአመነ በኋላ ንስሐ መግባት አለበት። ይህንንም ቅዱስ ጴጥሮስ "...ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ስም ተጠመቁ..." በማለት ለጥምቀት የተዘጋጁትን አማንያን አዟቸዋል። /የሐዋ.ሥ. 2÷38 ተጠማቂው ህጻን ከሆነ ግን የሃይማኖት ምስክርነት በህጻኑ ምትክ የክርስትና አባትና እናት ይፈጽማሉ። ኋላም ስለ ሃይማኖቱ በማስተማር ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ። የክርስትና አባት እናት ለህፃኑ መምህረ ሃይማኖት ናቸውና።



## 4.2. *<u>አጥማቂ ካህን</u>*

ጥምቀት ፍጹም የተሟላ እንዲሆን አጥማቂው ሰው ሥልጣነ ክህነት ያለው እውነተኛ ካህን ኤጲስ ቆጶስ ወይም ቄስ መሆን አለበት። ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው ፍጹም ማጥመቅ አይገባውም። በድፍረት ወይም በስህተት ቢያጠምቅ ተጠማቂው እንደተጠመቀ አይቆጠርም። በጥምቀት የሚገኘውን በረከትና ጸጋ አያገኝም። ስለዚህም ጥምቀትም ሆነ ሌሎቹ የቤተክርስቲያን ምስጢራት ያለ ሥልጣነ ክህነት ስለማይፈጸሙ የካህን አስፈላጊነት ወሳኝ ነው። ጌታችን ሐዋርያትን "ሂዱና አህዛብን ሁሉ አስተምሩ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው። ደቀመዛሙርቴ አደርጓቸው "በማለት አዟቸዋል። /ማቴ. 28÷19/ ሐዋርያዊ ሥልጣነ ክህነት የሌለው ማጥመቅ እንደማችል የሕግ መጽሐፋችን "ከኤጴስ ቆጶስ ወይም ከቄስ በስተቀር ማንም አያጥምቅ" ይላል በተጨማሪ ከመናፍቃን ዘንድ ሔዶ የተጠመቀ ሰውም ክርስቲያን እንደማይባል ማንም ሰው ከአላውያን ዘንድ ቢጠመቅ ምዕመናን

/ክርስቲያን/ አይባልም ይላል /ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ አንቀጽ ሦስት/

## 4.3. በውሃ መጠመቅ

ጥምቀት በግድ በውሃ መፈጸም አለበት። ጥምቀት በውሃ የሆነበት ምክንያት ጌታችን በወንጌል ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ብሎ ስለተናገረ ነው።*(7) ክርስቶስ የተጠመቀው በውሃ ነው እኛም እርሱን አብነት አድርገን በውሃ እንጠመቃለን። ሐዋርያትም ከጌታ በተማሩት ትምህርት መሠረት ሕዝቡን /ያመኑትን/ በውሃ አጥምቀዋል/ የሐ.ሥ 8÷38 ኤፌ 5÷26 የሐ.ሥ. 2÷3 እስከ 38 /በፍትሃ ነገሥት ፍትሀ መንፈሳዊ አንቀጽ 3 ላይ ጥምቀት በወራጅ ውሃ ወይም በማጥመቂያ በሚፈስ ውሃ ይሁን በዚያ የውሃ ችግር ቢኖር ያገኙትን ውሃ ቀድተው ወደ ማጥመቂያው ያፍስሱ "በማለት ለጥምቀት የውሃን አስፈላጊነት ደንግጓል። ውሃ የሰውነትን እድፍ ያስወግዳል

*(7) ፍትሐ መንፈዋ አንቀፅ ሦስት ተመልከት በፍትሐ ነገሥት



ጥምቀትም የነፍስን እድፍ ያስወግዳል ውሃ ከከፋ ሀሊና ለመንጻታችን ማረጋገጫ ነው። ዕብራ. 10÷22 ተጠማቂው ሰው በውሃ ውስጥ ሦስት ጊዜ ብቅ ጥልቅ በማለት ጌታችን ሦስት መአልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ መነሳቱን ይመሰክራል። ጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አብረን ለመሞታችንና ለመነሳታችን ማረጋገጫም ነው። /ሮሜ. 6÷3-8/

ለንጊኖስ የተባለ ወታደር በእለተ አርብ ክርስቶስ ተሰቅሎ እያለ የጌታን ቀኝ ጎን በጦር በወጋው ጊዜ ትኩስ ደምና ውሃ በአንድነት ፈሷል። /ዮሐ. 19÷34/ ደሙን ለመጠጣችን ሰጥቶናል ውሃውንም ለጥምቀታችን መሆኑን ሲያጠይቅ ነው። ይህንንም ፍቁረ እግዚእ ዮሐንስ እንዲህ ሲል ገልጾታል። "በውሃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በውሃና በደሙ እንጂ በውሃው በቻ አይደለም" 1ኛ ዮሐ. 5÷6-8 የምንጠመቅበት ውሃ አስቀድሞ ተራ ውሃ ቢሆንም እውነተኛ ካህን ጸሎትን ጸልዮ አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቀዱስ አሐዱ ውዕቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ ሲባርከው ውሃው ተለውጦ ከጌታችን ቀኝ ጎን የፈሰሰው /ማየ ገቦ/ ይሆናል። በሕዝ. 36÷25 ላይ "ጥሩ

ውሃንም እረጭባቸኋለሁ ከርኩስታችሁም ትጠራላችሁ "ተብሎ የተነገረው ይህንኑ የሚያስረዳ ነው።

## 4.4. በሥላሴ ስም መጠመቅ

ማንም ሰው በእውነተኛ ካህን ሥርዓተ ጥምቀት የሚፈጸምለት በሥላሴ ስም ነው። ጥምቀት በሥላሴ ስም የሆነበት ምክንያት ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ ያዘዝኳችሁንም እንዲፈጽሙ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው። እነሆ እኔ እስከ አለም ፍጻሜ ድርስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ "ማቴ 28፥19-20 በማለት ለሐዋርያት ባዘዘው መለኮታዊ ትዕዛዝ አማካይነት ነው። በፍትሀ ነገሥት ይህንኑ የጌታን ቃል በመከተል "የሚጠመቀውን ሰው ራስ የሚጠልቅ ውሃ ባያገኝ እፍኝ ያሀል ውሃ ወስዶ በሥላሴ ሥም /በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም/ ራሱን ያጥምቀው" በማለት በስመ ሥላሴ መጠመቅ እደሚገባ ያስረዳል።

አንዳንድ ክፍሎች በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሐዋርያት "በኢየሱስ" ስም ብቻ ስላጠመቁ ዛሬም በሥላሴ ስም



መጠመቅ የለብንም የሚሉ አሉ። ሐዋርያት በጥንተ ስብከት በኢየሱስ ስም ያጠመቁት የጌታን ትዕዛዝ ዘንግተው ወይም ጥሰው አይደለም። በርግጥ በሐ.ሥ. 2፥38 8፥16 18፥48 19፥5 ላይ እንደተገለጸው ሐዋርያት በኢየሱስ ስም ቢያጠምቁም ይህንን ያደረጉበት መሠረታዊ ምክንያት ነበራቸው። ሐዋርያት ለስብከት ወንጌል በተሰማሩ ጊዜ በቤተ አህዛብ ይቅርና በቤተ አይሁድም እንኳን የክርስቶስ አምላክነት አይታመንም ነበር። እንደውም አይሁድ "ክርስቶስ ሞቷል ሐዋርያትም ሥጋውን ከመቃብር ሠርቀው በመውሰድ ከሙታን ተለይቶ ተነሳ እያሉ በሐሰት ያስተምራሉ" እያሉ ሕዝቡ ወንጌልን እንዳይቀበል ያውኩ ነበር።

ስለዚህ ሐዋርያት የመጀመሪያ ሥራቸው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ እንዳልቀረ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሳና ወደ ሰማይ እንዳረገ በእግዚአብሔር አብ ቀኝ እንደተቀመጠ እንዲሁም ክርስቶስ እውነተኛ የባህርይ አምላክ እንደሆነ ማስተማር ነበር። ይህንንም ለማስረዳት በቃል ትምህርት ብቻ ሳይወሰኑ በክርስቶስ ስም አሳምነው በማጥመቅ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ በማድረግ፣ የተለያዩ

አስደናቂ ታምራትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በማድረግ ክርስቶስ ህያው አምላክ እንደሆነ ስሙም ሕይወት መድኃኒት መሆኑን ያስረዱ ነበር። በሐ.ሥ. 4÷33 ተመልከት በማለት ተጽፏል። እንዲሁም አይሁድና የአይሁድ ሊቀ ካህናት ሐዋርያትን በክርስቶስ ስም እንዳያስተምሩ እንዳገዱዋቸው ሐዋርያትም እለት እለት ስለ ክርስቶስ ያስተምሩ እንደነበር በሐዋ. 5÷40-42 በግልጽ ጽፏል።

ስለዚህ ሐዋርያት የጌታን የባህርይ አምላክነት በተጨባጭ ለማስረዳት በቅድሚያ በክርስቶስ ስም አሳምነው ያጠምቁ ነበርና ነው።

## 5. *ጥምቀት አንዲት ናት*

ጥምቀት አንዲት መሆንዋን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ግልጽ በሆነ ቃል "አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" /ኤፌ 4÷5/ በማለት አስቀምጦልናልና። እግዚአብሔር አንድ ስለሆነ አንድ እግዚአብሄር በትክክል የሚመለክበትን ሃይማኖት አንድ ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው፤ እውነተኛ ሃይማኖት አንድ ብቻ ስለሆነ፤ በዚህ ሃይማኖት አምነን የምንጠመቀው ጥምቀት አንድ መሆኑ የግድ



ነው።*[8] በጸሎተ ሃይማኖት ቅዱሳን አባቶች "በአንዲት ጥምቀት እናምናለን" በማለት ጥምቀት የማያስልስ አንድ ብቻ መሆኑን ገልጸውታል።

### *ጥምቀት የማይደገም አንድ ብቻ*. *የሆነበት ምክንያት:-*

5.1. ከሥጋዊ ወላጆቻችን የምንወለደው አንድ ጊዜ ብቻ እንደሆነና ሊደገም እንደማችል ከመንፈሳዊ አባታችን ከእግአብሄር የምንወለደው መንፈሳዊ ልደታችን አንድ ጊዜ ብቻ ነው አይደገምምና /ዮሐ. 3÷6-7

5.2. ለጥምቀት ምሳሌ የሆነው ግዝረት አንድ ጊዜ ብቻ እንደሚፈጸም ጥምቀትም አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማልና /ቆላ 2÷11-13

5.3. ጥምቀት የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ምሳሌ ነው

ክርስቶስ የሞተው አንድ ጊዜ የተነሳውም አንድ ጊዜ ነው ጥምቀትም እንዲሁ አንድ ጊዜ ብቻ ይፈጸማል አይደገምም። /ሮሜ 6÷14/ ጥምቀት አንዲት ናት ስንል

---

*[8] ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ሃጢአት እንዳሉ ሠለስቱ ምዕት

በ40ና በ80 ቀን ቢጠመቁ፣ እንዲሁም በ40 እና በ80 ዓመት ቢጠመቁ፣ በአቢይ ባህር ወይም በንዑስ ባህር ቢጠመቁ፣ በሊቀ ጳጳስ፣ በኤጲስ ቆጶስ፣ በቄስ እጅ ቢጠመቁ፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እስከተጠመቁ ድረስ ለውጥ የለውም ማለት ነው። ሁሉም ከእግዚአብሔር የምንወለድበት ነው። ስለዚህ ጥምቀት አንዲት ናት።

## 6. የአንዲት ጥምቀት ክፍሎች

ልጅነት የምታስጠው ጥምቀት አንደ ስትሆን በሶስት ወገን ትከፈላለች:-

1. የውሃ ጥምቀት /ማየ ገቦ/
2. ደመ ሰማዕት /ስለ ክርስቶስ ብለው በመከራ የሚያፈሱት የሰማዕታት ደም/
3. ባህረ እሳት ናቸው።*

የጥምቀት ምስጢራዊ ፍቺ ከክርስቶስ ጋር አብሮ መሞት መነሳት ነው። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ በፃፈው

* በቤተክርስቲያን ሊቃውንት አተረጓጎም እንብዐ ንስሀም /የንስሀ እንባ/ ከጥምቀት የቆጠራል።



እንረዳለን በሮሜ 6÷14 "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ ለመሆን የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን እንግዲህ ከክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበርን ሞቱን በሚመስል ሞት ከርሱ ጋር ከተባበርን ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን" ደግሞም በገላ. 3÷27 "ክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል" የሚል ቃል ተፅፎ ስናገኝ በቆላስ 2÷12 በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ከርሱ ጋር ተነሳችሁ" የሚል ቃል ሰፍሯል።

ከላይ የሰፈሩት የቅ/ጳውሎስ መልእክታት ሁሉ የሚያስረዱት ጥምቀት ማለት ከክርስቶስ ጋር ሞቶ መነሳት ማለት እንደሆነ ነው።

ስለዚህ በውሃ ጥምቀት ሳይደርሱ በመንገድ ላይ ስለ ክርስቶስ ሲመሰክሩ በአላውያን ሰይፍ ተቀልተው ያረፉ ወይም ወደ እሳት የሚወረወሩ ሰዎች ውሃ ጥምቀት

ባለመብቃታቸው የእዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም አይባልም። እነዚህ ሰዎች በተግባር ክርስቶስን መስለውታል የጥምቀት ምስጢራዊ ፍቺ ከክርስቶስ ጋር ሞቶ መነሳት ከሆነ እነዚህ ሰዎች በደማቸው ወይም ወደ እሳት በመጣላቸው ከክርስቶስ ጋር ስለሞቱ እርሱ ክርስቶስ ደግሞ ከርሱ ጋር ያስነሳቸዋል በክርስቶስ አምነው ሁሉን አሟልተው ነገር ግን ሳይጠመቁ ቆይተው ስለ ክርስቶስ መስክረው ቢሞቱ በደማቸው የተጠመቁ ስለሆነ እንደ እውተኛ ጥምቀት እንደሚቆጠርላቸው ቤተክርስቲያን ታስተምራለች።

ቀድሞ ኢ-አማንያን የነበሩ ኋላ ግን አምነው በአላውያን ነገሥታት ፊት ስለ ጌታ አዳኝነት ሲመሰክሩ በሰማዕትነት የሚያልፉ ሰዎች ስለ ክርስቶስ ሲሉ ያፈሰሱት ደማቸው ደመ ጥምቀት ይሆንላቸዋልና ወደ እሳቱም ቢጥሏቸው እሳቱ የጥምቀት ባህር ይሆንላቸዋል። ጌታን በሞቱ መስለውታልና። ፀጋውን ይጎናጸፋሉ የክብር ትንሣኤም ይነሳሉ። እነዚህ ሰዎች በመንገድ ላይ ሰማዕትነትን ባይቀበሉ ኖሮ በውሃ መጠመቃችን የማይቀር ነበር። ለክርስቶስ ቃል ታዛዥ መሆናቸውን በተግባር አሳይተዋልና።



ጌታ እነዚህ በውሃ ሳይጠመቁ በሰማዕትነት ላለፉ ሰዎች “በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ” /ማቴ. 10÷32 ተብሏል። በተጨማሪም በማቴ 16÷25 ላይ “ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል ስለእኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል” በማለት ሰማዕታት ደማቸው ደመ ጥምቀት ወደ እሳት የተጣሉበት ቦታ ባህረ ጥምቀት ሆኖላቸው ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚገቡ ገልጿል አስተምሯል።

ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ብለው በሰማዕት ያረፉ ሰዎች የዘላለም ሕይወት ያገኛሉ። ቤተክርስቲያናችን አማናዊት ጥምቀት በእንዲህ ዓይነት መልኩ እንደምትሰጥ ታምናለች ታስተምራለችም። ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና በሲኦል የነበሩ ነፍሳትና ፈያታዊ ዘየማኑን ጌታን ይማፀኑት ነበር። ፈያታዊ ዘየማን ጌታን ይቅር በለኝ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ብሎታል። /ለመጠመቂያ ጊዜ የለውም ነበርና/*(9)

---

*(9) ፈያታዊ ዘየማን በቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ሲሆን ቀድሞ በስደት እመቤታችንን በበረሃ አግኝቶ፣ ጌታን ከእጇ ወስዶ ታቅፎ፣ ጓዛቸውን ተሸክሞ፣ መልካም ነገርን አድርጎ ሸኝቷቸው ነበርና፤ ዛሬም በዕለተ ስቅለት ጌታ ያን ውለታውን አስቦለት፤ እርሱም በመስቀል ባጠገቡ ተሰቅሎ ያሰማውን የንስሀ ጥሪ ቃሉን ተመልክቶ ገነትን እንዲወርስ አድርጎታል። ስሙም ጥጦስ ይባላል።

ጌታም እስከ እለተ አርብ ድረስ በሲኦል ውስጥ ሆነው አምላካችን አምላካችን ምነው ተውከን" ለሚሉት ነፍሳት ድህነት ሲል ደሙን አፍስሷል። እነዚህ ሰዎች የንስሐ እንባቸውን አፍስሰዋል ንስሀም ገብተዋል። ስለዚህ ለሁሉም የጌታ ደም ደመ ጥምቀት ሆኗቸው ወደ ገነት ገብተዋል ንስሐቸውም የጌታ ደም ደመ ጥምቀት እንዲሆንላቸው አድርጓል።

## 7. <u>*የሕጻናት ጥምቀት*</u>

በቤተክርስቲያናችን ሁለት የጥምቀት ዘመናት አሉ። እነርሱም የሕፃናትና የትልልቆች የጥምቀት ዘመን በመባል ይታወቃል። እድሚያቸው ለአቅመ አዳምና ሔዋን ከደረሱ በኋላ የሚጠመቁት ጥምቀት የትልልቆች ጥምቀት ይባላል። ይህም ምስጢረ ጥምቀት ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ነገሮች በሚለው ርዕስ ስር የተጠማቂው ሃይማኖት በሚለው ንዑስ ርዕስ የተገለጹ ስለሆነ አሁን የሕፃናትን ጥምቀት እንመለከታለን። ቅድስት ቤተክስቲያናችን ለምስጢረ ጥምቀት አፈጻጸም ብርቱ ጥንቃቄ ታደርጋለች ሰው ሁሉ በጥምቀት አማካኝነት የሚሰጠውን ጸጋ እንዲያገኝ



አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ትፈጽማለች። ሰዎች ሳይጠመቁ እንዳይሞቱ በማለት ሕፃናትን እንዲጠመቁ ታስተምራለች ታጠምቃለችም ሕፃናትን የምታጠምቀው በቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት በቅዱሳን አበው ትውፊትና ሥርዓት መሠረት ነው። የህጻናት ጥምቀት ክርስትና ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ የነበረ ነው። ህጻናትን የምታጠምቀው ከቅዱሳት መጻህፍት በተረዳችው መሠረት እንደሆ ከዚህ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

7.1. በመጽሐፈ ኩፋሌ ም.4 ቁ.9 ላይ "ከተፈጠረባት ምድር ለአዳም አርባ ቀን ከተፈጸመለት በኋላ ይገዛትም ይጠብቃትም ዘንድ ወደ ገነት አስገባነው። ሚስቱንም በስማንያ ቀን አስገባናት" ይላል ለአዳምና ሔዋን ንጽሐ ጠባይዕ ሳያድፍባቸው ከመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ልጅነት ተቀብለው በመላእክት ታጅበው በ40 እና በ80 ቀን ገነት እንደገቡ ዛሬም ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ በጥምቀት አማካይነት ከእግዚአብሔር ተወልደው ገነት መንግሥተ ሰማያት እንዲገቡ ታደርጋለች" ምንም እንኳን ልደተ አዳም ከምድር፣ ልደተ ሔዋን

ከአዳም ጎን ቢሆንም እንኳን አዳምና ሔዋን በህጻናት መጠን ባይፈጠሩም ማለትም አዳም የ30 ዓመት ጎልማሳ ሔዋን የ15 ዓመት ቆንጆ ሆነው ቢፈጠሩም ያች የተፈጠሩባት እለት ካለመታየት ወደ መታየት የመጡባት ስብአዊ ፍጡርንትአቸው የታወቀባትና የተረጋገጠባት ዕለት በመሆኗ እንደ ልደት ቀን ትቆጠራለች። ህጻናትም ቢሆኑ በማሕፀን ሳሉ አይታዩ የነበሩት ወደመታየት የሚመጡትና ሰው መሆናቸው የሚታወቀው በልደታቸው ዕለት ነው። ስለዚህ አዳምና ሔዋን በተፈጠሩ በ40 እና በ80 ቀናቸው በክብር ወደ ገነት እንደገቡ ዛሬም ቅድስት ቤተክርስታያን እግዚአብሄር በመጀመሪያ በሰራው ሥርዓት መሠረት በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት የተወሰደውን ልጅነት ለማስመለስ ህጻናት ወንዶችን በ40 ቀን ህጻናት ሴቶችን በ80 ቀን ዕድሚያቸው ታጠምቃለች።

7.2. እግዚአብሔር የአብርሃምን የይስሐቅንና የያዕቆብን ልጆች ከአህዛብ ለይቶ የተመረጠ ሕዝብ ካደረጋቸው በኋላ የሚመሩበት ሕግ ሰጥቷቸዋል። ከነዚህም መካከል በዘሌዋውያን 12÷1-8 የሚገኘው ነው። እስራኤራውያን



በመንፈስ ረድኤት የእግዚአብሔር በረከት እነዲያ ድርባቸው የእግዚአብሔር ሕዝብ /ወገን/ መሆናቸው እንዲረጋገጥ ወንድ ልጅ በተወለደ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በተወለደች በ80 ቀኗ ወላጆቻቸው መስዋዕት ይዘው ወደ ቤተመቅደስ ይወስዷቸው ነበር። ካህናቱም መስዋዕቱን ሰውተው ህጻናቱን በእግዚአብሔር ስም ባርከው ስማቸውን በመዝገብ አስገብተው ይሰዷቸው ነበር። እንደ ኦሪቱ ሕግ የተፈጸመለት ህጻን የፈጣሪን በረከት ከማግኘትቱም በላይ የእግዚአብሔር ሕዝብ /ወገን/ ይሆናል። እንደዚሁም ቤተክርስቲያናችን ሕፃናቱን በ40 ቀን እና በ80 ቀን አጥምቃ የእግዚአብሔር ወገን ታደርጋለች በዘመነ ኦሪት / ህጻናቱ በወላጆቻቸው እምነት መስዋዕት ተሰውቶላቸው የእግዚአብሔር ወገን እንደሚሆኑ በዘመነ አዲስም ሕፃናት በወላጆቻቸው እምነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተወስደው በጥምቀት የእግዚአብሔር የፀጋ ልጆች ይሆናሉ። በዚህም ህጻናት መስዋዕተ ሐዲስ የሆነውን የክርስቶስን ሥጋና ደም ተቀብለው የእስራኤል ዘነፍስ የቤተክርስቲያን አባልና አካል ይሆናሉ።

7.3. በብሉይ ኪዳን ዘመን አብርሃም እግዚአብሔርን አምኖ ከዘመዶቹ ተለይቶ አምላኩን ከተከተለ በኋላ እግዚአብሄር

የቃል ኪዳን ምልክት ሰጠው ይህም የቃል ኪዳን ምልክት በእግዚአብሄርና አብርሃም በዘሩም መካከል የዘላለም ምልክት ስለሆነ ማናቸውም ወንድ ልጅ በተወለደ በ8ኛው ቀን እንዲገረዝ ታዟል። ትልልቅ ሰዎችም በልጅነታቸው ካልተገረዙ ካደጉ በኋላ ይገረዛሉ። አብርሃም ሲገረዝ የ99 ዓመት ሽማግሌ ነበር። እስራኤል*(10) በ13 ዓመቱ ተገርዟል ይስሐቅ ግን በተወለደ በስምንተኛው ቀን ተገርዟል። እግዚአብሔር አምላክ የዚህን ቃል ኪዳን ፅኑነት "የቁልፈቱን ሥጋ ያልተገረዘ ቆላፍ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና" በማለት ገልጿል። /ዘፍ. 17 በሙሉ ዘፍ. 21÷1-5

በአዲስ ኪዳን ግዝረት ለጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በቆላ. 2÷11-12 ላይ "የሥጋንም ሰውነት በመግፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ የተገረዛችሁ በጥምቀት ከርሱ ጋር ተቀበራችሁ" በማለት ጥምቀት በክርስቶስ አማካኝነት

*(10) እሥራኤል የተባለ ያዕቆብ ነው። ያዕቆብ ማለት አዕቃፂ ሰኩና (ተረከዝ ያዥ) ማለት በመሆኑ አምላኩ እግዚአብሔር በቤት-ኤል ከባረከው በኋላ ስሙ ተቀይሮ እስራኤል ተብሏል።



የሚፈጸም ሕመም የሌለው ከመርገመና ከኃጢአት ቁልፈት የምንለይበት ግዝረት እንደሆነ ገልጿል። በአራቱ ሕጻናትም አዋቂዎችም ተገርዘው እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ወራሾች እንደሚሆኑ ሁሉ ዛሬም ሕጻናትንም አዋቂዎችንም በማጥመቅ የቤተክርስቲያን አባል የክርስቶስ አባል እንደ ተስፋ ቃሉ የመንግሥተ ሰማያት ወራሾች ይሆናሉ። ያልተገረዘ ሰው ከወገኑ ከእስራኤላውያን ተለይቶ እንደሚጠፋ ዛሬም በአዲስ ኪዳን ያልተጠመቀ ሰው ከክርስቲያኖች ተለይቶ በገሃነም እሳት ይጠፋል መንግሥተ ሰማያት መግባት አይችልም።

7.4. ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 10÷1-2 ላይ "ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባህር መካከል ተሻገሩ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባህር ተጠመቁ" ብሎ በመጻፍ የእስራኤላውያን ቀይ ባህርን መሻገር የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ገልጾልናል። እስራኤላውያን ከፈርኦን ባርነት ከግብፅ የመከራ ቦታ በእግዚአብሔር ኃይል ነፃ ከወጡ በኋላ ወተትና ማር ወደ ምታፈሰው ሀገር ለመኻዝ ቀይ ባህርን መሻገር ነበረባቸው ቀይ ባህር እስራኤላውያንን ሲያሻግር

ግብፃውያንን አስጥሟል። በቀይ ባህር መካከል የተሻገሩት እስራኤላውያን አዋቂዎች ብቻ አልነበሩም ህጻናትም አብረው ተሻግረዋል።

ቀይ ባህርን በተአምራት እንደተሻገሩ ጠላቶቻቸው እንደሰጠሙ የአምላክን ድንቅ ሥራን ኃይል የሙሴን ባለሟልነትና ንግግር የሰሙትና ያዩት ትልልቆቹ ናቸው። ህጻናቱ ግን በወላጆቻቸው አማካይነት ከተሻገሩ በኋላ ነፍስ ሲያውቁ እግዚአብሔር በዘጠኝ መቅሰፍት በአስረኛ ሞተ በኩር በአስራአንደኛው መቅሰፍት ስጥመት ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ ባህሩን ከፍሎ ደመና ጋርዶ እንዳሻገራቸው ይነገሩዋቸውን አምነው ከመቀበል በቀር ታሪኩን የሚያረጋግጡበት ሌላ መንገድ የላቸውም። ሕጻናቱም አዋቂዎችም እኩል ተሻግረዋል። ሕጻናቱ በልጅነታቸው ሳያውቁ ሳይረዱ በቀይ ባህር መሻገራቸው ትክክል አይደለምና እስኪያድጉ ድርስ በበረሃ ይቀመጡ አይባልምና ወይም በህጻንነቴ ሳላውቅ የተሻገርኩት መሻገር ስህተት ነውና አሁን ሳውቅ ስረዳ እንደገና ቀይ ባህርን ልሻገር ቢል አይችልም። ቀይ ባህር አንዴ የተሻገረ ለምንግዜም ተሻገረ እንግዲህ በአዲስ ኪዳንም ያለው የጥምቀት ሥርዓት ከዚህ ታሪክ ጋር የተያያዘ ነው። ተነፃፃሪም ነው። እስራኤል ዘነፍስ



ከሲኦል ግብፅ ከፈርኦን ዲያቢሎስ ከግብፃውያን አጋንንት በክርስቶስ መሪነት ነፃ ወጥተው ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ለመግባት የግድ ከጥምቀቱ በቀይ ባህር በኩል መሻገር /ማለፍ/ አለባቸው። ጥምቀት ክርስቲያኖች ከፈጣሪያቸው የጸጋ ልጅነት የሚያገኙበት ከሰይጣን ነፃ የሚወጡበት ሲሆን በአንፃሩ ሀጢአታቸውም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ እንደፈርኦንና ሰራዊቱ በጥምቀት ይደመሰሳል። አዋቂ ሳለ የተጠመቀም በህጻንነቱ የተጠመቀ ውጤቱ አንድ ነው። በሕፃንነቱ የተጠመቀ ሰው መጠመቁን ወላጆቹና የክርስትና አባቱ የሚነግሩትን አምኖ መቀበል ለምግባር ለትሩፋት መነሳሳት አለበት እንጂ እንደገና አጠምቃለሁ ማለት የለበትም የእስራኤላውያን ሕጻናት ቀይ ባህርን አንዴ ብቻ ከተሻገሩ ከዚያም በኋላ መሻገር እንደማይችሉ ይህም ህጻን አንድ ጊዜ ስለተጠመቀ ዳግም መጠመቅ አያስፈልገውም። አንድ ጊዜ የተጠመቀ ለምንግዜውም ተጠምቋል።

7.5. በዘፍ. 7÷1 ላይ እንደምንረዳው "እግዚአብሔር ኖህን አለው አንተ ቤተሰቦችህን ሁሉ ይዘህ ወደ መርከብ ግባ በፊቴ ፃድቅ ሆነህ አይቼሃለውና" በማለት በመርከብ አማካኝ ነት ከጥፋት ውሃ ኖህን ከነቤተሰቡ ሊያድነው እንደወደደ

እንረዳለን ኖህ በትዕዛዙ መሠረት ቤተሰቦቹን ሁሉ ይዞ ወደ መርከብ እንደገባ በዘፍ. 7÷17 ላይ ተገልጿል። ኖህና ቤተሰቦቹ ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥ ሆነው በመርከቡ ውስጥ እንደገቡ ከጥፋት ውሃም እንደዳኑ ተረድተናል። ኖህ ሶስቱ ልጆቹ ሴም፣ ካም፣ ያፌት፣ ህጻናት ቢሆኑ ኖሮ ወደ መርከብ እንዳይገቡ ያግዳቸው ነበርን? የኖህ ልጆች ህጻናት ልጆች ቢኖሩዋቸው ኖሮ ህጻን ስለሆኑ ከመርከብ ውጭ ይተውአቸው ነበርን? እግዚአብሔርን በሃይማኖት ያላወቁና ያላመኑ ለድህነት የተዘጋጀውን መርከብ አይተው ያልተረዱ በመርከብ ውስጥ ለመግባትም ሆነ ላለመግባት በራሳቸው ፈቃድ መወሰን የማይችሉ ሕጻናት ቢኖሩ ኖሮ አድገው የፈጣሪን መኖር አውቀው አምነው ለደህንነት የተዘጋጀውን መርከብ አይተው ወደ መርከቡ ለመግባት በራሳቸው ነፃ ፈቃድ እስኪወስኑ ድረስ ከመርከብ ውጭ የሚያቆይ ወላጅ ይኖር ይሆንን? ምንም ያልበደሉ ህጻናት በጥፋት ውሃ እንዲጠፉ ከመርከብ ውጭ የሚያስወጣቸው ሰው እውነተኛ ወላጅም ጤነኛም መሆኑ ያጠራጥራል እግዚአብሄር ኖህን ያዘዘው ቤተሰቡን ይዞ ወደ መርከብ እንዲገባ ነው ማንም እንዳይጠፉ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ነውና።



ኖህ ከጥፋት ውሃ የዳነበት መርከብ የጥምቀት ምሳሌ እንደሆነ ቅዱስ ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥ.3÷20-22 ላይ ገልጾታል።[*(11)] በመርከቡ ውስጥ ኖህ ከነቤተሰቡ እነዲገባ እንደታዘዘ ዛሬም ከነቤተሰባችን እንድንጠመቅ ቤተክርስቲያን ታዛለች። በእግዚአብሔር ዘንድ ከፊል ድህነት የለውም። ኖህ መላውን ቤተሰብ ይዞ ወደ መርከቡ እንደገባ ዛሬም በኖህ አንፃር የሚገኙ ወላጆች ቤተሰባቸውን በሙሉ ህጻናትንም ሳይቀር ማስጠመቅ አለባቸው። ህጻናትን ከጥምቀት መከልከል ማለት ልጅን ከመርከብ አውጥቶ የጥፋት ማዕበል ውስጥ እንደመወርወር ነው። ይህም በእውነተኛው ዳኛ በእግዚአብሔር ያስጠይቃል።

ጌታ "ሰው ዳግመኛ ከወሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም" ብሏል። /ዮሐ. 3÷8/ የመዳን ወይም የድኅንነት ትርጉምና የመጨረሻ ግቡ የእግዚአብሔርን መንግሥት መውረስ ነው። /1ኛ ቆሮ. 2÷9 ማቴ. 25÷34/ የዘላለም

---

(11) በኖህ መርከብ የገቡት ኖህና ልጆቹ፣ ከብቶቹ፣ አራዊቱ ሁሉ፣ አውሬውም፣ ውሬ፤ ሃጥዐ.ም ሀጥዕ፤ ፃድቅም ፃድቅ፤ ሆነው ሲወጡ፤ በቤተ ክርስቲያን መርከብነት ውስጥ የገቡ ግን ሃጥዑ ፃድቅ፣ ዘማዊው ድንግልከሃዲው አማኝ፣ ርኩሱ ቅዱስ፤ ሆነው ነው የሚወጡት፤ ቤተ ድህነት መበረከት ናትና።

ደህወት የሚባለውም ሞት በሌለበት መንግሥተ ሰማይ የሚኖረው ኑሮ ነው። /ራዕይ 21÷1-4/ ይህንን የዘላለም ደህወት የሚገኝበትን ቦታ ለመውረስ ሰው ሁሉ መጠመቅ አለበት። ይህ ግድ ከሆነም ምንም ያልበደሉ ክፋትም የሌለባቸው ህጻናት ዳግመኛ ተወልደው /ተጠምቀው/ የእግዚአብሔር የፀጋ ልጆች እንዳይሆኑ የሚከለክላቸው ማን ነው? መንግሥተ ሰያማት የአዋቂዎች ብቻ ሳትሆን የህጻናትም ስለሆነች ህጻናት ይድኑ ዘንድ መጠመቅ ይገባቸዋል። መድኃኒታችን በመስቀል ላይ የተሰዋው በአካል ላደጉ በእድሜ ለበለጸጉ ብቻ አይደለም። ህጻናትም የዚህ መስዋዕትነት ተጠቃሚዎች ናቸው።

የክርስቶስ ሞት ለሁሉ ነውና ክርስቶስ የተሰዋላቸውን ሕጻናት አላውቁም አላመኑም ተብሎ ከበረከተ ጥምቀት መለየት በሰው ነፍስ ላይ የሚፈጸም ረቂቅ ወንጀም ነው። ከላይ እንደተጠቀሰ እስራኤላውያን ልጆቻችውን ወደ ቤተ መቅደስ ወስደው መስዋዕት ሲሰውላቸውና ሲያስባርኩዋቸው ህጻናቱም ምንም አያውቁ የህጻናቱ ምንም አለማወቅ በረከታቸውን አላስቀረውም ህጻናቱ ሲገረዙም እንደሌላው እስራኤላዊ የእግዚአብሔር ወገን ሆኑ እንጂ የእግዚአብሔር



ሕዝብ ከመሆን አላገዳቸውም። ዛሬም በህጻንነታቸው ሲጠመቁ አለማወቃቸው በጥምቀት የሚያገኙትን ፀጋ አያጡትም። ከእግዚአብሔርም መወለዳቸውን አያስቀራ ቸውም። ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል ዳግመኛ እንዲወለዱ ወደ ቤተክርስቲያን ወስዶ ማስጠመቅ የክርስቲያን ወላጅ መንፈሳዊ ግዴታ ነው።

7.6. እግዚአብሔር /አምላክ ህጻናትን ከፀጋው አያርቃቸውም ከበረከቱም አይነፍጋቸውም። ገና በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ የተቀደሱና ሀብተመንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ ነቢዩ ኤርሚያስ ገና በእናቱ ማህፀን ሳለ እግዚአብሔር እንደቀደሰው ሲገልፅ "የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ በሆድ ሳለሰራው አውቄሃለው ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአህዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ።" /ኤር. 1÷4-5/ በማለት ጽፏል። በተመሳሳይም ሁኔታ መጥምቁ ዮሐንስም ገና በእናቱ ማህፀን መንፈስ ቅዱስ እንደሚሞላበት ቅ/ገብርኤል ለአባቱ ለዘካርያስ ሲያበስረው "ገናም በእናቱ ማህፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።" በማለት ነግሮታል። /ሉቃ. 1÷15 ይህም

ትንቢት መፈጸሙን በሉቃ 1÷42-45 ላይ እናነባለን። ስለዚህ እግዚአብሔር ህፃናትን በማህፀን ሳሉ የሚቀድሳቸው መንፈስ ቀዱስ የሚያሳድርባቸው ከሆነ ከተወለዱ በኋላ እንዳይጠመቁ የሚከለክላቸው ማነው? በቅዱስ ወንጌል ተጽፎ እንደምናገኘው ፈጣሪያችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለህጻናት ልዩ ትኩረት በመስጠት አቅርቦአቸው አቅፎአቸውና እጁን ጭኖባቸው እንደባረካቸው ተፅፏል። በጊዜው የነበሩ ወላጆች በኦሪቱ ልማድ ልጆቻቸውን ለማስባረክ ወደ መድኃኒታችን ይዘዋቸው ሲመጡ ሐዋርያት ወላጆቹን ተቆጧቸው ህጻናቱን ከለከሉዋቸው መድኃኒታችን ግን ሐዋርያት የሰሩትን ተመልክቶ በዝምታ አላለፈም። "ህጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተው አትከልክሉአቸው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና" በማለት እስከ ምፅአት ለሚነሱ ህፃናት ወደ ፈጣሪያቸው ቀርበው በረከት እንዳያገኙ ለሚያግዱ ወላጆች ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ አቀፋቸውም እጅንም ጭኖ ባረካቸው ይላል። /ማቴ. 19÷13-15 ማር 10÷13-16 ሉቃ. 18÷15-17/ በወላጆች እምነት ልጆች መባረካቸውን ልብ እንበል እንግዲህ ባለቤቱ



ህጻናትን ከበረከቱ ካልነሳቸው ካጠገቡ ካላራቃቸው ተጠምቀው ጸጋ መንፈስ ቅዱስን እንዳይቀበሉ የሚከለክላቸው ማን ነው?

7.7. ቅዱሳን ሐዋርያት በጥንተ ስብከት ሰዎችን አስተምረው አሳምነው ሲያጠምቁ ነበር። የቤተሰቡ ኃላፊ አምኖ ሲጠመቅ ቤተሰቡ በሙሉ አብሮ ይጠመቅ እንደነበረም ተጽፎ አለ። የቤተሰብ ኃላፊ እንደ ራስ ሲሆን ሌላው ቤተሰብ እንደቀረው አካል ነው። ራስ ሲጠመቅ የቀረው አካል እንደማይለይ የቤተሰቡ ሃላፊ አምኖ ሲጠመቅ መላው ቤተሰብ ይጠመቅ ነበር። ቤተሰብ የሚለው ቃል የዕድሜና የፆታ ልዩነት ሳይኖር በአንድ ቤተሰብ ሥርና ስም የሚተዳደሩ ሰዎችን ያጠቃልላል። እስራኤሎች በቤተሰብ ይኖሩ ነበር። በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ቤተሰብ ይባላሉ። /ዘፍ.12÷14/ አብርሃም ብዙ ቤተሰብ ቢኖረውም እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባው ከአብርሃም ጋረ ነው። በረከቱ ግን ለቤተሰቡ ሁሉ ነው። /ዘፍ. 14÷14 ዘፍ. 17÷9-10

በዚሁ መሠረት ሐዋርያት የቤተሰብን ኃላፊ /አስተዳዳሪ/ ባጠመቁ ጊዜ መላው ቤተሰብም ይጠመቅ ነበር።

በቤተሰብ ውስጥ ከህጻን እስከ አረጋዊ ድረስ ስለሚገኝ ሁሉም የእድሜ ገደብ ሳያግዳቸው ይጠመቃሉ። በሐ.ሥ. 2÷38 ላይ ቅዱስ ጴጥሮስ "ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ጸጋ ትቀበላላችሁ የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነው" በማለት ጥምቀት ፀጋ መንፈስ ቅዱስና የተስፋ ቃል ለአዋቂ ብቻ ሳይሆን ለሕጻናትም እንደሚታደል ገልጿል። ለምሳሌ በሐ.ሥ. 10÷44-48 እና በሐ.ሥ. 11÷13-14 ቆርኖሌዎስ ከነቤተሰቡ በሐ.ሥ. 16÷15 ላይ ሊድያ ከነቤተሰብዋ በሐ.ሥ. 16÷43-44 የእስር ቤቱ ዘበኛ ከመላ ቤተሰቡ ጋር በ1ኛ ቆሮ 1÷16 የእስጢፋኖስ ቤተሰብ እንደተጠመቁ ተጽፎ ይገኛል። እነዚህ ቤተሰብ ውስጥ ህጻናት የሉም ማለት ሀሰተኛነት ነው። ህጻናት መጠመቅ የለባቸውም ማለት ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተጻፈ ማንበብና ኢ.ክርስቲያናዊነት ነው።

በእነዚህና እነዚህን በመሳሰሉት ምክንያቶች ቤተክርስቲያናችን ህጻናትን በ40ና በ80 ቀን ታጠምቃለች



በፍትሐ ነገስት አንቀጽ 3 ላይ ቅዳሳን አባቶች "በጥምቀት የተሠራው ለወንዶችም ለሴቶችም ለትልልቆችም ለትንንሾችን ነው" ማለታቸው ከቅዱስ መጽሐፍ መረዳታቸው የቅዱሳን ሐዋሪያት ተከታዮች በመሆናቸው ነው። ስለዚህ ወንድ በ40 ቀን ሴት በ80 ቀን እዲጠመቁ ታዟል። ነገር ግን ህጻኑ ወይም ህጻኗ ለሞት የሚያሰጋቸው ሆኖ ከተገኘ ከ40 ቀን በፊት መጠመቅ ይችላሉ። ህጻኑ ሳይጠመቅ ቢሞት በካህን ጥፋት ከሆነ ከሥልጣነ ክህነት እንዲሻር ጥፋቱ በወላጆች ከሆነ ለተወሰነ ጊዜ ከምዕመናን እንዲለዩ ይደረጋል።
ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ አንቀር 3

ህጻናት የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኙ የወላጆችና የቤተክርስቲያን ፍላጎት ነው። ያለጥምቀት ደግሞ ዘላለማዊ ሕይወት አይገኝም። ቤተክርስቲያን ህጻናት በወላጆቻቸው እምነት የተነሳ የወላጆቻቸውን እምነት የእነሱው እምነት በማድረግ ሕጻናትን ከእግዚአብሔር መንግሥት ውጭ እንዳይሆኑ ታጠምቃለች። ህጻናት በመጠመቃቸው የቤተክርስቲያን ህይወት ይለማመዳሉ።

ከረጅሙ ባጭሩ ከሙሉ በከፊሉ ከብዙ በጥቂቱ የምስጢረ ጥምቀት ትምህርት ይህን ይመስላል።

ምስጋና ይሁን ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን!!



# ክፍል ፫ (ሦስት)

## የመናፍቃን ማንነት

## ከቤተክርስቲያን ታሪክ አንፃር

በመጀመሪያ ስለ መናፍቃን ማንነት ከማየታች አስቀድሞ ይህን ትምህርታዊ ጽሁፍ ለምን መማርና ማወቅ አስፈለገ እንል ይሆናል። ማወቅ ያስፈለገበት ዋናው ቁም ነገር ዛሬ ዓለምን በክህደታቸው ለሞት የዳረጓት የመናፍቃን የሐሰት ትምህርታቸውን ምዕመናን እንዲያውቁትና ጥርጥርን አስወግደው ማንነታቸውንም ተገንዝበው በቀደመችው እምነታቸው እንዲጸኑ ለማድረግ ነው። መናፍቅ የሚለው ቃል " ናፈቀ" ተጠራጠረ ካለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ነው።

መናፍቅ "ተጠራጣሪ በብዙ ቁጥር "መናፍቃን ይሆናል ማለት ነው። መናፍቃን የተለያዩ ስያሜዎች አሏቸው

- በዘመነ ክርስቶስ "ፀራዊ ወልደ ፀራዊ /ጠላት የጠላት ልጅ/ ተብለው ይጠሩ ነበር። ማቴ 13÷39 ማቴ 22÷46-47
- በዘመነ ሐዋርያት "ቢፅ ሐሳውያን" ይባሉ ነበር 2 ቆሮ 11÷26 የሐ.ሥ. 15÷1
- በዘመነ ሊቃውንት መናፍቃን ተባሉ። ትርጓሜውም ተቃዋሚዎች ማለት ሲሆን የክርስቶስን አምላክነት፣ የትድስት ድንግል እመቤታችንን ክብር፣ የቅዱሳንን ምልጃ፣ የመላዕክትን ተራዳኢነት፣ የካናትን ሥልጣን ወዘተ. ባጠቃላይ ኦርቶዶክሳዊ ትውፊትን ስለሚቃወሙ መናፈቃን ተብለዋል።

__መናፈቃን__

- የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ያጣምማሉ 2ጴጥ.1÷20-21 ማር. 4÷5-7
- በንባብ ብቻ እንጂ /በመጻህፍት ምሥጢር/ አያምኑም 2ቆሮ 3÷6
- ሆዳቸው አምላካቸው ነው። ዕን. 12÷15-17 ሮሜ. 16÷17-20 ፊልጲ. 3÷17-21



የቤተክርስቲያን አባቶችም በዘመኑ የተነሱትን መናፍቃንን አሳፍረው ለመመለስ እና ሃይማኖታችንን ለማጽናት ሦስት አበይት ጉባኤዎችን አዘጋጅተው ከሃደያንን አሳፍረው አውግዘው ለይተዋቸዋል።

## *ሦስቱ የቤተ ክርስቲያን ዓለም አቀፍ ጉባዔያት*

- ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን የምትቀበላቸው ጉባዔያት ሦስት ብቻ ናቸው። 4ኛውን የኬልቄዶንን ጉባኤ አትቀበልም።

## *1ኛ. የኒቅያ ጉባዔ በ325 ዓ.ም ተደረገ*

- በአርዮስ የወልድን የባይህርይ አምላክነት መካድ ምክንያት በታላቁ ቁስጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት 318 ሊቃውንት በተገኙበት ተደረገ።
- የጉባዔው መሪ የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ አለስክንድሮስ ሲሆን አፈጉባዔው ሊቀዲያቆናት* አትናትዮስ ነው።

---

* በሃይማኖተ አበው ሠለስቱ ምዕት "ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚዕ ማህየዊ" እስከሚለው የወሰኑ መሆኑ ተገልጿል።

- "ሁሉን በፈጠረ" ከሚለው ጀምሮ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም" እስከሚለው ያሉው የጸሎተ ሃይማኖት አንቀጽ ተወስኗል።*

## 2ኛ ጉባዔ

## የቁስጥንጥያው ጉባዔ በ381 ዓ.ም ተደረገ

- የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት ለካደው በመናፍቁ በቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ በመቅዶንዮስ ምክንያት በታላቁ ቴዎዶስዮስ ዘመን መንግሥት 150 ሊቃውንት በተገኙበት ተካሔደ።
- የጉባዔው መሪ የኢስክንድሪያው ሊቀ ጳጳስ ጢሞቲዎስ ዘአልቦ ጥሪት ነው።
- ሠለስቱ ምዕት ከወሰኑት ከኒቃያው ጉባኤ የሃይማኖት ቀኖና በማያያዝ

---

በዘመኑ አትናቴዎስም የእንስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ዲያቆናት ነበር።



"በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን" ከሚለው ጀምሮ "የሚመጣውን ሕይወት ለዘላለሙ" እስከሚለው የሃይማኖት ቀኖና አንቀጸ ሃይማኖት ተወሰነ።

## 3ኛው ጉባዔ

## የኤፌሶን ጉባዔ በ431 ዓ.ም ተደረገ

የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት በመጠራጠር ሁለት አካል ሁለት ባህርይ አለው ብሎ በተነሳውና የድንግል ማርያምን ወላዲተ አምላክነት፣ በካደው በመናፍቁ በቁስጥንጥንያው ሊቀ ጳጳስ በንስጥሮስ ምክንያቱ ተደረገ።*

- 200 ሊቃውንት ተሰብስበዋል።
- በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቅዱስ ቄርሎስ አማካኝነት ጉባኤው ተመርቶ መናፍቁ ንስጥሮስ ተወግዞ ተለይቷል።

---

* በሃይማኖተ አበው ሠለስቱ ምዕት ኒወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚዕ ማህየዊኖ እስከሚለው የወሰኑ መሆኑን ተገልጿል

* በዘመኑ አትናቴዎስም የእንስክድርያ ቤተ ክርስቲያን ሊቀ ዲያቆናት ነበር።

## 4ኛው ጉባኤ

## የኬልቄዶን ጉባኤ በ451 ዓ.ም ተደረገ

### ጉባኤ ከለባት ይባላል

- ቤተ ክርስቲያናችን አትቀበለውም
- ኬልቄዶናውያን መልካሙንና ቀናውን የ3ቱን ጉባኤዎች የሃይማኖት ቀናና ለማፍረስና የንስጥሮስን ባህል ለማደስ በንጉሡ በመርቅያኖስ ትእዛዝ የተደረገና የተቋቋመ ጉባኤ ነው።
- "ሁለት ባህርይ ሁለት ፈቃድ ሁለት ሥራ" በማለት የሚያስተምሩ መለካውያን ከቤተክርስቲያን ተለዩ
- እውነተኛው የቤተክርስቲያን ቅዱስ አባት ዲዮስቆሮስ በጉባዔው ተገኝቶ የመናፍቁን የልዮንን ደብዳቤ ስህተት በማጋለጡ ተደብድቦ ጥርሶቹ ረግፈው ጽህሙ ተነጭቶ በደሴተ ጋግራ ተጋዘ።

  "ዛቲ ይዕቲ ፍሬ ሐይማኖት" ብሎ ለመንፈስ ቅዱስ ልጆቹ ላከላቸው።*1

*1 ቅዱስ ዲዮስቆሮስ በደሴተ ጋግራ በእሥር ቤት በተወሰደ ጊዜ በአረማውያን ድብደባ የረገፉ ጥርሶቹን ላስተማራቸው ክርስቲያን ወገኖቹ ይህች የሃይማኖት ፍሬ



- የንስጥሮስን ትምህርት የተቀበሉ የልዮን ተከታዮች "ካቶሊክ" ወይም የሁለት ባህርይ እምነት ተከታዮች ተባሉ፤ የጥንቱን የአባቶቻችንን እምነት አንለቅም ያሉት ደግሞ ኦርቶዶክሳውያን ተባሉ። እምነታቸውም የጥንቱን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት የተቀበሉትና የተከተሉት አንድ አካልና አንድ ባህርይ ያሉት ያዕቆባውያን /ኦርቶዶክስ ተዋህዶ/ ተብለዋል።
- በ1054 ዓ.ም መለካውያን /የካቶሊክ እምነት ተከታዮች/ በሥልጣንና በትምህርተ ሃይማኖት ተጣልተው ለሁለት ተከፈሉ።

1. የግሪክ ኦርቶዶክስ መለካውያንና
2. የሮማ ካቶሊክ ተብለው ተለያዩ

## የልዩነታቸው ምክንያት

ካቶሊኮች የቁስጥንጥንያ ጉባኤ ከወሰነው ውጪ ወነእምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚዕ ማህየዊ ዘሠረፀ እምአብ በሚለው ላይ ወእም ወልድ ማለትም መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ ሰረጸ ብለው ስለጨመሩ ይህ አባባል ከመጻህፍት

ነች ብሎ እንደላከላቸው የቤተክርስቲያን ታሪክ ያስተምረናል። እውነትም /ፍሬ

ሐዲሳትም ሆነ ከአበው ቀኖና ሃይማኖት የወጣ አዲስ ባህል በመሆኑ ነው። የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ከካቶሊክ የተለዩት።

## *ፕሮቴስታንትና ክፍፍሎቹ*

### *ከሐድያንና ከሀዲታቸው መናፍቃንና ኑፋቄያቸው*

### *1. ሉተራውያን*

- የፕሮቴስታንት እምነት መስራቹ በ1517 ዓ.ም ከካቶሊክ እምነት የተገነጠለው ጀርመናዊ መነኩሴ ማርቲን ሉተር ነው
- በዘመኑ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥጋዊ ሥራ ተስስፋፍቶ ነበር።
- የኃጢአት ማስተሠረያ ካርድ /......../ መስፋፋት የነበረበት ሠዓትና ጊዜም ነበር።
- የቤሔረተኝነት ስሜትና ሎሎችም ችገሮች ነበሩ

ሃይማኖት/



- ሉተር ይህንን የኃጢአት ማስተስሪያና ሌሎች ችግሮችን ተቃውሞው 95 የክርክር አንቀጾችን የያዘውን ጽሁፍ ዊቲን በርግ ባለው የቤተክርስቲያን ደጃፍ ለጠፈው።

መመሪያውም "መጽሐፍ ቅዱስን ማንም ሰው እንደ ራሱ ፈቃድ መተርጎም ይችላል" የሚል ነበር።

### *ሉተር ማነው?*

- በ1483 ዓ.ም በማዕድን ማውጣት ሥራ ላይ ከተሰማራው አባቱ ከሐንሰንና ከእናቱ ከማርጋሪት ሔድነሪ ጀርመን ውስጥ አይስከን ከተማ ተወለደ።
- ወላጆቹን ጠይቆ ወደ ኤርፋትት /ዩኒቨርስቲው/ ሲመለስ ከመንገድ ላይ አደገኛ አውሎ ነፋስ ሲያንገላታው የሚሞት መስሎት ከዚህ ብታተርፈኝ ቀሪ ሕይወቴን አምላኬን በምንኩስና አገለግላለሁ በቅድስናም እኖራለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶ መነኮሰ /በ1505 አውግስቲንያን ገዳም/
- በ1520 ፓፓው አወገዘው እርሱም መለየቱን አበሰረ።

- በ1521 በንጉሥ ፓርልክ /እስፓኝ/ ሞት ተፈርዶበት ለ1 ዓመት ያህል ስሙን ለውጦ ጆርጅ ተብሎ ተደብቆ ኖረ።
- በ1525 ለጀርመን ገበሬዎች በመቆም ፈንታ ለልዑላን ኃያላን ቆሞ ገበሬው ካላረፈ በሠይፍ ቆራርጡት በሎ አዘዘ
- በ1517 በምንኩስና መኖሩን ባለመፈለጉ ቆቡን አውልቆ በሴት ገዳም ያለችውን ማርጋሪት የተባችውን መነኩሲት አግብቶ ምንኩስናውን አፈረሰ
- በ1546 ሞተ "ሞቱ ለሐጥዕ ፀዋግ" እንዲሉ በክፉ አሟሟት ሞተ። ዛሬም ተከታይ ልጆቹ የቅድስናን ኑሮ ሲቃወሙ እናያቸዋለን።

## 2. *<u>አናባፕቲስቶች /ዳግም አጥማቂዎች/</u>*

## *<u>(Anna-Baptists)</u>*

- በ1525 ዓ.ም በኮንራድ ግወቤልና በፈልናስ ማንዝ መሪነት የተሰበከው የአናባፕቲስቶች ትምህርት ስዊዘርላንድ ውስጥ በዙሪክ አካባቢ እየተስፋፋ ሔደ።



- በመጀመሪያ ሉተር ወጥ መንገድ የሚፈጽምባቸውን ቅጣት ተቃውሞ ነበር። ነገር ግን በ1530 ዓ.ም ንቅናቄአቸውን በሠይፍ እንዲገልጡ አዘዘ።

ሀ. ሚኖ ሲሞንስ በ1559 ኔዘርላንድ ውስጥ ሚኖናይትን /ሚኖናውውያንን መሠረተ። /Mennonites/

ለ. ጃኮብ ሉተር እስትርያ ውስጥ ሉተራይት /ሉተራውያንን/ መሠረተ ተከታዮቻቸው የግል ሐብትን ይቃወማሉ። እምነታቸውን በተግባር ለመግለጽ በሚያደርጉት ሐሴትና ፈንጠዝያ በመገፋፋት አንዳንድ ጊዜ ሕገ ወጥ ተግባሮችን ፈጽመዋል።

- ሚኖናይቶች በ1924 ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሞክረው አልተሳካላቸውም በኋላ በ1938 ናዝሬት ከተማ ገብተው ኃ/ማርያም ማሞን ሆስፒታል አቋቋሙ። ዛሬ <u>መሠረተ ክርስቶስ</u> ይባላሉ።

## 3. *<u>ካልቪኒዝም /Calvinism/</u>*

- መሥራቹ የፈረንሣይ ተወላጅ ጆን ካልቪን /1509-1564 ዓ.ም/

- በመጀመሪያ ዝዊንግል /ሪፎርምድ ቸርችን/ በ1518 ጀመረ
- በ1522 ዓ.ም በዙሪክ ተደራጀ
- በ1581 ዓ.ም ሲዋጋ በጦርነት ሞተ
- ካሊቪኒስቶች በአውሮፖ "ሪፎርምድ ቸርች" ሲባሉ በእንግሊዝና በአሜሪካ "ፕሪስባይቴሪያን" ይባላሉ።
- በ1531 ካቪን ተተካ
- ትምህርቱን ሰምተው በማይፈጽሙት ላይ ውግዘትና የቅጣት ሕግንም አወጣ።
- ማንኛውም ሰው ለጽድቅም ሆነ ለዘላለማዊ ቅጣት አስቀድሞ ተወስኗል ብለው ያምናሉ።
- በ1910 ወደ ኢትዮጵያ ገባ

## 4. <u>*አንግሊካን*</u> /*Annglican*/

- በንጉሥ ሔኔሪ 8ኛ በቀጥታ የተደረገ ለውጥ ነው።
- በጋብቻው ምክንያት በ1532 ከካቶሊክ ተገነጠለ።
- በ1533 ዓ.ም አዲስ ጳጳስ ሾመ። ሌላም ሚስት አገባ፤ ዝሙት!!



- በ1534 ዓ.ም የተቃወሙትን እየሰየፈ ያስፈራራቸው ጀመር
- ሔኔሪ በ1547 ዓ.ም ከሞተ በኋላ አምነታቸው ተደበላለቀ

## 5. <u>*ሜቶዲስት*</u> /*Methodist*/

- በ1784ዓ.ም ከእንግሊዝ ቸርች ተገንጥለው በአሜሪካ ሚቶዲስት ቸርች ተብለው ተቋቋሙ።
- ጆን ሚስሊይ፣ ቻርለስ ዌርለስ፣ ዌስሌይና ጆርጅ ዘዋይት የተባሉ ሰዎች ናቸው መሥራቾቹ።
- ሥርዓትና ዘዴ የሚል መጽሐፍ ጽፈው ስለነበር ሜቶዲስት ተባሉ።

*የቤተክርስቲያንን ሥርዓትና ትውፊት የሚቃወሙ ናቸው።*

## 6. <u>*ጴንጤዎች*</u> /*Pete- Coastal*/

- በአሜሪካ ቶኪኮ በተባለው ሥፍራ በ1991 ዓ.ም ቻርለስ ፖርሃም በተባለ ሜቶዲስት ቄስ ተመሠረተ
- በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ሞንታንየስ የተባለው መናፍቅ ተከታዮች ናቸው።

- ሞንታንየስ ከልጆቹና ከተከታዮች ጋር በመሆን በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ፣ በልሣን እናገራለሁ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተሻለና የላቀ ራዕይ ተሰጥቶኛል ይል ነበር።
- የዛሬዎቹም ጴንጤዎች ክፍፍሉ'ሽ ቢኖራቸውም ትምህርታቸው የሞንታንየስ በመሆኑ ምንታኒስት ይባላሉ። ሁለቱ ዋና ዋና ክፍሎቻቸውም ከዚህ የሚከተለው ነው።

## ሀ. <u>ዩኒተርያሊዝም ወይም ኢየሱስ ብቻ የሚባሉት ናቸው</u> /Only Jesus/

-ትምህርታቸው እንደመናፍቁ እንደ ሰባልዮስ ነው።

-በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁት ሁሉ እንደገና በኢየሱስ ስም መጠበቅ አለባቸው ይላሉ።

-ፀረ ሥላሴ ናቸው። በሥላሴ አያምኑም፤ ወይም አንድነት ሦስትነትን አይቀበሉም።

-ዋንስ ቸርች ተብለውም ይጠራሉ*

* Only Jesus ኢየሱስ ብቻ በማለት አብና መንፈስ ቅዱስን ለያይተው የሚክዱ ናቸው።



-በመቀሌ በኩል የገባውና በኢትዮጵያ ያለው ቅርንጫፋቸው <u>የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን</u> ይባላል።

## ለ. <u>ትሪኒቴሪያን /Triterian/</u>

በሥላሴ እናምናለን ካሉ በኋላ ክርስቶስን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ አሳንሰው ይመለከቱታል። 26 ቅርንጫሮች ሲኖራቸው ከእነዚህም መካከል <u>"አሴምብልስ ኦፍ ጎድ፣(Assembles of God) ቸርች ኦፍ ጎድ ኢን ክርይስት፣ /Church of God in Crist)</u> <u>ዩናይትድ ፔንቴክስታል ቸርች United Pent-Costal Church etc.</u> ወዘተ ይገኙበታል። በኢትዮጵያም፣ <u>ሙሉ ወንጌል፣</u> <u>መሠረተ ክርስቶስና ቤተል፣</u> የመሳሰሉ ቅርንጫፎች በመባል ይጠራሉ።

## *8. <u>የይሆዋ ምስክሮች /Jehauea Witness/</u>*

- የይሆዋ ምስክሮች ማኅበር በአሜሪካን አገር ፔንሲልቫኒያ በተባለው አውራጃ በ1872 ዓ.ም ቻርልክስ ቴይዝራበል በተባለ ሰው ተመሠረተ
- ኑፋቄአቸውን ለማሠራጨት ጋዜጦችና መጽሄቶችን ያስራጫሉ ከእነዚህም ውስጥ:-

ሀ. በምድር ለዘለዓለም እንኑር የሚሉ ጽሁፎች
ለ. መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት ታወቁ
የሚሉ ጽሁፎች ይገኙበታል።

- በ1884 ዓ.ም የራሳቸውን ትምህርት ለማስፋፋት የሚጠቅማቸውን መጽሐፍ ቅዱስ አሳተሙ
- በዚህ መጽሐፍ ብዙ ጥቅሶችን ለውጠዋል /ለምሳሌ ዮሐ. 1÷1፣ ቆላሲ. 1÷15-17፣ ራዕ. 2÷6፣ ቲቶ. 2÷13፣ 2ኛ ጴጥ 1÷1፣ ራዕ 3÷14
- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በ236 ቦታ ላይም "በእግዚአብሄር" "ፈንታ" "ይሆዋ" የሚለውን ቃል ተክተዋል።
- ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ የራሳቸወን መጽሐፍት አክብረው ይቀበላሉ።
- ትምህርታቸው የአርዮስ ትምህርት ሲሆን እነርሱም በቤተክርስቲያን አነጋገር አርዮሳውያን ይባላሉ /Arianism/



## ቻትልስ ራስል ማን ነው?

- በመጀመሪያ የፕሪስባይቴሪያን ተከታይ የነበረና በኋላም ከንግሪጌሽናል ቸርች የገባ። በኋላም ተመልሶ ኢ-አማኒ /Pagon/ ሆነ። እንደገናም እምነቱን በመለወጥ የአድቬንቲስት ዕምነት ተከታይ ሆነ።
- የክርስቶስ አመጣጡ በማይታይና በመንፈሣዊ አካል ነው እንጂ በክበበ ትስብዕት አይደለም በማለት ከአድቬንቲስት ተገነጠለ።
- ተከታዮች በቅድስት ሥላሴ አንድነትና ሶስትነትን በክርስቶስ የባህርይ አምላክነት አያምኑም።
- መሬት ለወደፊት ገነት ትሆናለች፤ ዘላለማዊት ስለሆነች አታልፍምና፤ ክርስቶስ ምድራዊ ንጉሥ ነው፤ በመሬትም ላይ ይነግሳል፤ መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱት 144,000 የጌታ ታማኖች ብቻ ናቸው ብለው ያምናሉ። የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሷት አስበው ይሆን? እንጃ! እንደነርሱ አባባል በክርስቶስ ደም ከዘላዓለም ሞት ነፃ የወጣ ሁሉ የገሃነም እሳት ተቀጪ መሆኑ ነዋ! ወይ ክህደት?

- በ1914 ክርስቶስ ወደ መቅደሱ ገብቶ መግዛት ይጀምራል የጥፋት ጊዜም 1914 ነው ብለው ነበር፤ አልተሳካላቸውም እንጂ! ትንቢታቸውም ሐሰት በመሆኑ።

እስከ ዛሬ ክርስቶስ በምድር ላይ ለመንገስ አልመጣም አሁንም በምድር ሊነግሥ አይመጣም ሰማያዊ ሥልጣን አምላክነትና ጌትነት የማን ሆኖ? ክብር ይግባና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ የሚመጣው ለፍርድ ነው።

- እንደገናም በ1975 ምፅአት ነው ቢሉም ከሸፈባቸው።
- በሕክምና ደም መስጠትንና፣ ለሀገር መዋጋትን፣ ለምድራዊ መንግሥት መገዛትንና፣ የአንድ ሃገር መለያ የሆነውን የነፃነት ምልክትን ባንዲራን ማክበርን ይቃወማሉ። ምክንያቱም የሃይማኖት ሰዎች ሥላልሆኑ የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የወንድም /የወገን ፍቅር/፣ የሃገር ፍቅር የሌላቸው ሥለሆኑ ማንነታቸውን በሥራቸው እየገለፁት ይገኛሉና እናስተውል።



- በአለም አብያተ ክርስቲያናት ህብረትም አባል አይደሉም /W.C.C./ (*) ምንም እንኳን መነሻው መጽሐፍ ቅዱስ ቢሆንም ትምህርታቸው ክህደት ስለሆነ ፀረ ክርስቶስ በመባል ይታወቃሉ።

8ኛ. ሰባልዮስ:- የተባለው መናፍቅ ደግሞ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት በመቃወም እንዲህ አለ። አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ ገፅ ናቸው እንጂ ሦስት አይደሉም ምክንያቱም አለ። እግዚአብሔር በዘመነ አበው አብ በመባል ሲታወቅ፤ በዘመነ ሥጋዌ ደግሞ ወልድ ተብሎ መጣ፤ ቀጥሎም በዘመነ ሐዋርያት መንፈቅ ቅዱስ ተባለ እንጂ ያው አንድ አምላክ አንድ ገፅ ነው። በማለት ክህደቱን አስተላልፎ አናገኘዋለን።

እኛ ግን አባቶቻችን ሐዋርያት እንዳስተማሩን ሥላሴን በስም በግብር መአካል ሦስት ስንል በመለኮት በአገዛዝ በሥልጣን አንድ አምላክ ብለን እናምናለን። ሠለስቱ

(*) world Church Council

ምዕትም "ይሄለሱ በአካላት ወይትዋሃዱ በመለኮት" በማለት አስተምረውናል"[2]

9. <u>ፎጢኖስ:-</u> እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ታወቀ እንጂ ቀድሞ ከአብ ዘንድ የለም በማለት "ለሬ እማርያም ከዋኔሁ" ብሎ ልጅን ከአባቱ ከአብ፣ ከግህየዊ ህይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ፣ ለይቶ የተናገረ ሲሆን እኛ ግን በመንፈስ ቅዱስ መምህርነት ምስጢርን ከተርጉሙ ጠንቅቀው ያሳወቁን አበው እንዳስተማሩን ለአይን ጥቅሻ ያህል እንኳ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የተለያዩበት ጊዜና ሠዓት እንደሌለ ስናምን፤ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመናት ከመቆጠራቸው፣ ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር ከመምጣቷ አስቀድሞ የነበረ ዛሬም ያለ ለዘለዓለምም የሚኖር ፍፃሜ የሌለው አምላክ መሆኑን እናምናለን። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው "ኢየሱስ ክርስቶስ ዘትማልም ወዮም ወከመ ውዕቱ እስከ ለዓለም"* እንዲሁም ከዓለም መፈጠር በኋላም ከእመቤታችን ከቅድስት

[2] ፀሎተ ሃይማኖት ወይም የሃይማኖት ፀሎት በደረሱት አንቀፅ ውስጥ ተመልከት
* ዕብራውያን ምዕ. 13÷8 ተመልከት



ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ በተዋህዶ ከበረ ብለን እናምናለን።

ክብር ይግባውና ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ቀዳማዊነቱ ሲናገር "እምቅድመ ይትወለድ አብርሃም ሃሎኩ አነ" ብሎ አስተምሮናል።[3]

10ኛ. <u>አርሱሳውያን</u>:- በመባል የሚታወቁት የአርሲስ ወገኖች ደግሞ አካላዊ ቃል ሲኦል የወረደው በነፍስና በሥጋው ነው ብለዋል። ፍፁም ክህደት! እኛ ግን አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ነፍስ ሲኦል ወረደ፤ በአካለ ሥጋ በዮሴፍና በኒቆዲሞስ ተገንዞ ወደ መቃብር ወረደ፤ ያም ሥጋ ከመለኮት ሳይለይ ከነፍስ ብቻ ተለይቶ እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ በዚያ በመቃብር ውስጥ ሰነበተ። በዚያም ሙስና መቃብርን አጠፋልን መለኮትም ከነፍስም ከሥጋም ሳይለይ በአካለ ነፍስ ሲኦል ወረደ በሲኦል ያሉትን ነፍሳት ነፃ ያወጣ ዘንድ። በመሆኑም በባህርዩ ምሉዕ በኩለሄ እንደመሆኑ ምንም እንኳ በከርሰ መቃብር ቢያድርም በዕርሃ አርያም በአብ ዕቅፍ በዘባነ ኪሩብ ነበረ፤ አለ፤ ይኖራልም፤ ብለን

[3] ዮሐ. 8÷59

እናምናለን። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም ድርሳነ ቶማስን ሲተረጉም እንዲህ አለ "አንተ ውዕቱ አምላክ ዘበአማን ወአንተ ውዕቱ ፍፁም ሰብዕ አንተ ውዕቱ ዘትነብር ውስተ አርያም ዲበ መንበረ ስብሃቲከ ወአንተ ዲበ ዕፀ መስቀል" በማለት ገልፆታል።

11ኛ. <u>አውጣኪ:-</u> የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ እንደ አዳም ወገኖች ሥጋ የሚራብ የሚጠማ፣ የሚደክም አይደለም ብሎ ክህደትን ሲያስተላልፍ እንሰማለን። ነገር ግን እኛ የምናምነው መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሰው በመሆኑ በለበሰው ሥጋ ተራበ፣ ተጠማ፣ ደከመ፣ ታመመ፣ ሞተ፣ ተቀበረ ስንል በመለኮታዊ ባህርዩ ግን ይህ ሁሉ እንደሌለበት እናምናለን። ቅዱስ ጴጥሮስም "ሞተ በሥጋ ወሃይወ በመንፈስ" በማለት አስተምሮናል።(*)4)

12. <u>መንክዮን:-</u> የክርስቶስ ሥጋ እውነተኛ የሠው ሥጋ ሳይሆን ምትሐት ነው። በማለት የሥጋዌን ምስጢር ይቃወም [illegible] የን ግን የክርስቶስ ሥጋ ከእኛ



ባህርየ ሥጋ ያልተለየ ከራስ ጠጉር እስከ እግር ጠፍር ድርስ አዳማዊ አካል ያለው ሲሆን ነባቢት ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ያለችው ፍፁም ሰው ፍጹም አምላክ ነው እንጂ ምትሐት ነው አንልም። እርሱ ራሱ መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተጠራሩት እንዲህ አለ "ስለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይወጣል ይወርዳል? እኔ ራሴ እንደሆንኩ እጆቼንና እግሮቼን እዩ በእኔ እንደምታዩት ለመንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሳችሁ እዩ...... ብሎ እግሮቹንና እጆቹን አሳያቸው"።(*)5)

13ኛ. <u>አርጌንስ:-</u> የሥላሴን ባህርይ የሚያበላልጥ ሲሆን ወልድ ከአብ ያንሳል አብን በስልጣን በክብር አይተካከልም፤ መንፈስ ቅዱስም ከወልድ ያንሳል በህልውናው አንድነት የለውም፤ ብሎ ሲክድ እኛ ግን በሥላሴ ዘንድ መብለጥ መበላለጥ የሌም አንድነታቸው ሦስተነታቸውን ሳይጠቀልለው ሦስትነታቸው አንድነታቸውን ሳይለያየው ዕሩያን ናቸው እንላለን።

አባ ሀርያቆስም በቅዳሴው እንዲህ አለ:-

---

(*)5) ሉቃ 24÷38-42

"አብርሃም ከይስሐቅ እንደሚበልጥ ይስሐቅም ከያዕቆብ እንደሚበልጥ ለመለኮት እንዲህ አይደለም፤ አባት በመሆን አብ ልጁን አይበልጠውም ወልድም ልጅ በመሆን ከአብ አያንስም መንፈስ ቅዱስም ትክክል ነው" (*)6) በማለት አሪናቸውን ብሩህ አድርጎ ገልያቻል።

14ኛ. <u>እስማኤላውያን:-</u> ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ሕይደለም። ምክንያቱም አላህ አይወርድም አይወለድምና በመስቀልም የተሰቀለ እርሱ ሳይሆን አምሳያውን በመስቀል እንዲሰቀል አደረገው በማለት ሲናገሩ እንሰማለን።* እኛ ግን ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ባህርየ መለኮቱ የማይለወጥ የባህርይ አምላክ እንደሆነ ስናምን በመስቀል የተሰቀለውም ብዙዎችን (አዳምንና ልጆቹን) ለመታደግ የእኛን ርግማን ለመደምሰስ እንደሆነ ሁሉ፤ በሊቀ ካህናቱ ባሪያ እጅ በጥፊ የተመታው፣ በጲላጦስ አደባባይ የተገረፈው፣ በለንጊኖስ ሐራዊ ጦር ጎኑን የተወጋው፣ መድሃኒታችን ኢየሱስ

---

(*)6) ቅዳሴ ማርያምን ተመልከት

* የእስልምና እምነት ተከታዮች በሌላ አነጋገራቸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አይደለም ወይም የአብ የባህርይ ልጅ አይደለም በማለት ለሠማይ ደጅ ለእግዚአብሄር ልጅ የለውም ብለው ሲናገሩ እንሰማቸዋለን።



ክርስቶስ ነው እንጂ አምሳያው አይደለም ብለን እናምናለን እናሳምናለን።

15. <u>ሞርሞናውያን /Mormons/</u>:-

- በ1831 ዓ.ም በጆሴፍ ስሚዝ አማካይነት የተመሠረቱ ሲሆን፤
- እግዚአብሔር እንደኛ ሰው ነበር ሰውም እግዚአብሔር መሆን ይችላል ባዮች ናቸው። /ፍጹም ክህደት/
- ሰው ሳይጠመቅ ከሞተ በድኑን ያጠምቁታል
- መጽሐፍ ቅዱስንም በመተው የራሳቸውን መጽሐፍ The Book of Mormon የሚል መጽሐፍ አዘጋጅተዋል
- ከደረታቸው ላይ ብራዘርስ የሚለውን ለጥፈው ያዞራሉ። መለያቸው መሆኑ ነው።

ባጠቃላይ የተዳኛችሁ አርቶዶክስያውያን ወገኖቼ የመጨረሻ መልዕክቴም:-

እነዚህ ሁሉ መናፍቃን ከእውነተኛይቱና ከሐዋርያዊቷ ቤተ ክርስቲያን ተለዩ። እንደየሥጋ ፍላጎታቸውም በየራሳቸው መንገድ ተጓዙ። ዛሬም የእነርሱ የግብር ልጆች በተለያዩ ዘዴዎች የዋሃን ምእመናንን እያሳሳቱ ከእውነተኛው

እምነታቸው እየለዩአቸው ነው። ይህም አዲስ እንዳልሆነ ከላይ የተገለጸውን መሠረታቸው መመልከት ይቻላል። ስለዚህ ይህ ለምን ሆነ ብሎ ከመጨነቅና የጥፋት ተልእኮአቸው መሣሪያ ከመሆን ራሥን መጠበቅ ይገባል። መጨረሻቸው ጥፋት ነውና።

ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በወንጌል ሲያስተምር ተውአቸው እስከመከር ድረስ አብረው ይደጉ በመከርም ጊዜ አጫጆችን እልካለሁ በማለት ስለስንዴውና ስለ እንክርዳዱ ለቅዱሳን ሐዋርያት አምላካዊ ቃሉን የስተላለፈ ሲሆን ምሥጢሩም እንክርዳድ የተባሉ መናፍቃን እንደሆኑ አበክሮ ገልጾታል።*

* ወንጌለ ማቴዎስ ምዕ. 13÷24-31 ያለውን ተመልከት።



# ክፍል ፬ (አራት)

ሃሌ ሉያ! ዘበእንቲአሃ ለቤተ ክርስቲያን ተፀፋእከ

በውስተ አውድ ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር።

በክቡር በክርስቶስ ደም የተመሰረተች ራሷ ጉልላቷ፣ በሯ፣ ማዕዘኗ ክርስቶስ የሆነላት ንፅህት እና ቅድስት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ትባላለች። ስለ ቤተክርስቲያን ስናነሳ ብዙ ምስጢራቷን እንድንመራመር ግድ ነው። ምክንቱም ቤተክርስቲያን ለምዕመናን ሁሉ የዘለዓለም የክብር ቤት፣ የነገሥታት የክብር ድንኳን፣ ለፃድቃን ሽልማት፣ የሠማዕታት አክሊል ጌጥ በመሆኗ ነው። በመሆኑም የሠማያዊት ኢየሩሳሌም ምሳሌ ሆና ለዘለዓለም ትኖራለች እስኪ ስለ ቤተክርስቲያን በጥቂቱ እንመልከት:-

## ቤተ ክርስቲያን ማለት

1ኛ. በክርስቶስ ስም አምነው በጥምቀት ልጅነት ያገኙ ክርስቲያን የተባሉ ምዕመናን በህብረት የሚጠሩበት በቅዱስ

መጽሐፍም በጉልህ የሚታዩ የምዕመናንና የምዕመናት ስያሜ ነው።[1]

<u>ማስረጃ</u>:- ማቴ 16÷16-20፣ የሐ.ሥ. 5÷11፣
የሐ.ሥ. 20÷28፣ ኤፌ 5÷23-33

2ኛ ክርስቶሳውያን የተባሉ ክርስቲያኖች በማህበር ሆነው ሥርዓተ አምልኮትን የሚፈጽሙባት ልዑል እግዚአብሔርን በፀሎት የሚገናኙባት፣ ምህረትንና ይቅርታን ለማግኘት አምላካቸውን የሚማፀኑባት፣ በንስሐ ውስጥ በመመላለስ ክቡር ሥጋውንና ቅዱስ ደሙን የሚቀበሉባት መካነ ቅዱሳን የምትባል የፀሎት ቤት ስትሆን፤ ነዳያን የእለት ጉርስ የዓመት ልብስ ለማግኘት ደጅ የሚፀኑባት ህዙናን ከሀዘናቸው ለመፅናናት የሚሰበሰቡባት ባጠቃላይ "ምስካየ ሕዙናን" የምትባል ምሳሌዋ የምስክር ድንኳን የሆነች የድህነት ቤት ናት። [2]

የአማናዊቷ ቤተክርስቲያን ትክክለኛ ትርጉም የሚገኘው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ መሆኑ ቢታወቅም

(1) ማቴ 16÷16-20 የሐ.ሥ. 5÷11 የሐ.ሥ. 20÷28 ኤፌ 5÷23-33
(2) የሐ.ሥ. 2÷46 መፅ. ዜና.መዋ. ክልዕ 7÷11



የወንጌል አምሳልና መርገፍ በሆነችው በአራት በጉልህ በለ ቤተክርስቲያን የሚናገሩትን ምሳሌዎች ከዚህ በመቀጠል እንመለከታለን።

ይሁንና ቤተክርስቲያን ሥርዓት አምልኮ የሚፈጸምባት እግዚአብሔርና ሰው የሚገናኙበት መላዕክት ለተልዕኮ የሚወጡባት የሚወርዱባት ናት። ካልን ዘንድ ሥርዓተ አምልኮና ስብሐተ እግዚአብሔር መቸ ተጀመረ ማለታችን አይቀርም።

ዘበ እንቲአሃም ስንል ምዕመናንን ትቀድስ ታነፃ ዘንድ በአደባባይ መከራ ተቀበልክ ማለት እንደሆነ እንረዳለን አባታችን ቅዱስ ያሬድም በድጓው የዘመረው ይኼንኑ ነው።

## <u>ሥርዓተ አምልኮት መቼ ተጀመረ?</u>

ሥርዓተ አምልኮ የተጀመረው እግዚአብሔር ፍጥረቱን አምሀበ አልቦ አበቦ ከፈጠረ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን እንረዳለን። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ለተልዕኮም የሚፋጠኑ ቅዱሳን መላዕክት ከተፈጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ ፈጣሪያቸውን በማመስገን አምልኮአቸውን

በመግለጻቸው አምልኮተ እግዚአብሔር በአለመ መላዕክት ተጀመረ ማለት ነው።[3]

በአርአያ እግዚአብሔር የተፈጠረውም ክቡር የሆነው የሠው ልጅ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ለፈጣሪው ይገዛ ነበር። በመሆኑም ከመጀመሪያው ሠው ከአዳም በመቀጠልም ልጆቹ ከአባታቸው ባገኙት መንፈሳዊ የአምልኮት ውርስ መሠረት ለአምልኮአቸው መግለጫ የሆነ የተቀደሰ መስዋዕት አቅርበዋል። በመጀመሪያም መስዋዕት ያቀረቡት እነማን እንዴት እንዳቀረቡት በመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን።[4] እስከ ዚሀ ድረስ ሥርዓተ አምልኮትን ከተመለከትን የአማናቷን ቤተክርስቲን ምሳሌዎች የሆኑትን የብሉይ ኪዳንን አምልኮተ እግዚአብሔር መፈጸሚያዎች እንመለከታለን። ምስጢራ ቸውንም በሥፋት እንመረምራለን።

(3) ኩፋሌ 2÷6-8 ኢሳ. 6÷3-5

(4) ዘፍ 4÷3-6, ኩፋሌ 3÷9, ኩፋሌ 5÷1



## በብሉይ ኪዳን የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች

### 1ኛ. ሐመረ-ኖህ /የኖህ መርከብ

/ The Ark of Noah/

የሠው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ በሄዱ ጊዜ እግዚአብሔር አምላካቸውን በሃጢአታቸው፣ በበደላቸው፣ በስህተታቸው፣ አሳዘኑት። በዚህን ጊዜም የእግዚአብሔር ባለሟል አይጠፋምና አንድ ኖህ ፃድቅ አባት ተገኘ። እርሱም በህገ እግዚአብሔር የሚ መራ ህግ ሳይሰጠው ፈጣሪውን በህገ ልቡና አውቆ በቅድስና የሚኖር ታማኝ የአምላክ ባለሟል ነው።

በመሆኑም ሰዎች በሃጢአታቸው ምክንያት በንፍር ውሃ[5] ሲደመሰሱ ፃድቁ ኖህ ግን ስምንት የሚሆኑ ቤተሰቡን ከርሱ ጋር ይዞ ወደ መርከብ እንዲገባ ከእግዚአብሔር ታዘዘ። ለፍጥረቱ አዛኝ የሆነው አምላክ ከፍጥረታቱ ሁሉም እንዳይጠፉ ከእንስሳት፣ ከአራዊት፣ ከአዕዋፍ

(5) ማየ አይኅ /የጥፋት ውሃ/

እንደየወገናቸው ከጥፋት እንዲደኑ ከኖህ ጋር በመርከብ ገብተዋል። በመሆኑም

የኖህ መርከብ የእግዚአብሔር ሰዎች ከጥፋት የዳኑባት ስትሆን በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖችም ከሞተ ነፍስ፣ ከባህረ እሳት፣ ከግብርናተ ዲያቢሎስ የምታድን የአማናዊቷ ቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት።[6]

## 2ኛ. ክህነተ መልከጼዴቅ

/king of Salem Priest to God/

መልከጼዴቅ የሣሌም ንጉሥ የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌና የልዑል እግዚአብሔር ካህን በመባል የሚታወቅ ታላቅ አባት ነው። ይህ ታላቅ ካህን የብዙዎች አባት የተባለ ክቡር አባታችን አብርሃምን ባገኘው ጊዜ ሕብስትና ወይን አቅርቦ አብርሃምን ባርኮታል። አብርሃምም ለዚህ ለታላቅ ካህን ከአለው ሁሉ አሥራትን አበርክቶለታል።[7]

(6) ዘፍ. 6÷122
7÷1-ፍ.
8÷1-ፍ.
(7) ዘፍ. 14÷18



ምሳሌውንም ስንመራመር ካህኑ መልከጼዴቅ የሊቀ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን ለአብርሃም ያቀረበው ህብስትና ወይንም መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለብዙዎች ድህነት በቀራንዮ መስቀል የቆረሰው ሥጋና ያፈሰሰው ደም ምሳሌ ከመሆኑም በላይ ዛሬ ካህናት በቤተክርስቲያን አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፤ አሐዱ ውዕቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው አክብረው ቀድሰው የሚሰጡን የቅዱስ ቁርባን ምሳሌ ነው። [8] ይህም አማናዊ መስዋዕት ሆኖ እስከ ዕለተ ምጽአት ስንሰዋውና ስንድንበት እንደምንኖር እናምናለን። [9]

## 3ኛ. ቤተ ኤል /ቤቴል/ [10]

(This is the gate of Heaven)

አባታችን ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ እግዚአብሔርን ያየባት እንዲሁም ቅዱሳን መላዕክት ሲወጡባት ሲወርዱባይ ያያት የብርሃን መሠላል የተተከለባት በላይዋም ልዑል

(8) ሥርዓተ ቅዳሴ /ቁጥር 18/
(9) መዝ. 109/110/1÷4 ዕብ 7÷1-28
(10) ቤት-ኤል የሚለው ቃል በእብራይስ ሲሆን ቤት ማለት ማደሪያ ሲሆን ኤል ማለት እግዚአብሔረ ማለት ነው። ትርጉሙም ቤትኤል ማለት የእግዚአብሔር ማደሪያ ማለት ነው።

እግዚአብሔር የተቀመጠባት ስትሆን ምሳሌነቷም ዛሬ መልዕክተ እግዚአብሔር የምዕመናንን ፀሎትና የካህናትን መስዋዕት ይዘው፤ የታጠነውንም እጣን ወደ ሥሉስ ቅዱስ መንበር የሚያሳርጉባት ከመሆኗም በላይ የእግዚአብሔርን ቸርነት፤ በረከት ይቅርታ የሚያመጡባት ምዕመናንን በረድኤተ እግዚአብሔር የሚጠብቁባት ለሙታን ነፍሳት ይቅርታ የሚለመንባት ልዑል እግዚአብሔር በፍቅር የሚገለጽባት ቤት በመሆን ትታወቃለች ቤተክርስቲያን[11] ይህች የሠማይ ደጅ ናት እንዳለ ያዕቆብ።

## 4ኛ. ምኩራብ /ሲናጎግ/

ምኩራብ ማለት የአይሁድ የፀሎት ቤተ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን የአይሁድ አምልኮ በኢየሩሳሌም በነበረው ቤተመወቅደስ እንደ ሥርዓቱ የተመሠረተ ነበር። ይሁን እንጂ በዚሁ መቀጠል አልቻለም። ምክንያቱም ሃይማኖት የሚያጠፋ ቤተ መቅደስ የሚያፈርስና የሚያቃጥል አረማዊ ንጉሥ ተነሳ።

(11) ዘፍ. 28÷10
ዘፍ. 23÷25



አረማሪው ንጉሥ ናቡከደነጾር ቤተ መቅደሱን አፍርሶ ሕዝበ እሥራኤልን ወደ ባቢሎን አፍልሶ ስለነበር ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አይሁዶች በሚገኙባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ለፀሎት እና በማህበር ለማመስገን ቤቶችን ሊሠሩ እንደጀመሩ ይነገርላቸዋል።[16]

በምኩራቦችም የብሉይ ኪዳን መምለክያን አምልኮታቸውን ይፈጽሙ ስለነበርና ምኩራቦቻቸውም ብዙ ስለነበሩ ጌታችን መደሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋዌ ምስጢር ተገልፆ በተዋህዶ ከብሮ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜም ተከታዮቹን ሐዋርያርን እየላከ በምኩራቦቻቸው ያስተምራቸው ነበር።[17] በብሉይ ኪዳን ታሪክ እና በአይሁዳውያን ህግ አሥር የሚያህሉ ወንዶች በአንድ ማህበር ቢገኙ ምኩራብ ለመሥራት ይፈቀድላቸዋል። እንዲሁም በሚያንጹት ምኩራብ ውስጥ ሕግና ነበያት የተፃፉባቸው የብራና[18] ጥቅልሎች በአንድ ሳጥን ወይም

(16) ሕዝ. 11÷16
(17) ማቴ. 4÷23 የሐ.ሥ. 6÷9 13÷5 14÷1 17÷16-18
(18) Skroil / የብራና ጥቅልሎች/

ማህደር ውስጥ ይቀመጣሉ። /ፅላት በታቦት ዳዊት በማህደር እንደሚቀመጥ/

ምኩራብ እንደ ደብተራ ኦሪት ሁሉ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ህንፃ ነው። ምኩራብ የተመሠረተው ከልደተ ክርስቶስ በፊት ነበር።

ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔርን መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመሥራት ብዙ ጊዜ ቢመኝም ቤተ መቅደስ የሚሰራው ከአብራኩ በሚከፈለው ልጁ ሠሎሞን እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ስለነበር በሠሎሞን ንጉስ እሥራኤል /ወልደ ዳዊት/ ተሠርታለች።

ሠሎሞንም እግዚአብሔር ፈቅዶለት ቤተ መቅደሱን በአማረና በተዋበ አሠራር ካነጸ በኋላ ሰሎሞንና ካህናተ ኦሪት ለበዙ ዘመናት በደብተራ ኦሪት /ድንኳን/ ትኖር የነበረች ታቦት ከዳዊት ከተማ ከፅዮን አምጥተው ወደ ምኩራቡ አስገቧት። ከዚየን ጊዜ ጀምሮ መንፈሳዊ አገልግሎቷን በመቀጠል የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ በመባል መጠራት ጀምራለች።(19)

(19) ካል. ሳሙ. 7÷1 ቀዳ.ነገሥ 5÷3-17 ቀዳ.ዜና መዋ. 17÷1-14



## 4ኛ. <u>ደብረ ሲና /The Mauntain of God/</u>

ደብረ ሲና ማለት የሲና ተራራ ማለት ነው።

ሊቀ ነበያት ሙሴ 40 ቀንና 40ሌሊት በፆም በፀሎት ተወስኖ ሕገ እግዚአብሔርን (የቃልኪዳኑን) ፅላት ከእግዚአብሔር የተቀበለባት ለእስራኤል ዘሥጋ ህግ የሠራባት ሐመልማል ከነበልባል ጋር ተዋህዶ ሃመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ነበልባሉ ሀመልማሉን ሳያቃጥለው ምስጢረ ተዋህዶን ያየባት እንደሆነች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም በፆም በፀሎት ተወስነው ህገ እግዚአብሔርን ለጠበቁ እስራኤል የሥጋ ያይደለ የነፍስን ክብር የምታሰጥ በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው "ውሉደ እግዚአብሔር" የተባሉ ርስተ መንግሥተ ሰማያትን የሚወርሱባት ሃብተ ወልድና ሥመ ክርስትና የሚቀበሉባት የእግዚአብሄር ቤተ መንግሥት ናት።(12)

## 5ኛ. <u>ደብተራ ኦሪት /The meeting-tent</u>

ደብተራ ማለት ድንኳን ማለት ነው።

(12) ዘፀ. 24÷12-18 ዘፀ. 31÷18

ይህችም የተቀደሰች ድንኳን የቃል ኪዳኑ ታቦት የሚኖርባት ሌዋውያን ህገ እግዚአብሔር፣ ህገ-ቤተክርስቲያን፣ አምልኮትና ህግ የተማሩባትና ሥርዓተ አምልኮት የፈፀሙባት ድንኳን ናት። በዚህች ድንኳን ሰውና እግዚአብሔር የተገናኙባት ስለነበረችና ስለሆነችም "የመገናኛ ድንኳን" ትባላለች።[13]

የዚህች ቅድስት ድንኳን አሠራርም ልዑል እግዚአብሔር ለሙሴ እንደ ተናገረው "በመካከላችሁ አድር ዘንድ መቅደሴን ሥሩልኝ" እኔ እንደማሳይህ ሁሉ እንደማደሪያው ምሳሌ እንደ እቃውም ሁሉ ምሳሌ እንዲሁ ሥሩልኝ" ባለው አምላካዊ ቃል መሠረት ድንኳኑ ከተሠራ በኋላ አገልግሎት የሚፈፅምላቸው ህዝበ እስራኤል በሚጓዙበት ሁሉ አብሮ የሚጓዝና በሚኖሩበት የሚተከል ድንኳን ከመሆኑም ሌላ በዚህ ድንኳን የመጀመሪያው ካህን ሆኖ እንዲያገለግል በእግዚአብሔር የተመረጠው የሙሴ ወንድም አሮን ከነልጆቹ እንደነበር ቅዱስ መፅሐፍ ያስተምረናል። በመሆኑም ካህኑ አሮንና ልጆቹ ክህነት

(13) ዘዳ. 33÷1-7



ከተቀበሉ በኋላ የሚገለገያውን ልብሰ ተክህኖ ለብሰው ፈጣሪያቸውን በቅድስና ያገለገሉባት ድንኳን ነች።[14]

ይህች ደብተራ ኦሪት በሙሴና በህዝበ እስራኤል በእግዚአብሔር ህዝቦች በብዙ ጌጥ የተሰራች በመሆኗ እስከ ነቢየ እግዚአብሔር ቅዱስ ዳዊት ቀይታ ዳዊትም የቃል ኪዳኑን ታቦት አኑሮባት ለ480 ዓመታት ያህል አገልግሎት ስትሰጥ ኖራለች።[15]

ከዚህ በላይ በስፋት የተገለፁት ከብዙ በጥቂቱ በብሉይ ኪዳን የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ሲሆኑ አገልግሎታቸውም ለአምልኮተ እግዚአብሔር እንደሆነ ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ስለ ቤተክርስቲያን በተለያዩ ሊቃውንት የተነገረውን እንመልከት።

## *ቤተክርስቲያን በሊቃውንት አነጋገር*

በተለያየ ጊዜ ብዙ ሊቃውንት ስለ ቤተክርስቲያን አመስጥረው አጉልተውና አስፍተው ፅፈዋል። ከሊቃውንት

(14) ዘፀ. 25÷8-10 ዘፀ 26÷32-34 ኢሳ. 54÷2 ዘፀ.33÷7-11
*In the temple of Tabernacle The Lord would speak to Moses face to face as a man speaks to his friend. The book of Exodos 33÷7-12
(15) ካልዕ ሳሙ. 6÷3 ቀዳ.ዜና.መዋ. 16÷1 ዕብ. 8÷9 ዕብ. 10÷1-11

አንዱ የነበረው አባታችን ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ቤተክርስቲያንን በኖህ መርከብ መስሎ ከተናገረ በኋላ "ቤተክርስቲያን ከኖህ መርከብ ትበልጣለች" ምክንያቱም የኖህ መርከብ ያዳነች ሥጋን ነው። ቤተክርስቲያን ግን የምታድነው ከሞተ ሥጋና ከሞተ ነፍስ ነውና" እንዲህም አለ ሊቁ ሲናገር "በኖህ መርከብ የነበሩ አውሬዎች በወጡ ጊዜ ከአውሬነታቸው አልተለወጡም ወደ ቤተክርስቲያን የሚገቡ ግን ከቤተክርስቲያን ሲመለሱ ዘማዊው ድንግል፣ ሐጥኡ ፃድቅ፣ ከሃዲው አማኝ ሆነው ይመለሳሉ" በማለት ተናግሮታል። [20]

አዎ! ቅድስት ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር እምላካቸውን አምነው እንደኖህ መርከብ በውስጧ የገቡ ከዘለዓለማዊ መቅሰፍት ከመርገመ ሥጋ ከመርገመ ነፍስ ይድናሉ። በክርስቶስ አምነው ወደ ቤተክርስቲያን ያልገቡ ግን ከመርከቧ ውጭ ተገኝተው በጥፋት ውሃ ከጠፉት ጋር እድል ፈንታቸው ይሆናል የመዳን ተስፋ የላቸውምና።

(20) ሃይማኖት አበው መልዕክተ ዮሐንስ አፈወርቅ



ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ284 ዓ.ም የነበሩ ሰብአ ሊቃናት የተባሉ አበውም የብሉይ ኪዳንን ከዕብራይስጥ ቋንቋ ወደ ፅርዕ (ግሪክ) ቋንቋ መልሰው ሲተረጉሙ "ካሃል" የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል "ኤክሊስያ" ብለው በመተርጎም ተናግረዋል። ይህም ማለት ኅሩያን እግዚአብሔር የተባሉ የእግዚአብሔር ምርጦች መኖሪያ አንድነትና ህብረት መሆኑን ገልፀውልናል።[21]

"ኤክሌሲያ" ማለት የተመረጡ ቤተክርስቲያን ቅድስት ማለት ነው። መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ቤተክርስቲያን በምሳሌ ሲያስተምር ቤተክርስቲያንን

*ሀ/ መንግሥተ ሰማያት /መንግስተ እግዚአብሔር/*

*ለ/ የአሳ ማጥመጃ መረብ*

*ሐ/ የንፁህ ስንዴ አዝመራ*

*መ/ የከበረ እንቁ ማዕድን*

*ሠ. የሠርግ ቤት /የሙሽራውና የሙሽሪት የክብር* ድንኳን/ በማለት ስለ ቅድስት ቤተክርስቲያን የተናገረ ሲሆን

(21) የቤተክርስቲያን ታሪክ በአለም መድረክ ገፅ ፲፩

እውነትም ቤተክርስቲያን በኃጢአት በክህደት ረክሰው የነበሩ በንስሐ በእምነት ወደ እሷ ገብተው የሚቀደሱባት ቅድስት ክብርት ንፅሒት የቅድስና ድንኳን ነች። ቅድስና የባህርዩ የሆነ ጌታ በደሙ የቀደሳት የመንፅሂ የቀዳሲ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ናት። ማህደረ መንፈስ ቅዱስ ብለን እንጠራታለን።[22] በቤተክርስቲያን ታሪክም የመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እንደሆነች የሚነገርላት "ቤተ ማርያም" ነች። የማርቆስ እናት ማርያም ቤቷን ለቅዱሳን ሐዋርያት ለፀሎት፣ ለምስጋና፣ ለትምህርተ ወንጌል ሰጥታ ስለነበር ሐዋርያትም በበአለ ሃምሳ[23] በዚሁ በማርያም ቤት ተሰብስበው በመዘመር፣ በመፀለይ፣ በማመስገን ላይ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ በእሳት አምሳል ወርዶ በላያቸው ተቀመጠ። ሁሉም ቅዱስ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ አደረባቸው በዚህም እውቀት፣ ጥበብ፣ ቋንቋ ተገለጸላቸው ጥብአትንም አገኙ። ስልጣንን ክብርም አደላቸው በመሆኑም በሐዲስ ኪዳን ዋዜማ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን እንደሆነች ተነግሮላታል የማርቆስ እናት የማርያም ቤት።

(22) የሐ. ሥ. 20÷28-33 ኤፌ.5÷25-28
(23) ጰራቅሊጦስ



የእግዚአብሔር ህዝቦች ሁል ጊዜ የዓለም ፈተና አያጣቸውምና ክርስትና እየተስፋፋ ወንጌል እየተሰበከ ቤተክርስቲያን እየተመሰረተች ስትመጣ መላዋ የሮም ግዛት በቅዱሳን ሃዋርያት ይልቁንም በቅዱስ ጳውሎስና በቅዱስ ጴጥሮስ ሀገረ ስብከትነት የምትታወቀዋ ሮም ስለነበረች ህዝቡም ቃላቸውን በመስማት፣ አምልኮተ እግዚአብሔርን በመፈለግ አምነውና ተጠምቀው ክርስትናን ሲቀበሉ መንፈስ ቅዱስ ያላደረበት ከሃዲው የሮም መንግሥት ክርስቲያኖችን ማሳደድ ቤተ መቅደሱን ማፍረስ ስለጀመረ በዘመኑ የነበሩት ክርስቲያኖችም የወገኖቻቸውን አስከሬን በሰማዕትነት ያረፉትን የክርስቲያን ወንድሞቻቸውን መቃብር ዋሻ እየቦረቦሩ መሬት ውስጥ ማደሪያ አያበጁ የሰማዕታቱን የክብር ሰውነት ባንድ ወገን በማሳረፈ እነርሱ በአንድ ወገን ሆነው በመፀለይ ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡትን ምስጋና ያለማቋረጥ ያደረሱ እንደነበር ሲናገር ይህም ቦታቸው ካታኮምብ /ግበ በምድር/ በመባል ይታወቃል። ባጠቃላይ ቤተክርስቲያን ይህን የሚመስል ገፅታ ሲኖራት ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ።

- አቤል መስዋዕት ያቀረበባት ቦታ ንፁህ ጠቦት ታቀርባታልና እሳት ከሰማይ ወርዶ በልቶለታልና እግዚአብሔርን በመስዋዕት አገልግሎብትና የቤተክርስቲያን ሽታ አላት አለ

ቀዳማዊ ጎርጎርዮስ ዘኢትዮጵያ

- አብርሃም ልጁን ይስሐቅን ለመስዋዕት ያቀረበባት ተራራ [24]

- መልዐከ እግዚአብሔር ተገልጦባታልና

- መግዐ ይስሐቅ ተተክቶባታልና

- እሳት ነድዶባታልና

ብርሃን ታይቶባታልና እንዲሁም ሰማዕታት በክብር ደማቸውን የሚያፈሱባት ለምትረተ ርዕስ የቀረቡባት እንደ ሽንኩርት የተከተፉባት እንደጎመን የተቀረደዱባት በብረት የተፈጩባት ቦታ ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ሆና ትኖራለች።

ለምሳሌ ልዳ ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ክብር ያገኘባት ብለውላታል።

---

(24) የሞሪያ ተራራ ይባላል /The Region of Moriah/



አነሆ እኛም በዘመናችን አባቶቻችን እንዳስተማሩን ፀጋን፣ ክብርን፣ ረድኤትን፣ በረከትን ስለምናገኝባት ልናከብራት ልናገለግላት ይገባናል ክብርን በረከትን እንጎናጸፍባታለንና።

## ቤተክርስቲያን በፍትሐ ነገሥት

በቤተ ክርስቲያናችን ሥጋዊው ዓለም የሌለው ሃብት አለ። ይኸውም መንፈስ ቅዱስ ለአባቶቻችን የሰጣቸው ክብርና ቃል ኪዳን ሲሆን በመንፈስ ቀዱስ መሪነት እና አስተማሪነት ብዙ መፃህፍትን ፅፈው ለነገሥታት ፍርድ እንዳያጓድሉ ደሃ እንዳይበድሉ ለካህናት በህግ እንዲፀኑ ለምዕመናን የካህኑን ቃል እንዲያከብሩ በዓላትን እንዲያከብሩ ወ.ዘ.ተ. ከሚገልፀው አንድ "ፍትሐ ነገሥት" ነው።

ፍትሐ ነገሥትን የፃፉ ሰለስቱ ምዕት ናቸው[25] ስለ ቤተክርስቲያን በተናገሩበት አንቀፅ እንዲህ አሉ።

---

(25) ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ይባላሉ።

## ለቤተክርስቲያን ልታደርጉላት የሚገባ ቢኖር

-ዛፍ አፀድ ትከሉላት

-ሐረግ ሳቡላት

-በልምላሜ አጊጧት

-እጣን እጠኑላት

-መሥዋዕት ሰውላት

- መብራት አብሩላት

- ምንጣፍ አንጥፉላት

- ብዙ የበዙ ብዙ መብራት በውስጧ ያብሩባት

- ወንጌል አንብቡባት

- የተጣላ አስታርቁባት

- ጉባዔ ሥባባት ምስጢረ መፃህፍትን ስሙባት አስሙባት

- ደሃን (ነዳያንን) እርዱባት



በሠማይ ላይ ፀሃይ ጨረቃ ከዋክብት እንደሚያበሩባት በሰባቱ ብርነናማ አምሳለ ሰማያት አምሳል ቤተክርስቲያን ብርሃን ትሁን ብለው አባቶቻችን ህግ ሰርተውላታል።[26]

## ሰባቱ ሰማያትና ቤተ ክርስቲያን

ቤክርስቲያን በሰባቱ ሰማያት ትመሰላለች የምስጋና ቤት ነችና

<u>ሰባቱ ሰማያት</u> የሚባሉት

1. ኤረር
2. ራማ
3. ኢዮር
4. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት
5. ሰማይ ውዱድ
6. መንበረ መንግሥት እና
7. ፅርሃ አርያም ናቸው።

---

[26] ፍትሐ ነገሥት አንቀፀ ቤተክርቲያን የመጀመሪያውን ተመልከት ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያም ይህንኑ ቃል በሃይማኖተ አበው ፅፎታል

ኢዮር

ራማ ⇒ እነዚህ ሶስቱ ዓለመ መላዕክት ይባላሉ።

ኤረር

- ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ቀድሞ የሳጥናኤል አሁን ደግሞ የአዳም ዘር ከተማ ሆና ተሰጥታለች[7]
- ሰማይ ውዱድ
- መንበረ መንግሥት ↗
- ፅርሃ አርያም

እነዚህ ደግሞ ዓለመ ሥላሴ በመባልሲታወቁ ዙፋኑን የተሸከሙ ኪሩቤልና በቅዳሴ የሚያመሰግኑ ሱራፌልእንኳን የአምላካቸውንመልክ ሳያውቁ ስሙን ብቻ እየጠሩ ያመሰግኑባቸዋል።*

(7) ኢሳ. 14÷12-18 ሕዝ. 28÷13-19 እነዚህ የትንቢት መልክዕክቶች የሳጥናኤልን የቀደመ ክብር በመግለጽ የንጋት ልጅ፤ የአጥቢያ ኮከብ፤ የሚጋርድ ኪሩብ፤ የተቾመው አለቃ እያሉ ይናገሩለታል።

* ሐዋርያት በቢናዶሳቸው በዲዲስቅልያ እንደፃፉት አባታችን አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በሰዓታት መፅሐፉ እንደገለጸው "ቤተ ክርስቲያን ትትሜሰል በፅርሃ አርያም ዘላእሉ" እንዲል

* ሰማይ ውዱድ ኪሩቤል የሚሸከሙት ዙፋኑ መንበረ መንግሥት የተዘረጋበት አምስተኛ ሰማይ ነው እግዚአብሔር በነቢያትና በሃዋርያት ሲመሰገን የተገለፀበትና የሚገለፅበት አርባዕቱ እንስሳ የተሸከሙት መንበረ መንግሥት ስድስተኛ ሰማይ ሲሆን ፅርሃ አርያም የመንበረ መንግሥት ጠፈር ሰባተኛ ሰማይ ነው።



ጠቅለል ባለ አነጋገር ቤተክርስቲያን ቤተ እግዚአብሔር ስትባል በሐዲስ ኪዳን የምንገኝ የክርስቶሳውያን ማለትም ክርስቶስን በማመን በጥምቀት ልጅነት ያገኘን ህዝቦች ህብረት ወይም የክርስቲያንኖች አንድነት ቤተክርስቲያን በመባል ይታወቃል። በመሆኑም በቅድስት ቤተክርስቲያን ብዙ ምስጢራት የሚገልጽ ሲሆን ጥቂቶቹም:-

ሀ. የሰውና የመላዕክት የምስጋና የዝማሬ የቅዳሴ ቦታ

ለ. ሰውና እግዚአብሔር የሚታረቁባት የእርቅና የሠላም ሥፍራ

ሐ. ነዳያን፤ ህዘ ናን ከሃዘናቸው የሚፅናኑባት ምስካየ ህዙናን

መ. የህይወት ለውጥ የምናገኝባት ማለትም

- ሃጥዑ በንስሐ ዓድቅ የሚሆንባት
- ዘማዊው በንስሐ የሚደነገልባት
- በሃጢአት የረከሰው በንስሐ እንባ የሚቀደ

ሰባትና (የሚታደስባት) የቅድስና የበረከት የይቅርታ

ሥፍራ ቅድስት ቤተክርስቲያን ነች(ምስትስራየ ሐጢአት) ናት

ክብሩ በጥቂቱ ከረጅም ባጭሩ ቅድስት ቤተክርስቲያን ይህንን የመሠለ ገፅታ ሲኖራት

ሀ. በክርስቶስ ያመኑ ህዝበ ክርስቲያን የሚኖሩባት

ለ. በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ የሚከብሩባት ማለትም ከእግዚአብሔር አምላካቸው ጋር በተዋህዶ የሚያከብሩባት

ሐ. ለዘለዓለም ርስት ሆና ከእግዚአብሔር ዘንድ የቃል ኪዳን ታቦት በክብር የሚገለፅባት ስትሆን ለዘለዓለም ስመ አምላክ ሲመሰገንባት ስለሚኖር ቅድስናን ንፅህናን ጠብቀው በእምነት ፀንተው በውስጧ ለሚመላለሱ ሁሉ እናትነትዋ የማይለወጥ ጣፋጭ የሆነው የእግዚአብሔርን ፍቅር የምታድል ረድኤትንና በረከተን የምትሸልም የክርስቶስ አካል ስትሆን የቤተክርስቲያን ሊቃውንት እንደተናገሩት ቤተክርስቲያን "ከሰማይ



ዝቅ ከምድር ከፍ ብላ ለሰማዕታት የወረደች የክብር ሽልማት የብርሃን አክሊል ትመስላለች"

መ. ክቡር የሆነው የሰው ልጅ በሃጢአትና በበደል ከረከሰ በኋላ ወደ አርሷ መጥቶ ፈጣሪውን በእንባ በፀሎት ከጠየቀ ምህረትንና ይቅርታን አግኝቶ በመንፈስ ቅዱስ ታድሶ የሚወጣባት የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ምሳሌ አማናዊቷ ቤተ መቅደስ ቤተክርስቲያን ናት።

ሠ. ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ተኝቶ ድንጊያ ተንተርሶ ህልም አልሞ የሰማይ መላዕክት ሲወጡባትና ሲወርዱባት ያያት የብርሃን መሰላል የተተከለባት ልዑል ባህርይ እግዚአብሔር በረድኤት የሚገለፅባት የክብር ድንኳን የሰማይ ደጅ የእረፍት ቦታ የክብር ሽልማት ቤተክርስቲያን ናት።

እኛም በቅድስት ቤተክርስቲያን በሃይማኖት ጸንተን የአምላካችን የፈጣሪያችን የልዑል እግዚአብሔር ታማኝ አገልጋዮች ለመሆን ያብቃን አሜን!!

# <u>ለመጽሐፉ ዋቢ የሆኑ መጻሕፍት</u>


1. <u>መጽሐፈ ሐዲሳት ሠለስቱ</u> ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1989ዓ.ም
2. <u>ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜ</u> ትንሳኤ ማተሚያ ድርጅት 1988 ዓ.ም
3. <u>መዝሙረ ዳዊት</u> ንባቡና ትርጓሜው ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1982 ዓ.ም
4. <u>መጽሐፈ ሕዝቅኤል አንድምታ ትርጓሜ</u> ትንሳኤ ማሳተሚታ ድርጅት አዲስ አበባ 1990ዓ.ም
5. <u>ሐዲስ ኪዳን በሊቃውንት ጉባኤ የተዘጋጀ</u> ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1975 ዓ.ም
6. <u>የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓም መድረክ</u> በብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀ/ስ ሊቀ ጳጳስ አዲስ አበባ 1987 ዓ.ም





7. <u>ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው</u> ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1958 ዓ.ም
8. <u>ሃይማኖተ አበው</u> ትንሳኤ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1986 ዓ.ም
9. <u>መዝገበ ቃላት</u> ኪዳነ ወልድ ክፍሌ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት አዲስ አበባ 1948 ዓ.ም
10. Justin martyr, <u>father of the Church</u> V 6 New York.
11. Josiah Royce, <u>The World and the individual</u> New York 1959
12. M.Grant Rober, <u>Christian doctrine.</u> London 1935
13. John Wisdom , <u>Nature man and the moral order,</u> Great Britain 1957
14. Hefner, <u>The human fctor</u> Dr. Philip Hefner, <u>Theology and the Sinces</u>, Minneapolis, 1993.
15. Holy Bible, <u>the Gideoьes international,</u> London 1969/
16. Hefner, <u>Problems of the history of phylosophy</u>, Dr Philip Hefner, Evolution, culture and Religion, New York 1985.

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት
*Ethiopian Orthodox Tewahedo Church*
*PATRIARCHATE HEAD OFFICE*

የመልእክት ሣጥን ቁጥር ፩ሺ፪፻፹፫
P. O. Box 1283

አዲስ አበባ
ADDIS ABABA

ቁጥር [illegible]
Ref. No.
26-4 ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ/ም
Date ............ 19 ......

ለመምህር ጥበበ ሥላሴ አሰፋ
<u>አዲስ አበባ</u>

የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት በመጠበቅ ብኩርና በሚል ርዕስ አነስተኛ መጽሐፍ ስላዘጋጀሁ በሊቃውንት ጉባኤ ተመርምሮ ለሕትመት እንዲፈቀድልኝ አመለክታለሁ በማለት በ20/3/92 ዓ.ም. የጻፉት ማመልከቻ ደርሶን ተመልክተነዋል ።

በጥያቄዎ መሠረት ብኩርና በሚል ርዕስ ያዘጋጁት ጽሑፍ በሊቃውንት ጉባኤ እንዲመረመር ታዞ የሊቃውንት ጉባኤ ጽሑፉ ከአሥራው መጻሕፍት ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሐዋርያት ሲኖዶስ፣ ከመጻሕፍተ ሊቃውንትና ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍተ ቀኖና ተውጣቶ የተዘጋጀ መሆኑን መርምሮ ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት ያልወጣና የቤተ ክርስቲያንን ብሂል የተከተለ ስለሆነ በትምህርት ሰጭነቱ ለምእመናን ከፍተኛ ጥቅም ስለሚሰጥ ታትሞ በአገልግሎት ላይ ቢውል ተፈላጊ ነው በማለት ታኅሣሥ 11 ቀን 1992 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ደርሶናል ።

ስለዚህ የሊቃውንት ጉባኤ መጽሐፉን መርምሮ በሰጠው ውሳኔ መሠረት የሥነ ጽሑፉ ዝግጅት በሕትመት ላይ ውሎ መጽሐፉ በአገልግሎት ላይ እንዲውል የተፈቀደ መሆኑን እናስታውቃለን ።

" ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር "

መልአከ ታቦር ተሾመ ዘሪሁን
የጠቅላይ ቤተ ክህነት
ም/ሥራ አስኪያጅ
M. T. Teshome [redacted]
D. General [redacted]
Ethiopian Orthodox [redacted]

<u>ግልባጭ፣</u>

ለሊቃውንት ጉባኤ መምሪያ
<u>አዲስ አበባ</u> ።